የነበራቸው ውድ የኢትዮጵያ ስጦታ ነበሩ። ከሕልሞቻቸው ጥቂቶቹን ብንመለከት፡- በአዲስ አበባ ብቻ በፒያሳና አራት ኪሎ አካባቢ የሚታዩ ትልልቅ ሕንጻዎች የዚያን ዘምን የእኒህ አባት የአእምሮ እድገትና የሀገር አሳቢነት ውጤት ናቸው። በየአካባቢው የሚገኙ የትልልቅ ገዳማት የልማት ጅምሮች የኒህ አባት ፍሬዎች ነበሩ። ወጣቱን ትውልድ ከሌሎች ሀገራት ወጣት ጋር በማገናኘት የእምነት አካሄዱንም ሆነ የስልጣኔ መስመሩን እንዲያጣጥም ያደራጁትና የመሠረቱት እኒህ አባት ነበሩ (ሃይማኖተ አበውን)።

ዛሬ ለነፋቂ የዳረገንን የደብተራና የጥንቆላ መጽሐፍ ቀዳሚ እትም ያሳተሙልን ፓትርያሪክ፣በኒህ አባት የግፍ መቃብር ላይ ቆመው የተሾሙት ናቸው። (*የ1980 ዓ.ምን 81ዱ መጽሐፍ ያሳተሙት*[236] አባ ተክለ ኀይማኖት ይባላሉ እኒህ ሰው ምንም የማያውቁ በረሸኛ ወይም ገዳማዊ ሰው ስለነበሩ በዐፄ ኀይለ ሥላሴ ጊዜ የጥንቆላ መጻሕፍቶቻቸው እንዳይታተም የተከለከለባቸው ደብተሮች ቂም ይዘው ስለነበር በኒህ ምንም የማያውቁ ሰው ጊዜ ያከናወኑት ፀረ እግዚአብሔር አጀንዳቸው ነበር[237]። ዛሬም ለሚሊኒዮም በሚል ከንቱ ፋከራ አሁን ፓትርያሪክ የሆኑት በግፍ የተገደሉት የሟቹ አባት /የአቡነ ቴዎፍሎስ/ ልጅ መሆናቸው ይታወቃል። ይሁን እንጅ ከታሪክ ተወቃሽነት እራሳቸውን ለመጠበቅ የደብተሮችን መጽሐፍ ባያሳትሙ በተሻለ ነበር። ነገር ግን "*ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣሁ*" እንዲሉ ያለ ተረት ሆኖባቸዋል። በዚህ ክፍል በስፋት የተመለከትነው የአፖክሪፓ መጻሕፍት ታሪክና አጠቃላይ ይዘት አንባቢ ከቅዱሱ መጽሐፍ ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነትና ፍጹም የሆነውን የልዑልን ቃል በአክብሮት ለመያዝ ልዩነቶችን በጉልህ እንዲመረምር ታስቦ የተጻፈ ነውና በሚገባ ቢነበብ መልካም ነው። ከንቱ የሆነውን የደብተራ ትምህርት የያዘውን ይህንን የ2ሺህ እትም መጽሐፍ ለማነፃጸር አመች እንዲሆንም እያጣቀሱ በማነጻጸር ልዩነቱን በጉልህ ለመረዳት ይጠቅማል።

---

[236] .የኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ የ1980 እትም መቅድም የመጨረሻ መግለጫው።

[237] . ከዘሁ ገጽ 4 - 5 ተመልከት



## *ክፍል ሦስት*

### *የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርና የኦርቶዶክስ ሊቃውንት የለወጡት የወንጌል ሀሳብ በልዩ ልዩ እትሞች ሲፈተሽ*

በዚህ ክፍል ውስጥ እጅግ ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ብቻ ወስደን በማነፃፀር እንገመግማለን። ጥቅሶቹም የ1980ና የ2ሺ እትም 81ዱን ከግእዝ የጥንት መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከ1954 እትም ከሮም ካቶሊክ ኢየሩሳሌም ባይብል ከግሪክና ዕብራይስጥ እናት ቋንቋዎችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይ ከሆኑ መጻሕፍት/KJV/ /ከኪንግ ጀምስ ትርጉም/ ጋር በማነፃጸር የምንዳስሳቸው ይሆናል[238]።

በአብዛኛው ጊዜ በሀገራችን የተለመደው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የ1954 ዓ.ም /1962/ እትም የተሻለና ትክክለኛ የእግዚአብሔር ቃል አድርጎ የመመልከት አባዜ በብዙዎቹ ዘንድ ይታያል። ነገር ግን ወደ እናት ቋንቋውና ወደ መንፈሳዊ መረዳት በዘለቅን ጊዜ ሁሉ ሀሳቡ የተለየ ትርጉም የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። ተርጓሚዎቹ በጊዜው የተሻለ ሥራ በመሥራታቸው ልናመሰግናቸው ይገባል። ነገር ግን መንፈሣዊ ሀሳቡን ከሃይማኖታዊ ቋጠሯቸው ጋር በማዳቀልና በማጠላለፍ ተርጉመውለታል ነው። ይህም በእነርሱ ዘንድ ያለውን የመረዳት ልክ አመላካች ሲሆን ይህኛው ትውልድ ግን የተሻለ የትርጉም ሥራን መስራት የሚጠበቅበት ይመስለኛል።

ይህንን ስገልጥ በጥቂቱ ያለውን የትርጉም ስህተት ለአንባቢ መጠቆም እወዳለሁ፡- ለምሳሌ በነፍስና በመንፈስ መካከል ያለውን ልዩነት ካለመለየት የተነሣ በቅዱሱ መጽሐፍ ውስጥ መንፈስ የሚለውን ቃልና ሀሳብ ነፍስ በሚል በመተካት መንፈሳዊ ትርጉሙ ተዛብቶአል። ይህም በልማድ ሰው ሲያርፍ /ሲሞት/ ነፍሱ ወጣች እንደሚባለው ነው። መጽሐፍ ግን መንፈሱ እንደምትወጣ ይናገራል ኢዮብ34፥14። ጌታችን ሕይወቴን በፈቃዱ አኖራታ ለሁ ማንም ከእኔ

---

[238] .BRENTO: LXX Septuaginta English BibleTtranslation &RAHLFS: LXX Septuaginta & Modern Greek Bible ከሚባሉ መጻሕፍት የተወሰደ መረጃ ነው።

*ትህትና ተመልክቶአልና»* *81ዱ* ሰውነቴ የሚለው ቃል በመጀመሪያ ለሥጋ እንጂ ለነፍስ አይሰጥም፤ልቡና ደግሞ ለነፍስ ዕውቀት የሚሰጥ እንጅ ለመንፈስ የሚሰጥ ወይም መንፈስን የሚገልጥ አይደለም:: የኛ ደብተሮች የድንግል ማርያምን ትንቢታዊ ቃል ለውጠው እርሷን ያከበሩ መስሏቸው ቃሏን ሸረው ጽፈዋል:: በዜማ የሚያንጎራጉሩት ውዳሴ ማርያምና የዘወትር ጸሎት የሚባለው የደብተሮች የድግምት መጽሐፍ ግን ***ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ወትትህሰይ መንፈስየ ባምላኪየ ወመድኀኒየ..*** ይላል ይህም ከትክክለኛው የወንጌል ቃል ጋር ይስማማል:: በ81ዱ ላይ ግን ተለውጦ የባሪያይቱን *ውርደት* ተመልክቶአልና የሚለውን *ትህትና* በሚል ቃል ተክተዋል:: ማርያምን ማክበር ቃሏን በጥንቃቄና በክብር ለትውልድ ማስተላለፍና ምክሯን መስማት ነው የሚላችሁን አድርጉ ስላለች ዮሐ2፥5 **የ1915ና የ1933ዓ.ም እትም**:-*ነፍሴ* እ/ሔርን ታላቅ ታደርገዋለች *መንፈሴም* በእ/ሔር ሐሴት ደስ ይላታል KJV For he hath regarded the low estate of his *handmaiden*: for, behold, from henceforth all generations shall call me blessed. **የግሪኩ ሙሉ ቃልም** διότι ἐπέβλεψεν ἐπὶ τὴν ταπείνωσιν τῆς ***δούλης*** αὐτοῦ. Ἐπειδὴ ἰδού, ἀπὸ τοῦ νῦν θέλουσι μὲ μακαρίζει πᾶσαι αἱ γενεαι(***δούλης*** ***means doule {doo'-lay}a female slave, bondmaid, handmaid***)

5. ***ሉቃስምዕ2ቁ7-*** «የበኩር ልጇን ወለደች አውራ ጣቱንም አሰረችው...»**81ዱ** *ይህ ሀረግ በእናት ቋንቋ አይገኝም* የአውራ ጣት መታሰር በወንጌል ያልተጻፈ ከመሆኑም በላይ በአይሁዳዊያን ታሪክ ፈጽሞ የሌለ ልማድ ነው:: በኛ ሀገር ያሉ ደብተሮች አውራ ጣት የሚያስሩት ለሟርት አሰራር ከፍተኛ እስራት ለመጠቀም ባሰቡ ጊዜ ነው:: በተለይም እናት ፈቅዳ ደሙን ከአውራ ጣቱ አስረው በመብጣት ከወሰዱ ለነርሱ ተዋርሶው /Possessed/ አጋንንት ዘንድ ትልቅ ተሰሚነትን የሚያገኙበት ነው:: ለሕፃኑ ደግሞ የእድሜ ልክ እስራትና ስቃይ ይሆንበታል:: ምክንያቱም ያሳደግሁት ነው የደም ኪዳኔ ነው እያለ አጋንንቱ ይነግስበታል:: በዚህ የድግምት አሠራር ሕጻኑ ወንድ ከሆነ ከሴት ጋር እንዳይገናኝ፤ሴት ከሆነች ወንድ የሚባል እንዳታገባ፤ብታገባ እንኳ አብሮአት የሚተኛው ሰው እንዲሞት ይሆናል::ይህ ከፍተኛ የሆነ አጋንንታዊ አሰራራቸው



ቢነቃበት ለምን የሚል ጥያቄ እንዳይነሳ የደለዙትን ወንጌል በመጥቀስ የጥንቆላ ሥራቸውን መረጃ እንዳለው ያቀርቡ ዘንድ የታረመ ነው:: እንዲህ ያለ አሰራር በቤተስኪያኒቱ ውስጥ ብዙ አለ:: **የ1915ና የ1933ዓ.ም እትም**"የበኩር ልጅዋንም ወለደች በመጠቅለያም ጠቀለለችው በበረትም አኖረችው"KJV ..And she brought forth her firstborn son, ***and wrapped him in swaddling clothes, and laid him in a manger /a place for food for cattle /***; because there was no room for them in the inn.ግሪኩም καὶ ἐγέννησε τὸν υἱὸν αὐτῆς τὸν πρωτότοκον, καὶ ἐσπαργάνωσεν αὐτὸν καὶ κατέκλινεν αὐτὸν ἐν τῇ φάτνῃ, διότι δὲν ἦτο τόπος δἰ αὐτοὺς ἐν τῷ καταλύματι. **ይላል**::

6. ***የዮሐንስ ወንጌል ምዕ1ቁ5***:-"ብርሃንም በጨለማ ያበራል ጨለማም *አላገኘውም* " **81ዱ** ይህ ሀሳብ አጠቃላይ የዮሐንስን መልእክት ካለመረዳት የተነሳ የተጻፈ ሀረግ ነው:: በወንጌሉም ሆነ በመልእክቱ በተደጋጋሚ ጨለማ፥ብርሃን የሚሉት ቃላት መንፈሳዊ ትርጉማቸው ብርሃን ክርስቶስ ጨለማ ደግሞ የዚህ ዓለም ገዥ መሆኑን ገልጦአል::ሙሴም ይኸው ሀሳብ በፍጥረት መጀመሪያተገልጦአል ዘፍ1፥2-5::ብርሃን ጨለማን ያሸነፈ ሲሆን በጨለማም አልተሸነፈም:: ያ ብርሃን በሂለኛው ዘመን በሥጋ የተገለጠ የሰው ልጆች ሁሉ ሕይወት የሆነው ክርስቶስ ነው:: ስለዚህ በጨለማ አልተሸነፈም ነው የሚባለው:: ነገር ግን ይህንን መንፈሳዊ ትርጉም ለውጠን ጨለማ አላገኘውም ብንል የመጽሐፉን ዋና መልእክትና መንፈሳዊ እሳቤ እናበላሻለን:: 81ዱ ጸሐፊዎች አባት አድርገው የያዙት የዲያቢሎስን ተልዕኮ ለመፈጸም እያከናወኑ መሆኑ ግልጥ ነው::

ምክንያቱም ከአጋንንት ሲዋረሱ /Possessed/ የክርስቶስን ደም የረጋ ነው ባንድ ወቅት የቀረበ ነው እያሉ ቃል ስለሚገቡ፤የጨለማውን ጉልበት ብርቱነትና ኃያልነትም እያጎሉ ኪዳን ስለሚለዋወጡ የዚህ ውጤት ነው:: ምክንያቱም ጨለማው አላገኘውም እንጅ ቢያገኘው ኑሮ ይሸነፍ ነበር ለማለት ነው ሀሳቡን የለወጡት:: የግእዝ ሙላቱ ግሪክ ነው ስለዚህ በግሪኩ ምን ይላል ስንል "Καὶ τὸ φῶς ἐν τῇ σκοτίᾳ

φαινει καὶ ἡ σκοτία δαὐτο κατέλαβεν αὐτό." [241] ኪንግ ጀምስም [KJV] And the light shineth in darkness; and the darkness ***comprehended*** it not. በካቶሊኩ መጽሐፍም and light shines in darkness, and darkness could not overpower it./**Jerusalem Bible**/ ይላል::

7. ***ዮሐ ምዕ2ቁ4***:- «ጌታችን ኢየሱስም አንቺ ሆይ! ካንች ጋር ምን አለኝ? ጊዜየ ገና አልደረሰም አላት» ፩ዐ፩ በዚህ ክፍል ላይ ርዕስ የሰጡት ሲሆን ርዕሱም ስለእናቱ ምልጃ ተብሎአል:: በጥንት የኦርቶዶክስ ምሁራንና በግእዝ የአንድምታ/Commentary/መጻሕፍ "*ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ ምንት ብየ ምስሌኪ ኦ ብሲቶ..." ጌታ የሱስም እንዲህ አላት አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ?... በአምላክነቱ አገብሮ ተአዝዞ እንደሌለበት ለማጠየቅ... ውሀውን ጠጅ አድርጌ የማጠጣቸው በኔ ፈቃድ እንጅ ባንቺ ትእዛዝ ነውን? አላት*" [242] ሲል ከአሁኑ የትርጉም ሂደት ፍጹም በተለየ መንገድ በግልጽና በማያሻማ ሀረግ ተገልጾአል:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አዲስ የመከራከሪያ ሀሳብና መጽሐፍ ቅዱስን ለመለዋወጥ በሚጠቀምበት ስልት "የቤተ ክርስቲያን" ቴክስት ውጤት ነው እንዳይሉን ግእዙም ሆነ አንድምታው /Commentary/ በዚህ መልክ አልጻፈውም:: ቅድስት ድንግል ተሳትፎዋ በሴትነት ጌታን ለመውለድ ከመመረጥ፣ ከማሳደግና የሰው ልጅ ይባል ዘንድ ለቀዳሚ የዘለዓለም አጀንዳው በእምነት ጸንታ በመቀበል የተባበረች ቡሩክ ሴት ነች:: ከዚህ ያለፈ ሂደት ቢኖራት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማንም ይቃወም ዘንድ አይችልም:: ነገር ግን በቅርብ ዓመታት የተፈጠረውን (ከ13ና14ኛው ክ/ዘ) በኋላ ለመጣ የጣዖት አምልኮ ጥማት ማካካሻ ሲባል ቅዱሱን መጽሐፍ መደለዝ ያልተጻፈም መቀየጥ ወንጀል ነው:: ደብተሮቹ በመደለዙ ድፍረት ረዘም ያለልምድ ስላላቸው ቅዱሱን ቃል ሲቀይሩ ችግር የለባቸውም:: የክርስትናን መጽሐፍ አስጠብቃለሁ የሚለው

[241] .Greek: *katalambano*, "to lay hold of," hence, mentally to apprehend: used of the spiritual capacity of the Christian "to ***comprehend*** (the Revised Version (British and American) "***apprehended " ; the Revised Version, margin "overcame"; compare Jn 12:35***)./ 2232 Dwight M. Pratt **ISBE DICTINARY ENCYCLOPIDA** /

[242] ወንጌል ቅዱስ ከቀደሙ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ: በተፈሪ መኮንን ማ/ቤት: 1916



የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ግን አብሮ መተባበሩና መጽሐፍ ቅዱስን መቃወሙ ያሳዝናል ያስገርማልም:: **<u>የ1915ዓ/33/ እትም</u>** "የሱስም አላት ካንቺ ጋር ምን አለኝ አንቺ <u>ሴት</u> ጊዜየ ገና አልደረሰም " **<u>የ1980 እትም (81ዱ)</u>**:: መጽሐፈ ዮዲት በተሰኘው የ81ዱ ክፍል ምዕ16ቁ7 "*ዮዲት*" የሚለውን ቃል በ2ሺ እትም ሴት ብለው ተክተዋል:: ስለዚህ *ሴት* የሚለው ቃል የሦስተኛ አካል መግለጫ እንጅ የነውር ወይም የንቀት ቃል አለመሆኑን በሚገባ ያውቁታል:: ይሁን እንጅ በዮሐንስ ወንጌል ያለውን ሴት የሚል ቃል ለመሰረዝ ምን አነሳሳቸው? ለምንስ አስፈለገ? (2ቆሮ 2፥13) አንዳንድ የዋህ ሰዎች ምንም ማለት አይደለም፤ይልቅ የክርስትናን አንድነት ማጠናከር ይሻላል:: እንዲህ ያሉ ጥቃቅን ነገሮችን ከማጉላት ይላሉ::

ነገር ግን እግዚአብሔር በድምጽ ብልጫ አያምንም:: በሕዝብ ቁጥርም አያምንም:: ይልቁንም ጥራትንና ክቡር የሆነውን ቃሉን በጥንቃቄ እንድንጠብቅለት ይሻል:: ለትውልድ መርገምን ለማስተላለፍ የሚሻ ከንቱ አእምሮ እንዲህ ያለውን ስህተት ሳይቃወም ያልፋል:: ለትውልድና ለአምላኩ ቃል የሚቀና ግን የራሱን ድርሻ ተወጥቶ ያልፋል:: ክርስትና በድምጽ ብልጫና በሆይ ሆይታ የሚኖርበት የታላቁ ሩጫ ይዘት የለውም:: በእምነት ፅናት የሚኖርበት የመንግስት ወንጌል ኑሮ ነው::በኪንግ ጀምስም <u>KJV</u> Jesus saith unto her, Woman, what have I to do with thee? mine hour is not yet come. በግሪኩ ትርጉምም Λέγει πρὸς αὐτὴν ὁ Ἰησοῦς· Τί εἶναι μεταξὺ ἐμοῦ καὶ σοῦ, ***γύναι*** δὲν ἦλθεν ἔτι ἡ ὥρα μου.

**8. *<u>ዮሐንስ ምዕ 14ቁ6</u>*:-«..ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አለ የእውነትና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ..» <u>81ዱ</u>** በብዙ ፈላስፎችና የዓለም ጠቢባን ዘንድ እጅግ አስደናቂና አስገራሚ የሆነውን ቃል ይልቁንም የክርስቶስን የማንነት መገለጫ እነርሱና አባቶቻቸው ለፈጠሩት ከንቱ ሃይማኖት መከራከሪያ ሲሉ ደልዘውታል:: እኔ ሕይወት ነኝ ቢል የሱስ በርግጥም የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጥቶ የኛን ሞት ሞቶልናልና ሕይወት ነው:: የሱስ እኔ እውነት ነኝ ቢል ከእርሱ ውጭ እውነት የለም:: ትክክል የሆኑ ብዙ ነገሮች ይኖራሉ፤

እውነት ግን አንድ ብቻ ነው እርሱም ክርስቶስ የሱስ ነው:: እኔ መንገድ ነኝ ቢል በርግጥ ያለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት አልተቻለምና ይገባዋል:: ሰውና እግዚአብሔር ተለያይተው ከኖሩበት የኃጢአት ግድግዳ በመስቀሉ አፍርሶ አገናኝቶአል:: የኞቹ ደብተሮች *<u>እኔ እውነትና ሕይወት</u> መንገድ ነኝ* የሚለውን ሀረግ ለሙት መንፈስ አምልኳቸው ለመስጠት ሲሉ ለውጠው የጌታዬን የማንነት ባህርይ መገለጫ ደልዘዋል:: በእናት ቋንቋው በግሪኩም Λέγει πρὸς αὐτὸν ὁ Ἰησοῦς· Ἐγώ εἰμι *<u>ἡ ὁδὸς καὶ</u>* *<u>ἡ ἀλήθεια καὶ</u>* *<u>ἡ ζωή·</u>* οὐδεὶς ἔρχεται πρὸς τὸν Πατέρα, εἰ μὴ δί ἐμοῦ (I am the way)(I`m the truth)(I`m the life) በ<u>KJV</u> Jesus saith unto him, I am the way, the truth, and the life: no man cometh unto the Father, but by me..

**9. *<u>የሮሜ መልእክት</u> ምዕ2ቁ27*:-"ተገርዘህ ኦሪትን ከምታፈርስ በተፈጥሮ ያገኘሃት አለመገረዝህ አብራህ ብትኖር ይሻልሃል" *<u>81ዱ</u>*** ግርዘት በአባቶች በአብርሐም የተጀመረ ሲሆን ሕግ በሙሴ የመጣች ነች:: የግርዘት ኪዳን ከሕግ በፊት የነበረች መሆኗን የማያውቁት ደብተሮች የሕግ ምሁሩ አይሁዳዊ ጳውሎስ የጻፈውን ወንጌል ሊያስተካክሉ ደፍረው መሞከራቸው የሚያሳፍር የመነይምነት ቅሌት ነው:: ኢትዮጵያ ግዝረትን የተቀበለችው ሕገ ኦሪትን ስለምትከተል ነው ይባላል:: በርግጥ አልተከተለችም ለማለት ባያስደፍርም የጎረቤቶቻቸውን ጣዖት አምላኪያን ፀረ ኦሪት ፀረ ይሁዲ የሆነውን የሴት ልጅ ግርዛትም ተቀብላ ኖራለች[243] በሕገ ኦሪት ሴት አትገረዝምና:: ስለዚህ ኦሪትንም ጣዖት አምልኮንም ተቀብለናል ቢባል ታሪክ ስለሆነ ልንቀበለው ይገባል:: በሐዲስ ኪዳን ዘመንም ይሁን አሁን ያለችዋ ኦርቶዶክስ ጥቂት የክርስትናን በርካታ የጣዖት አምልኮን ሀሳብ፤ ይዛለች ሲባል ከበቂ መረጃ ጋር የሚታይ ተጨባጭ እውነታ ስለሆነ ልንቀ በለው ይገባል:: ሪፎፍሜሽንንም መቀበል አዋቂነትና መንፈሳዊነት ነው **የ1915ና <u>/33/ እትም</u>:-** "ሳይገረዝም ሕግ የሚጠብቅ አይፈርድብህም ባንተ በመጽሐፍና

[243] .በቀ/ዶ/ምክረሥላሴ : የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመ/ቅ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ: ገጽ 13 /E. Ullendorff, Ethiopia & the Bible P.105 /



በግዝረት ሕግ አፍራሽ የምትሆን.." <u>KJV</u> And shall not uncircumcision which is by nature, if it fulfil the law, judge thee, who by the letter and circumcision dost transgress the law **የግሪኩ ቃልም** καὶ ὁ ἐκ φύσεως ἀπερίτμητος, ἐκτελῶν τὸν νόμον, θέλει κρίνει σὲ ὅστις, ἔχων τὸ γράμμα τοῦ νόμου καὶ τὴν περιτομήν, εἶσαι παραβάτης τοῦ νόμου **ይላል**::

**10. *<u>ሮሜ</u> <u>ምዕ8ቁ34</u>*- "*የሚፈርድ ማን ነው?...ደግሞ ስለእኛ <u>የሚፈርደው</u>* ኢየሱስ ክርስቶስ ነው"*<u>81ዱ</u>*** የተሠመረበት ቃል በየትኛ ውም ትርጉም የሌለ ከመሆኑም በላይ ሰው የሆነበትን ዓላማ የሚቃወም የአውጣኬ /የኦርቶዶክስ ካራ/ ትምህርት ነው:: የቤተ ክርስቲያን ቴክስት የሚሉትን የክህደት አባዚያቸውን እንኳ ያልተከተለ ነው:: በግእዙ መጽሐፍ *<u>ወይትዋቀስ በእንቲአነ</u>* ይላል ትርጉሙም ስለእኛ የሚከራከረው ማለት ነው:: ኪንጅ ጀምስም<u>KJV</u> Who *is* he that condemneth? *It is* Christ that died, yea rather, that is risen again, who is even at the right hand of God, who also maketh ***<u>intercession</u>*** for us. በግሪኩ ίς θέλει εἶσθαι ὁ κατακρίνων Χριστὸς ὁ ἀποθανών, μᾶλλον δὲ καὶ ἀναστάς, ὅστις καὶ εἶναι ἐν τῇ δεξιᾷ τοῦ Θεοῦ, ὅστις καὶ μεσιτεύεῖ(ἐντυγχάνω ***to meet a person,for the purpose of consultation,or supplication to pray***)ὑπὲρ ἡμῶν. ይላል:: ***<u>የ1933</u>*** እትም ደግሞ"..ማነው የሚኮንን ክርስቶስ የሱስ የሞተ ነውን ከሙታንም እንኳ የተነሣ በእግዚአብሔርም ቀኝ የተቀመጠ እርሱም ***<u>ያስምረናል</u>***" ይላል::

**11. *<u>1ኛ ቆሮ ምዕ1ቁ18</u>*** :- " የመስቀሉ **<u>ነገር</u>** በሚጠፉ ሰዎች ዘንድ ስንፍና ነውና ለምንድነው ለእኛ ግን የእግዚአሑር ኀይል ነው" ***<u>81ዱ</u>*** ከ15ኛው ክ/ዘ በሂላ በዐፄ ዘርዓያዕቆብ ለገባው ከንቱ ትምህርት ቅዱሱን የዘመናት ሽማግሌ መጽሐፍ መሠረዝና መደለዝ ተገቢ አይደለም:: የዚህ ምዕራፍ ዓውድ አጠቃላይ የሚናገረው ስለመስቀሉ ኀይል ነው:: ቁ24 ይህ ቃል የእግዚአብሔር ጥበብ የተባለው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ይላል:: መስቀል እንጨት አይደለም ድኅነትም በእንጨቱ አልተገኘም:: የተሰቀለው ግን ከድንግል የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ነው::በእርሱ የማያምኑትም ሰነፎች ይባላሉ ስንፍና አለማመን መሆኑንም መዝሙረኛው ዳዊት ይናገራል እንዲህ ሲል"*<u>ይብል አብድ በልቡ አልቦ እግዚአብሔር ሀሰሩ ወረኩሱ</u>*

አባታችሁ ሲል የሃይማኖተኞችን ሀሳብ የሚያፈራርስ ሀረግ ተናግሮ መገኘቱ ነው ዮሐ20 ቁ 17፡፡ ስለዚህ ቃሉ የሚደግፈውን የጌታን ሀሳብ መቀበል ማስተዋል ነው መታደልም ነው፡፡ KJV Blessed *be* the God and Father of our Lord Jesus Christ, which according to his abundant mercy hath begotten us again unto a lively hope by the resurrection of Jesus Christ from the dead, የግሪኩ ሙሉ ቃልም Εὐλογητὸς ὁ *Θεὸς* καὶ *Πατὴρ* τοῦ *Κυρίου* ἡμῶν *Ἰησοῦ Χριστοῦ*, ὅστις κατὰ τὸ πολὺ ἔλεος αὐτοῦ ἀνεγέννησεν ἡμᾶς εἰς ἐλπίδα ζῶσαν διὰ τῆς ἀναστάσεως τοῦ Ἰησοῦ Χριστοῦ ἐκ νεκρῶν, ይላል፡፡

13.*1ኛ ዮሐንስ ምዕ2ቁ1*፡-"ልጆቼ ሆይ! እንዳትበድሉ ይህን እጽፍላችሂለሁ የሚበድልም ቢኖር ከአብ ዘንድ ጰራቅሊጦስ አለን የሱስ ክርስቶስም ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ጻድቅ ነው" **81ዱ** ይህ ክፍል ሙሉ በሙሉ ሀሳቡ የተለወጠ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ የአውጣኬን ትምህርት በአደባባይ እንደምትቃወም ብታውጅም በውስጥ መተዳደሪያዋ ግን ትምህርቱን ማራመዷ የአደባባይ ምሥጢር ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ የአውጣኬ ትምህርት "መለኮት የሥጋን ባህሪይ አጠፋው" የሚል ነው፡፡ ከትንሣኤ በሂላ መለኮት ሥጋውን ወይም ትስብዕቱን ውጦታል፤አሁን በሰማይም ተማላጅ እንጅ ስለእኛ የሚታይ አይደለም፡፡ በሰማያዊዋ መቅደስ በሕያው ደም የሚታይልን ጠበቃና ዋሳችን አይደለም የሚል አስተምህሮ ያቀርባሉ፡፡ ከንቱ የሆነውን የሃይማኖት ሀሳባቸውንም ለማቆም ሲሉ መሠረዝና መደለዛቸውም ምሥጢሩ ይኸው ነው፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያውኑ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ነው ዮሐ8፥40፡፡

ለሐዲስ ኪዳን ትርጉም የግሪኩን እናት ትርጉም አንቀበልም ያሉት የኦርቶዶክስ ሊቃውንት ነን ባዮች፤አንባቢን ለማደናገር ሲሉ የግሪኩን ትርጉም ሳይሆን እንዳለ የግሪኩን ቃል አስቀምጠውታል፡፡ ጠበቃ የሚለውን የጥንት የአማርኛ ቃል ቀየረውም ጰራቅሊጦስ በሚል ትርጉም /ፍች/ አልባ የግሪክ ቃል አሳትመውልናል፡፡ ክፍሉ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ካለ በኋላ በቁ2 እርሱም የኀጢአታችን ማስተሰሪያ ነው ይላል፡፡



በአደባባይ እንደምትቃወም ብታውጅም በውስጥ መተዳደሪያዋ ግን ትምህርቱን ማራመዷ የአደባባይ ምሥጢር ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ የአውጣኬ ትምህርት "መለኮት የሥጋን ባህሪይ አጠፋው" የሚል ነው፡፡ ከትንሣኤ በሂላ መለኮት ሥጋውን ወይም ትስብዕቱን ውጦታል፤አሁን በሰማይም ተማላጅ እንጅ ስለእኛ የሚታይ አይደለም፡፡ በሰማያዊዋ መቅደስ በሕያው ደም የሚታይልን ጠበቃና ዋሳችን አይደለም የሚል አስተምህሮ ያቀርባሉ፡፡ ከንቱ የሆነውን የሃይማኖት ሀሳባቸውንም ለማቆም ሲሉ መሠረዝና መደለዛቸውም ምሥጢሩ ይኸው ነው፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያውኑ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ነው ዮሐ8:40፡፡

ለሐዲስ ኪዳን ትርጉም የግሪኩን እናት ትርጉም አንቀበልም ያሉት የኦርቶዶክስ ሊቃውንት ነን ባዮች፤አንባቢን ለማደናገር ሲሉ የግሪኩን ትርጉም ሳይሆን እንዳለ የግሪኩን ቃል አስቀምጠውታል፡፡ ጠበቃ የሚለውን የጥንት የአማርኛ ቃል ቀየረውም ጰራቅሊጦስ በሚል ትርጉም /ፍች/ አልባ የግሪክ ቃል አሳትመውልናል፡፡ ክፍሉ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ካለ በኋላ በቁ2 እርሱም የኀጢአታችን ማስተሰሪያ ነው ይላል፡፡

ስለዚህ የሰው ልጆች የኀጢአት ይቅርታን ያገኙት በክርስቶስ የሱስ ከሆነ እንዴት በቀን ስሌት አካላዊ ማንነትን ይለውጣሉ? ዮሐንስ ሲጽፈው ክርስቶስ ከሞተ ከተቀበረና ከተነሣ ብሎም በአባቱ ቀኝ ከተቀመጠ በሂላ ነው፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስንም ሆነ ጳውሎስን ያረሙት ብሎም መንፈስ ቅዱስን ያስተካከሉት የሀገራችን ደብተሮች መናፍቅ መባል ካለባቸው ከእነርሱ የበለጠ መናፍቅ በየትኛው ዓለም ይገኛል? ለምንስ የጥንት አባቶች እንደተረጎሙት ይህንኑ ቃል አልተጠቀሙም? ***በ1933 እትም ይህንኑ ሀረግ ስንመለከት*** "ልጆቼ ሆይ! ይህችን ነገር እጽፍላችኋለሁ ኀጢአትን እንዳሰሩ ከላንትም ምንም ኀጢአት ቢሰራ ***ከአብ ዘንድ አማላጅ አለን የሱስ ክርስቶስ*** ጻድቅ" ይህም በዘለዓለም መንፈስ በቀረበው ደም ማለት እንጅ በየዕለቱ ጎንበስ ቀና እያለ አባቱን አብን ይለምናል ይማጠናል ማለት እንዳይደለ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ የአንድ ሃይማኖት ድርጅት ሀሳብን ለማራመድ ሲባል መጽሐፍ ቅዱስን መለዋወጥና መሰረዝ መደለዝ አላዋቂነት ነው፡፡

14. **በኢሳይያስ ምዕ53ቁ8ና10** ላይ "በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ ሕይወቱ ከምድር ተወግዷልና ልደቱን ማን ይናገራል?"...ስለኀጢአት መሥዋዕትን ብታቀርቡ ሰውነታችሁ ረዥምም ዕድሜ ያለውን ዘር ታያለች" ይላል (*የ2ኛ*

***81ዱ***):: ስለኀጢአት መሥዋዕት ብታቀርቡ የሚለው ሀረግ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ ነው:: ስለኀጢአት መሥዋዕትን ያቀረበ ክርስቶስ ነው ኤፌ5÷2:: በሌሎች የጥንት ትርጉሞችና በ1980 የ81ዱ "በማስጨነቅና በፍርድ ተወገደ ስለሕዝቤ ኀጢአት...እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ነፍሱን ለኀጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል.." ይላል በጥንቱ ***በ1915/33*** ደግሞ "..ስለወገኔ ኀጢአት ተቀሠፈ..".. ነፍሱን ስለ ኀጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል" ይላል 81ዱ ፍጹም ስቶአል:

***ማጠቃለያ*** :- በዚህ ክፍል ውስጥ አጠቃላይ ግንዛቤን የምናገኘው በንጽጽርና በተዛምዶ ልዩነቶችን በልዩ ልዩ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናበት ነው:: ሁሉንም ትጉሞች የምንመዝንባቸው ደግሞ ብሉይ ኪዳን በግሪክ ቋንቋ ስለሆነ በመጀመሪያ የተጻፈው በዚሁ በእናት ቋንቋው ሲሆን፤ ብሉይ ኪዳንን ደግሞ በዕብራይስጥ በማነጻጸር ብቻ የሚፈታና ዋናውን የተጻፈበትን ዓላማ ማግኘት ይቻላል:: የዚህ ክፍል /ምዕራፍ/ አላማም በሁሉም ትርጉሞች ልዩነቶችን በማነጻጸር ማጥናት እናት ቋንቋውንም ማጣቀስ ተገቢ መሆኑን እንድንረዳ የሚጠቅም ነው:: ከሁሉም ይልቅ ሃይማኖተኞች የራሳቸውን የጎጆ አስተምህሮ /ዶክትሪን/ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማስገባት ወደራሳቸው ሀሳብ ለማስጠጋት ለማቀራረብ የሚጠቀሙበትን ከንቱ መላና ዘዴ በማፍረስና በተገቢው መንገድ በመቃወም ስህተታቸውን ማሳየት ነው:: ለቃሉ የምንጠነቀቅና የተጻፈበትን ዓላማ መረዳት ለሚፈልግ ደግሞ በሚገባ ሀሳቡንና መልዕክቱን በመረዳት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ብቻ ለመታዘዝ ብሎም ፈቃዱን ለመፈጸም ማስተዋልን እንድናገኝ እንዲያግዝ ታስቦ የተሰራ ነው:: ስለዚህ በጥንቃቄና በማስተዋል በድጋሚ ብንመለከተው እንጠቀምበታለን::

## ክፍል አራት

### ገመና ዘሰማንያ አሀዱ (81ዱ)

### *የአዳም ቋንቋ ግእዝ አለመሆኑን ሰማንያ አሀዱ አጋለጠ*

የግእዝን ቋንቋ ከየት መጣ ታሪክ ስናጠና ከሳባውያን ፊደል "አበገደ" እንደሚነሳና በፍሬምናንጦስ /አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን/ የዕብራይስጥና የዓረብኛን የአናባቢ ፊደላት በማዳበሪያነት በመጠቀም የአናባቢ



ቅጥያዎችን በመጨመር ያደገ መሆኑን እናያለን [182]:: ከአባ ፍሬምና ንጦስ በሂላም ዘጠኙ መነከሳት /፱ቱ መነከሳት/ ይህንኑ ግእዝ ካጠኑ በሂላ ብዙ መጽሐፍትን በመተርጎም ግእዝን እንዳስፋፉ በታሪክ ይነገራል[183]:: በሌላ መልኩ ደግሞ አባ ፍሬምናንጦስና ባልደረቦቹ ለፊደላቱ አናባቢ ሲያደርጉ ከዓለም የሴም ቋንቋዎች ለይተው ገለልተኛ አድርገውናል የሚሉ ወገኖች አሉ:: ምክንያቱም ከ"*አበገደ*" የሚጀምረው ፊደል ወደ ሀሁሂ.. ሆሂያት መፈደሉ ከዕብራይስጥም ሆነ ከሌሎች ጋር እንዳንገናኝ አግልሎናል ባዮች ናቸው::

የኦርቶዶክስ የሊቃውንት ጉባኤ መሪ የነበሩት አለቃ አያሌው ታምሩ "ግእዝ እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰው ጋር የተነጋገረበት የአዳም ቋንቋ ነው፤ሰባት የድምጽ ንብረት /አናባቢ/ ያለው ብቸኛ ነው" ሲሉ ብዙ ይከራከሩ ነበር[184]:: መረጃ ቢስ የሆነው ልብ ወለድም ሀገር ወዳድ ነን በሚሉ ምሁራን ዘንድ ሳይቀር ሰርፆ በመግባቱ ግእዝ የአዳም *ቋንቋ* ነበር ይላሉ[185]:: ስንኳንስ የአዳም መግባቢያ መሆኑን መረጃ ሊያቀርቡ፤ብሉይ ኪዳን በግእዝ ተጽፎአል ለሚሉት ወግ እንኳ መረጃ ማቅረብ አልቻሉም[186]:: ሰባት ርባታ የኖረው ከ340 ዓ.ም.ቧላ መሆኑን ያላጣሩ ምሁር ባዮችም ይህንን መረጃ ይጠቅሳሉ /ሀሁሂሃሄህሆ የሚለውን ርባታ/ይሁን እንጅ በዚህ ሁሉ ንትርክ ውስጥ በተለምዶ 81ዱ የሚባለው መጽሐፍ በመጽሐፈ ኩፋሌ ምዕ11ቁ13 ላይ" *ፍጥረቱ በተፈጠረበት በዕብራይስጥ ቋንቋ ከእርሱ ጋር እናገር ጀመርኩ...እነዚያም የዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈባቸው ናቸው ከዚያም ቀን ጀምሮ ይማራቸው ጀመር...*" ይላል:: ሊቃውንት ተብየዎች እንዴት ሳያርሙት ይህ ጽሑፍ ከእጃቸው እንዳመለጠ ብዙዎቹን

---

182 . ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መቅድም 4ኛ ክፍል

183 . መልክዐ ከሣቴ ብርሃን ሰከናፍሪክ አንቀጽ፤እንዲሁም በስንክሳር የሐምሌ ንባብ ይገኛል::

184 .ኢትኦፕ ጋዜጣ፡ ሐምሌ 30 1995ዓ.ም. ከአለቃ አያሌው ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ

185 .ንቡረ እድ ኤርምያስ:ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት:1996:ቼምበር ማ/ቤት:ገጽ141-142

186 .የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር:ቃሉ ይናገር መጽሔት: ልዩ ዕትም ቁጥር 3 ገጽ20

አስደምሞአል፡፡ ግእዝ ከጥንት ቋንቋዎች መካከል አንዱ ሲሆን እንደ ቋንቋነቱ ብቻ ተቀብለን ለትውልድ ማስተላለፍ ብንችል ጥሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም ለዛሬዎቹ አማርኛ፣ትግረና ትግርኛ ቋንቋዎች ፊደላትን ያበረከተ ምሉና ሰፊ ቋንቋ በመሆኑ እንዳይጠፋና እንዳይረሳ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ቋንቋውን ማመናፈስና ከሃይማኖት ቋጠሯቸው ጋር ማዳቀሉ ግን የቋንቋውን እድገት ያቀጭጨዋልና አጉል ተረት ነው፡፡ የግእዝ አባት ከወደደቡብ ዓረብ የመጣው የሳባ ቋንቋ ነው[187] ስለዚህ ምንጩ እየታወቀ የአዳም ቋንቋ ነው ማለቱ ያስቃል ያሳፍራልም፡፡፣

*<u>በየጎዳናው ስንደባደብ፤የተቀበረ አስከሬን አውጥተን ስንጥል፤ትዳር ስናፈርስ ኖረን፤81ዱአችን ግን የሞቱ ጻድቃን አያማልዱም አለን</u>*

ጻድቃን ያማልዳሉ ድንግል ማርያምም፣መላእክትም ድርሻ አላቸው ኡራኤል፣ራጉኤል ብለውን ነበር፡፡"የቤተ ክርስቲያናችን" ሊቃውንቶች 81ዱ መጽሐፋቸውን ያነበቡት አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ጻድቃን አያማልዱም ይላልና፡፡ "የቤተክርስቲያኒቱ" የመጽሐፍት ወሳኝ አካል የሚባለው ሲኖዶስም በቁጥር የማያውቃቸውን ገድላት ከየጥሻው እያወጣ ያማልዳሉ ብሎናል፡፡ እንዴት አንድየ እያለ! ይህ ነገር ለሌላ ይሰጣል? የሚል ጥያቄ ከተነሳም ግንዱን ሲሰነጥቁት፣መብረቁን ሲያወርዱት፣ውሃውን ሲያፈሉት፣እያሉ ስለሚያስፈራሩን ያለን አማራጭ ልክናችሁ አሜን ! እያሉ መኖር ነበር፡፡ ክብር ለመድኀኔ ዓለም ይሆንና የውስጥ ዓይናችንን ሲያበራው (2ቆሮ4፥6፤ኤፌ1፥18) ሁሉም የደብተራ ወሬ ብቻ መሆኑ ተገለጠ፡፡ እኛም ሌት ተቀን የተከራከርንላቸው፤በየጎዳናውና በየመንደሩ በየአደባባዩና በየዓውደ ምሕረቱ ቢያንስ የአንድ ጎልማሳ እድሜ ያህል ባልና ሚስትን ልጅና እናትን የለያየንላቸው፤በሐዘንና በደስታ ተደጋግፈው የኖሩ ጉርብትናዎችን የበተንላቸው፤በአዋጅ በየመድረኩ የ2ናየ3 ቀንሬሳ ከመቃብር አውጥተን የወረወርንላቸው[188]፤በሌሊት በር ገልብጠን ከልጅና

[187] .ተ/ጻድቅ መኩሪያ፡የኢትዮጵያ ታሪክ ኑቢያ-አክሱም ዛጉዌ፡1951፡ትንሣኤ ማ/ቤት ገጽ 19

[188] በሰሜን ሸዋ ደብረሲና ከተማ 3 ጊዜ የተቀበረ አስከሬን ከመቃብር ወጥቶ ተጥሎል (ሕይወት መንፈሳዊ ጋዜጣ የታህሣስ ወር 1991 እትም)



ከሚስቶቻቸው ፊት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረን ሰው እንደ እንስሳ በመጥረቢያ የከተከትንላቸው[189] ሙታን ጻድቃን የምንላቸው እንደ ማያውቁንና እንደ ማናውቃቸው፤በነፍሳችን ጉዳይም እንደ ማይመለከታቸው አዲሱ እትም 81ዱ በግልጥ ተርኮልናል፡፡

ምንም እንኳ ውሸት ሲያረጅ እውነት ይመስላል እንዲሉ ሆኖ እንጅ *የጻድቃን የሰማዕታት ምልጃ፣ የስዕልና የእንጨት ስግደት ጣዖት አምልኮ ነው፡፡ ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ያልተረከብነው ክህደት ነው ሲሉ* ብዙ አባቶቻችን በንጉሥ ዐፄ ዘርዓያዕቆብ እጅ በሰይፍ የተቀሉ፣ትዳር ልጆቻቸውን ያጡ፣ ጥረው ግረው ያፈሩትን ንብረትም ለእሣት የገበሩ ከ13ኛው - 15ኛው ክ/ዘመን ብዙ ነበሩ[190]፡፡ ዐፄው ከምሥራቃውያን ጉብኝታቸው በኋላ በየቦታው ላመጡት የጣዖት አምልኮ ልማድ የኦርቶዶክስን "ቤተክርስቲያን" ሲያምሷት ከደብተሮቹ በስተቀር ሕዝቡ አምርሮ ተቃውሞ ነበር፡፡ ይህ ታሪክ በንጉሡ ዜና ገድል በደቂቀ እስጢፋኖስ፣በገድለ አንውና በነአባ አበከረዙን ገድላት ተጽፎ ይገኛል[191]፡፡ ክርስትና ጀህድ የሆነባት "ቤተ ክርስቲያን" ዛሬም ከዚህ ግብሯ አለመለየቷን በመረጃዎች እንመለከታለን፡፡ 1ኛ. መምህር ዳምጠው ደመላሽ ይባላሉ በምዕራብ ጎጃም ሜጫ ወረዳ መራዊ ከተማ በመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወገናቸውን በመምህርነት ያገለግሉ ነበር፡፡ ከዕለታዊ የሥራ ገበታቸው ውጭ በትርፍ ሰዓታቸው የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር፡፡ስለፍቅሩና መሀሪነቱም ያስተምሩ ነበር፡፡ ይህንን የፍቅር አምላክ በትምህርትም ሆነ በሕይወት ኑሮአቸው የተመለከቱ ምስኪን ጣዖት አምላኪያን፤አምላክ ማለት የዳምጠው አምላክ ነው፡፡ እያሉ በፍቅር በመማረክ ከጣዖት አምልኮ ብዙዎች ስለፈለሱ፤የሰዎችን መዳንና ወደዘለዓለም ርስት መመለስ የማይወደው ክፉ ሰይጣን ደብተሮችንና የበተስኪያን መሪዎቹን አስተባብሮ ከምሽቱ 3 ሰዓት በተኙበት ቤታቸው ውስጥ በር ገልብጠውና ሰብረው ከ2 ልጆቹ መካከል ጭንቅላቱን በመጥረቢያ ከፈነከቱት ቢሂላ በዚህ ያልረኩት ኀይማኖተኞች ለሃይማኖቴ እሞታለሁ የሚል መፈክር በማሰማት የወደቀውን አስከሬን ጽድቅ እንደሚያገኙበት እንደተማሩት በዱላ እየተጋገዙ ይቀጠቅጡት ነበር፡፡ የጉዳዩ መንስኤ ሲጣራም እናቱን ከደው ልጁን እመኑ እንዴት ይለናል? የሚል ነበር፡፡ መምህር ዳምጠው የሙሉ ወንጌል ቤተ

[189] . ጴርጋሞን መንፈሳዊ መጽሔት 1994ዓ.ም

[190] .ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡ከዐፄ ይኩኑ አምላክ - ዐፄ ልብነ ድንግል 2ኛ መጽሐፍ፡ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት፡ ገጽ 191

[191] . ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ገዳም 1996ዓ.ም

ክርስቲያን አባልና የወንጌላዊነትን አገልግሎትም ያገለግሉ ነበር። ውሸት ሲያረጅ እውነት መሰለና አባቶቻችን እናመልክም ብለው ለሞቱበት ጣዖት አምልኮና የሙት መንፈስ ልማድ ዛሬ አሣዳጅ ሆኑለት:: ለሃይማኖቴ እሞታለሁ የሚል የቂል መፈክርም ተነገበለት:: ክርስትና በመሞት እንጅ በመግደል፣በፍቅር እንጅ በማሳደድ፣እራስን በመስጠት እንጅ ለራስ በመከራከር አልተመሠረተም:: መሪው ይህንኑ ብቻ ነበር ያስተማረው ለዚሁ ገዳይ ዓላማ ሲባል የቀደመችው ቀጥያለችው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣችልን ሃይማኖት የሚል ዜማና ግጥም ተደርሶለት እንደ ጦር አዝማች ስሜት መቀስቀሻ ሆኖአል:: 2ኛ.ወጣት አሰለፈች መንገሻ በሰሜን ሸዋ ዞን ደብረሲና ከተማ ነዋሪ የነበረች ስትሆን ስለ እርሷ ኀጢአት ሲል ነፍሱን በመስቀልላይ አሳልፎ በመስጠት ከኀጢአትና ከሞት እስራት ነጻ ያወጣትን ብቸኛ አዳኝ የሱስ ክርስቶስን በመከተሏናጣዖት አምልኮን በመተዋ ምክንያት የተበሳጩ ደብተሮች ከዚህ ዓለም መስከረም 25ቀን ስትለይ የተቀበረችበትን አስከሬን ከ10ቀናት በሗላ እፈላልገው በማግኘት ሀውልቱን በመፈንቀል አስከሬን አውጥተው ወደገደል ሲልኩት ገደሉ አፋፍ ተንጠልጥሎ በመቅረቱ በሕዝቡ ፍለጋ እንደገና የተቀበረ ሲሆን፣ወንጀሉን በፈጸሙ አካላት ላይ  ግን ምንም ዓይነት እርምጃ ባለመወሰዱ ሲደግሙት እንደገናም ሲፎክሩ የሚች ቤተሰቦች ወደሌላ ሀገር ወስደው ለማሳረፍ ሲሉ አስከሬኑ ለ3ኛ ጊዜ መውጣቱን *ሕይወት በተሰኘ መንፈሳዊ መጽሔት* ማዝበባችን ይታወሳል:: (አሰለፈች የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያን አባል ነበረች) በተለምዶ 81ዱ የተሰኘው መጽሐፍ ጻድቃን አያማልዱም የሚለን *በመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ምዕራፍ6ቁ34-37* ክፍል ነው"አባቶችም ለልጆቻቸው ልጆችም ለአባቶቻቸው እንዲሁም ዘመድ ለዘመዱ መለመን ይችላሉን? ... ዛሬ አባት ልጁን ስለ እርሱ፣ ልጅም አባቱን፣ጌታም አገልጋዩን፣ ወዳጅም ወዳጁን፣ስለ እርሱ ታሞ ይተኛ ዘንድ፣በልቶ ጠጥቶ ደስ ይለው ዘንድ፣ይፈውሰው ዘንድ እንደማይልከው፣እንዲሁ አንዱ *ለሌላው መለመን ፈጽሞ የሚችል ማንም የለም፣ የራሱንም ሸክም በባልንጀራው ላይ የሚመልስ ማንም የለም ሁሉም ዋጋውን ያገኛል፣ ሥራውም የየራሱ ነውና* " ሲል በስፋት ያብራራል:: ስለዚህ አንዱ አንዱን ለማዳን የማይቻል ከሆነ፤ የሞቱ ጻድቃን ያድኑኛል ያማልዱኛል በማለት በየሙታን መቃብሩ በባዱ እግሩ የሚኀርፈው ያገሬ ሰው በከንቱ ነውና እባክህ ተመለስ በሉት፤ የወንጌሉ ቃልም እንዲሁ ነው የሚለው /ራዕ22፥12፤ሕዝ14፥14፣16፣20፤መዝ49፥7/::



በየመንደሩ ከዕቁብና ከእድር የተለያዩትን ፣ጋብቻቸውን የናዱትን አምላካችንም በቅዱስ ቃሉ "መፋታትን እጠላለሁ" (ሚልክያስ 2፥16) ስላለ የዘመመ ጎጆና የፈረሰ ትዳር ይመስለ:: ክርስቶስ የሠላም አለቃ ስለሆነ አስታርቄ ገድልና ድርሣናቱ ውልና መነሻ የለሽ ናቸውና በከንቱ የደብተራ ትምህርት አትሳቱ ማለት ጥሩ ነው::

## *ከትንሣኤ በሂላ ዘረኝነት በሰዎች ነግሦ ይኖራል*

በተለምዶ 81ዱ የተሰኘው መጽሐፍ በ1ኛመቃብያን 10፥1-3 "ከአባቶቻቸው መቃብር ውጭ ሊቀበሩ ያልወደዱ ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ያነሳና በትንሣኤ ጊዜ ከዘመዶቻቸው ጋር በአንድነት እንዲነሱ ነው" ሲል ምላሹን ይሰጣል:: በዚህ ክፍል ከአዳም ጀምሮ ኖህ፣ ሴት፣አብርሐም፣ይስሐቅና ያዕቆብ እንዲሁም ሙሴና አሮንን በአንድ መቃብር እንደ ተቀበሩ ይጠቅሳል:: ፀሐፊው የእስራኤልንም ሆነ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ የማያውቅ ነው:: በኖህ ዘመን አዳምና አቤል የት እንደተቀበሩ አይታወቅም፤በነአብርሐም ዘመን ደግሞ ኖህና ሴም የት እንደተቀበሩ አይታወቅም፤የሙሴ መቃብር በእስራኤላውያንም (ዘኀልቁ27ቁ12) ሆነ በዲያቢሎስ ሠራዊት ዘንድ አይታወቅም(ይሁዳ ቁጥር9):: የአሮን መቃብር በሖር ተራራ ላይ የተፈጸመ ስለሆነ በአባቶቹ መቃብር ተቀብሮአል ማለት አይቻልም ዘሁቁ 33፥38:: የመቃብያን ደራሲ የአሮጌውን አዳም ባህርይ በልዐል መንግስት እንዳለ አድርጎ በማቅረብ የዘርና ቀለም መድሎን /አፓርታይድን/ አምርራ በተቃወመች ሀገር ውስጥ ይህንን መጻፋቸው ያሳፍራል::

ጎሣ፣ነገድና ዘርን በመንተራስ የሰውን ልጅ ፍቅር የሚበታትነው የጨለማው ልጅ ዲያቢሎስ ብቻ ነው:: የእርሱ እንደ ራሴዎችና ጭፍሮች ደግሞ ይህንኑ ፍቅርና አንድነትን እርስ በርስ ተከባብሮና ተደጋግፎ እንዳይኖሩ የሚሻውን የአጋንንት አለቃ ሀሳብ በማስፈፀም ይተጋሉ:: በየትኛውም ዘመን የተከናወኑ የታሪክ ድርሣናትን ስናገላብጥ ጎሣ፣ዘርንና ቋንቋን መሠረት አድርገው የተነሱ ሁሉ በጠባሳ ታሪክ ይታወሳሉ:: እንደነ ሂትለር፣ሩዋናዳና ስፔን የሌሎችንም ማስታወስ ለትምህርታችን በቂ ነው:: ይህ እንግዲህ የእግዚአብሔርን የፍቅር አጀንዳ የሚቃወም ስለሆነ ነው::

እስከ ላይኛው ግብጽ ሲሸሽ እንደታየ ተደርጎ ተጽፎል። መጽሐፉ ከአይሁድ ምድር የመጣ ቢሆን ኖሮ፤ግብጽ ለእስራኤል ደቡብ ስለሆነች ወደአዜብ (ደቡብ) ምድር ተሰደደ ባለነበር።

ነገር ግን የሀገር ቤት ድርሰት ነውና ነጩ እጣንና የአሳው ሀሞት ሲሸተው ላይኛው ግብፅ ድረስ ተሰደደ ይላል። የ81ዱ ደራሲዎች በማጫጫስ አጋንንት ይባረራል ብለው ሳይሆን፤ እንደጦር የሚፈሩትን ስም (የሱስ ክርስቶስን) ላለመጥራት ለመሸሽ አማራጭ መንገድ ማቅረባቸው ነው። ነገር ግን ይህ አካሄድ የተነቃበት መሆኑን ሊረዱት ይገባል። ይልቁንም ወደዚህ የአብ ስጦታ ወደሆነው የከበረ ስም *የሱስ* (የሕዝቡን ሁሉ ኀጢአት ወደ ሚያስተሰርይ ስም) መመለስ ይሻላልና ወገኖቼ ቢያስቡበት መልካም ነው እላለሁ ማቴ1፥21፣ ሉቃ1፥31፣ ቆላስይስ ምዕ 3፥17 ።

## <u>ሐሰተኛው መሲህ ክቡርና ቅዱስ ፈጣሪም ነው</u>

ስለሐሰተኛው መሲህ ብዙ ነቢያት ቢናገሩም ት/ዳን11፥31ና 12፥11። ጌታችን ግን በግልጥና በስፋት አስተምሮአል። ከእርሱ በሂላም እንደሚመጣ ተናግሮአል ማቴ24። የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ አሁን እንኳ መንፈሱ እንደሚሰራ ሐዋርያው ከአምስት ጊዜ በላይ በመጥቀስ አብራርቶአል 1ዮሐ2ቁ18፣4፥3።። ይህ መንፈስ የክርስቶስ የሆኑትን የሚገድልና የሚያሳድድ ከመሆኑም በላይ የክርስቶስን ስም የሚጠላ ስለሆነ ስሙ በሚከብርበትና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሚገለጥበት ሁሉ ተቃውሞውን ያነሣል። የፍጻሜ ሀሳቡም የክርስቶስን ተከታይ መግደልና ማሳደድ ይህንኑ ገዳይ ሀሳቡንም ማስረጽ ነው።

ዛሬ የሐሰተኛውን መሲህ መንፈስ በስውር የሚቀበሉ አካላት የሱስ የሚለው ስም ሲጠራ ይቀፋቸዋል። የ81ዱ ባለቤትና አሣታሚዎች የክርስቶስ ብቸኛ አዳኝነት ሲጠራ ሲሰሙ አይመቻቸውም። ሐዋርያትንና አገልግሎታቸውን አከብራለሁ እያሉም ክርስቶስ ብቸኛ አዳኝ ነው የሚሉ ሰዎችን ሲቃወሙ፣ሲያንገላቱና ሲገድሉ ከኖሩበት ዓውደ ምሕረት ጎትተው ሲያወርዱ ይታያሉ። የሱስ የሚለው ስም ሲጠራም እሬት እንደጠጣ ሰው ያንገፈግፋቸዋል። በጨለማና



በብርሃን ነጸብራቅ መካከል ያሉ ወጣቶችም ጌታ የሱስ የሚለውን ስም ጠንከር ጠበቅ አድርገው ከጠሩ ጆርባው ይጠና ከነማን ጋር ነው የሚውለው? አንተ ሰው ይህንን ስም ደጋገምከው? ጻድቃን ሰማዕታትን /የሞቱ ሰዎችን/ እረስተሃል ይባላሉ። ይህም ድርጊት በሀገራችን ኢትዮጵያ ባህልና ልማድ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል። አዲስ በታተመው መጽሐፍ መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል 12፥24 "*አስቀድመው ከሞቱ ሰዎች በሐሳዊ መሢህ ሕያዋን ሁነው የተገኙ ሰዎች ፈጽመው ክቡራን እንደሆኑ እወቅ*" ይላል።

የትርጉም ስህተት ነው እንዳንል ጥቃቅን ነገሮችን በመጽሐፉ ላይ በቅንፍ በማድረግ ያብራራሉ ስለዚህ ምንአልባት ይህ ዋነኛ አጀንዳቸው ይሆን? የክርስቶስን ተቃዋሚ መንፈስ መሲህና ፈጣሪ ነው ከሞትም የሚያስነሳ ማንነት አለው በማለት በሐሰተኛው መሲህ አማካኝነትም ሕያው ሆኖ መኖር የሚቻልበትን ትምህርት የሚያስተምረን አዲሱ የኦርቶዶክስ 81ዱ መጽሐፍ ዋና አጀንዳው ምን ይሆን? ፍርዱን ለአንባቢ ልተው እወዳለሁ።

## <u>ለሰው ልጅ ማንበብና መጻፍን ያስተማረ የአጋንንት አለቃ</u>

በጥንታዊው የጋርዮሽ ዘመን ኑባሬ ውስጥ ሰው እርስ በርሱ ለመግባባትና ለልጆቹ ቀሪ አሻራውን ለማስተላለፍ ልዩ የፈጠራ ችሎታውን ተጠቅሟል ይባላል። በታሪክ አጥኚዎች ዘንድም ቀዳሚውን ሥፍራ የያዘው በየዋሻዎች ውስጥ የሚገኘው የደንጋይ ላይ ምስሎቹ ናቸው። ቀስ በቀስ ሂደቱ ወደምስላዊ ፊደላት ተለውጦ ዛሬ ወደሚጠቀምበት ፊደል አደገ ሲሉ በብዙ የጥናት ማስረጃ አስደ ግፈው ያረጋግጣሉ። ስለዚህ የሰው ልጅ እግዚአብሔር በሰጠው ነፃና ብሩህ አእምሮው ያፈለቀውን የእውቀት አሻራ የኦርቶ ደብተሮች የአጋንንት ውለታ ነው ሲሉ በ81ዱ መጽሐፋቸው ላይ ጽፈዋል። ለሰው መልካም ነገርን የማያስበ አጋንንት ሥነ ጽሁፍ እንደቸሩት ተደርጎ መንፈሳዊ በሚመስል ጽሁፍ ውስጥ ባለውለታነታቸው መሰበኩ ጉዳዩን በጥንቃቄ ለሚያጤን አእምሮ ዓላማቸው ምን እንደሆነ ማስተዋል የሚችል ይመስለኛል። "ቤተ ክርስቲያኒቱ" እየተመራች ያለችውም በእነማን እንደሆነ አመላካች ነው። ሰው

በደንጋይ ከዚያም በፓፒረስ ቅጠል በሂላም ከእንስሳት ቆዳና ከእጽዋት በሰራው የወረቀት ውጤቶቹ ሀሳቡን ፣ታሪኩንና የኑሮ ዘዮውን በጽሁፍ ማስፈሩ ፈጠራውን እያሻሻለ ለመምጣቱ በቂ መረጃዎች ናቸው:: ልዑል አምላክም ሕጉን እንዲያከብሩለት በፈለገ ጊዜ በድንጋይ ጽፎ ለሕዝቡ እንደሰጠ በዘጸአት ምዕ 20 ተጽፎአል::

ከዚህ እንደምንረዳው የአምላኩን ትእዛዛት በሚገባ ተረድቶና በየእለቱም እያስታወሰ ለማምለክ ይረዳው ዘንድ መጻፉ አስፈላጊ ነው (ዘዳ9፥10) ይህ ሆኖ እያለ መ/ሄኖክ በመባል የሚጠራው የሀገር ቤቱ የደብተራ ጽሁፍ በምዕ19ቁ15-24 ገጽ1010 ላይ"*የመቶ አጋንንት አዝማች...አራተኛው ስም ፔንሙ ለሰው ልጆች የተሰወረ ጥበብን ሁሉ አስተማራቸው ለሰዎችም በጥቁር ቀለም በወረቀት ላይ መጻፍን አስተማራቸው...ሰው በእንዲህ ያለ ሥራ አልተፈጠረም ነበር በጥቁር ቀለምና በቀይ ቀለም ጽፈው ሃይማኖታቸውን ሊያጸኑ ሰው ለእንዲህ ያለ ሥራ አልተፈጠረም ነበርና..*" ይላል:: የአጋንንት አለቆችን የስም ዝርዝር የሚያትተው ይህ መጽሐፍ ከ40 ያላነሱ የአጋንንት ስሞችንም ይጠራል:: በነገድ ቆጠራው ላይም በሴም ዘር አብርሐም ይስሐቅ ያዕቆብ እያለ፤የይሁዳን ነገድ የዳዊት ልጅ የአብርሐም ልጅ ብሎ የየሱስን ዘር ከአጋንንት ጋር ለማቀላቀል ሞክሮአል:: የአጋንንትን ዘር ከሰው ዘር ጋር በማዋሀድ ተአምረ ማርያም የተሰኘ ው የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መጽሐፍም ተመሣሣይ ታሪክ ይዞአል[194]:: የአጋንንት አለቃን በሃምሳና በመቶ ነገድ እየከፋፈለ በየአለቃቸው የሚቆጥረው የመጽሐፈ ሄኖክ ደራሲ ከዘረዘራቸው አጋንንት ጋር የጠበቀ ቀረቤታ እንዳለው ይጠቁማል:: የ81ዱ መጽሐፍ ትክክለኛና ዋና እንደሆነ በየመድረኩ የምታውጀዋ "ቤተክርስቲያን " ከእግዚአብ ሔር ይልቅ አጋንንት ለሰው ባለውለታዎች መሆናቸውን መስክራ ለች:: ፈጣሪ ከሰው የሸሸገውን ጥበብ በመግለጥ ባለውለታ ሆኖ የቀረበው የአጋንንት አለቃ ስውሩን በሰማይ ያለጥበብ ለሰዎች በመግለጥ ሃይማኖታቸውን አጽንተው እንዲይዙም አድርጓል ተብሎ ቀርቦአል:: ሃይማኖት የሰው አእምሮ ውጤት ነው፤እምነት ደግሞ

[194] .ተአምረ ማርያም፡መቅድም፡1956፤ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡አዲስ አበባ



በፈጣሪ መደገፍ ነው:: ስለዚህ ሃይማኖት ሁልግዜም ቢሆን ልዑልንና ቃሉን የሚቃወም ስለሆነ፤ተጠቃሹ አጋንንት ለሃይማኖት ማጽኛ የሆነውን ጥበብ ገልጠላቸው ከሆነ እነርሱ በርግጥም ልክ ናቸው:: ፊደልንና ሥነ ጽሁፍን በሰማይ ያለውንም ጥበብ ሊገልጥልን የሚችልበት አቅም ግን ለሰይጣን ፈጽሞ የሌለው የተዋረደና ትቢያ መሆኑን ግን መጽሐፍ ያስተምረናል ሕዝ28፥16-19፣ራዕ12፥7-10::

መጽሐፈ ሄኖክ ስለጌጥ ማጌጫ ስለጨረቃ አወጣጥ ስልት ስለ ቅንድብ መኳልና የሰማይ ምስጢራትን ሁሉ አጋንንት ለሰው ልጅ ያስተማሩት ነው ሲል በምዕራፍ2፥19-25 ያትታል:: ከዚህ በመነሳት መ/ሄኖክ አጋንንታዊ መጽሐፍ አይደለም ለማለት እንዴት ይቻላል? የዚህ መጽሐፍ ሕትመት ተሟጋች የነበሩት አለቃ አያሌው በድሮ መጽሐፋቸው ፊደልን የሰጠ በሄኖስ ዘመን የሰላም አምላክ እግዚአብሔር ነው ፊደላቱንም በሰማይ ገበታነት ጥፎና ቀርጦ አስተምሯል[195] ቢሉም ከ25 ዓመት በሂላ ግን የመጽሐፈ ሄኖክ ተሟጋች ሆነው በመቅረብ 81ዱ እንዲታተም አድርገዋል::

## <u>ቅዱስ ሚካኤል ሀሜተኛ መላእክ ነው ተባለ</u>

በቅዱስ መጽሐፋችን ውስጥ በግልጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የዚህን ታላቅ መልአክ ስም የምናገኘው በትንቢተ ዳንኤል ሲሆን ለ3 ጊዜ ያህል ተጠቅሶ እናነባለን:: በሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ይህ መልአክ ትሁት፣ቅን፣ለአምላኩ ታዛዥና ተገዥ መሆኑን እናያለን <u>ለምሳሌ</u> በይሁዳ መልእክት ቁጥር 8-9 "የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያቢያሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ..እግዚአብሔር ይገስጽህ አለው እንጅ የስድብን ቃል /ፍርድ/ ሊናገረው አልደፈረም" ይላል:: ይሁን እንጅ 81ዱ የተሰኘው "የቤተ ክርስቲያናችን" መጽሐፍ መላእክትን ሀሜተኛ ከማድረጉም በላይ፤ሥርየት በሌለበት የኃጢአት መስመር ውስጥ ማስገባቱ በመላእክት ለሚያምኑና ያማልዱናል ለሚሉት ተከታይ ምዕመኖቹ ግራ የሚያጋባና ተራ ልብ ወለድ

[195] .ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ፡የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት፡ 1953፡ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት፡ ገጽ70

ይሆናል:: ምክንያቱም በየወሩ ወገባቸው እስኪላጥ ከመላኩ ምልጃን ለማግኘት ደፋ ቀና የሚሉትን ምዕመናን ራሱ መላኩ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን የሚሳደብ ተሳዳቢ አድርገው ጽፈውለታል:: እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሆነው ሐዲስ ኪዳን በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው ኃጢአቱ አይሠረይም ይለናል ማቴ12፥32፣33 እንዲሁ በማርቆስ ወንጌል ምዕ3ቁ29 በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘለዓለም ኃጢአት እዳ ይሆንበታል እንጂ ለዘለዓለም አይሠረይለትም ሲል ያስጠነቅቃል:: ከዚህ የእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳው እነርሱ የሚተርኩለት የመላእክት አለቃ ሚካኤል አሁን መኖሪያው ከዲያቢሎስ ጋር በሆነ ነበር:: ምክንያቱም ኃጢአትን ሳደረጉ መላእክት እግዚአብሔር ሳይራራ ወደገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ አሳልፎ እንደሠጣቸው መጽሐፍ ይናገራልና 2ጴጥ2፥4::

ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከኀጢአት ጋር የመኖር ባህርይ እንዳለው አድርጎ 81ዱ ማቅረቡ ፤ ከሀሜተኛው መልአክ ጋር አብሮ መኖር የማይችል ባህሪውን እንደሚችል አድርጎ በማሳየት ስንፍና ያለባቸው መላእክት በዙፋን ፊት እንደሚገኙ በሰማይ ኀጢአት እንዳለና ምንም ችግር እንደሌለው በሰዎች አእምሮ በመሳል የኀጢአት ድፍረትን ማለማመድ ዋና ዓላማው ያደረገ ይመስለኛል:: መ/ሄኖክ ምዕ19ቁ1 ስለቅዱስ ሚካኤልም ሆነ ስለባህርየ እግዚአብሔር የተሳሳተ ግንዛቤን ለትውልድ ማስተላለፍ ዋና ዓላማው አድርጎአል:: በሌላ ክፍልም እንዲህ"*በዚያች ቀን ቅዱስ ሚካኤል የመንፈስ ቅዱስ ዕውቀቱ ወደ ኀዘን ይወስደኛል ያበሳጨኛ ልም ብሎ ለቅዱስ ሩፋኤል መለሰለት*" (የ1980ው እትም)::

በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው ሚካኤል በመንፈስ ቅዱስ እውቀት መበሳጨቱ ሀሜተኛ ጓደኛም ማግኘቱን ይተርካል:: የአይጥ ምስክር ድንቢጥ እንዲሉ ጥናታዊ ወረቀት ሰርቼአለሁ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው መጽሐፈ ሄኖክ ትክክለኛ ነውና ሊታተም ይገባዋል:: እያለች የምታስተባብረው የሮም ካቶሊክ ይህንን እንኳ ማጣራት የተሳናት የሃይማኖት ድርጅት መሆኗን ማየት ችለናል:: በነዐዩ



ሱሱንዮስ ዘመን ብዙ ኦርቶዶክሳዊያን በቀን ከ800 በላይ አንገታቸውን ለሰይፍ ስለት የሰጡት የሮም ካቶሊክ ሃይማኖትን ላለመከተል ነበር[196]:: ይህ የታሪክ ጠባሳና የፈሰሰው ደም ባልደረቀባት ምድር፤የዛሬዎቹ የኦርቶዶክስ ሊቃውንት ነን ባዮችና ሲኖዶሱ ከግማሽ በላይ የካቶሊክን አስተምህሮ በክብር ተቀብለው በሕዝቡ ልብ ውስጥ ማስተናገዳቸው ለምን ይሆን ? [197]::

እንደ መጽሐፈ ሄኖክ ገለጣ ሀሜተኛው መልአክ ሚካኤል ሳይሆን ወር በገባ በየ12 ቀኑ "ቤተክርስቲያኒቱ" የምታከብረው የግብጽ ጣዖት ዙሀል ነው:: (በድሮ የድርሣን ሚካኤል መቅድሞች ይህ ታሪክ ተጠቅሶአል በ12ቀን በሚካኤል ስም እንደተተካ) በልዑል አምላክ ፊት የሚቆመው ቅዱሱ መልአክ አይደለም:: ለደብተሮቹ የተገለጠላቸው በየስምና ነገዱ ከምዕራፉ ጅማሬ አንስቶ የሚዘረዝሩት የእነርሱ ወዳጅ የአጋንንት አለቃ መሆኑ ግን አያጠራጥርም:: ለዚህ ነው በየዓመቱ /ሰኔ12ቀን/ በእርድና በጥንቆላ አምልኮት፤በዘፈንና በብዙ የሟርት አሰራሮች የሚከበረው:: እውነተኛው መላክ ሚካኤል መስዋዕትም ሆነ አምልኮ አይሻም አይቀበልምም:: ምስጋናና መስዋዕት ማቅረብ ብንፈልግ እንኳ ለማን ማቅረብ እንዳለብን ያስተምረናል መ/መሳፍን13፥15-19::

## <u>የቅዱስ ሚካኤልና የቅዱስ ገብርኤል የይገባኛል አተካራ</u>

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በነጻነት የመጻፍ ዲሞክራሲ መብታቸውን እየተጠቀሙ ለነፍሳቸው ሳይሰስቱ ጥቂት ገመናዎችን ጽፈው ለሕዝብ በማሳየታቸው፤በየቤቱና በየአዝመራው ሲደገም ከነበረበት የክብር ዙፋኑ እንዲሁም ከተወሸቀበት ከሕፃን አዋቂው ትራስ ሥር እየተመዘዘ መወርወር የጀመረው ድርሣነ ሚካኤልና ድርሣነ ገብርኤል የተሰኙ የደብተሮች መጻሕፍት ከድህነት፣ከረሀብ፣ ከተምች፣ ከወባ፣ ከኩብኩባና ከወረርሽኝ በሽታዎች ይጠብቃሉ ይባል ነበር:: እናም ሰው ሁሉ የቻለ እራሱ ያልሆነለት በወር ኮንትራት ድርሣኑን በየቤቱ የማያስነብብ /የማያስደግም/ አለ ቢባል እርሱ እግዚአብሔር

---

[196] .ያሬድ ግርማ ኀይሌ፡የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ሲነፃፀር፡1999፡አሜይጽሪንተ ማ/ቤት ገጽ56

[197] . ቻርሊስ ሲራይሪ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

የረዳው ብቻ ነው። በተለይም አቅማቸው በመድከም ላይ ያሉ ጡረተኞችና ማኅበረ ቅዱሳን ከብብታቸው ሥር አይጠፋም። ችጋር በድርሣነ ሚካኤል ቢባረር ኑሮ ዓለም ሁሉ የማያውቀው ድርሣን ነበረን። ነገር ግን በተቃራኒው የድህነታችን ማማ በዓለም አንደኛ አድርጎናል። የድርሣኑ የውስጥ ሚስጥር ወር እስከ ወር አባቶቻችን እንዳይሰሩ የሚከለክል ነው። ወባና ኩብኩባ ቢወገዱ ኑሮ ቀን ከሌት ድርሣኑን[198] ታቅፈው የሚያድሩ ያገሬ ገበሬዎች ጤነኛ በሆኑ ነበር።

*__ድርሣነ ሚካኤል ከቁርዓንና ከጥንቆላ ሀሳብ ጋር ይስማማልን__* ?

__ለምሳሌ__:- የጥር ሚካኤልን ድርሣን ስናነብ "*ወይኔጽሩ ራዕዮሙ ወየአኩትዎ ለገባሬ መላእክት አበኩሉ ወአሐዱስ ሊቅ ምስለ ሠራዊቱ ወድቀ ወበእለ ይቤሉ ዲያቢሎስ ወድቀ ሶበአበየ ሰጊደ ለአዳም*" አንዱ አለቃ ግን ከሠራዊቱ ጋር ወደቀ ዲያቢሎስ ለአዳም መስገድን እምቢ ስለአለ ወደቀ ይላል[199]። ቁርዓንም ይህንኑ በሱራህ2:34፣17:61ይህንኑ ይናገራል። መጤው የካቶሊክ ቅጅ "የቤተ ክርስቲያኒቱ" መጽሐፍ የሦስቱ ልጆች መዝሙር በተሰኘው ክፍሉ ውስጥ፤የዘመናት አተካራን ያበርዳል ተብሎ ተስፋ የተጣለበትን አዲስ ሀሳብ ይዟል። በድርሣነ ሚካኤል[200]ታህሳስ 12 ንባብ ላይ እና ድርሣነ ገብርኤል[201] የግንቦት ንባብ ላይ "*ወተለዐለ ነበልባለ እሳት መጠነ አርብዓ ወተስዐቱ በእመት ወአውዓዮሙ ለእለ ያነድዱ እሳተ ወሚካኤል ዘበጦ በበትረ ዚአሁ ለነበልባለእሳት ወአጥፍአ እምላዕለሠለስቱ ደቂቅ ወአልከፎሙ እቶነ እሳት ግሙራ ወረሰዮ ለእቶነእሳት ከመ ማይ ቆሪር በጊዜ ጽባሕ*" __ትርጉም__ የእሳቱ ነበልባል አርባ ዘጠኝ ክንድ ያህል ከፍ ከፍ አለ፤እሳት የሚያነዱትንም አቃጠላቸው ሚካኤልም የእሳቱን ነበልባል በበትሩ መትቶ ከሦስቱ ጎልማሶች ላይ አጥፍቶ አዳናቸው፤የሚነደው እሳት ፈጽሞ ምንም አልነካቸውም የሚነደውን እሳት እንደጧት ውሀ የቀዘቀዘ አድርጎታልና ይላል።

---

198 .ድርሣን:- የተደረሰ፣ድርሰት፣ቅንብር፣ፈጠራ፣የሰው አእምሮ ጭምቅ ውጤት ማለት ነው።

199 .ድርሣነ ሚካኤል: በግእዝና በአማርኛ:1981:ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት ገጽ153

200 . ከዚሁ ከላይ: በገጽ 115

201 . ድርሣነ ገብርኤል: በግእዝና በአማርኛ: 1989: ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት ገጽ 159



3ቱ ወጣቶችን ሚካኤልና ገብርኤል እኔ ነኝ ያዳንኩ በሚል አተካራ "ቤተ ክርስቲያኒቱ" ከወንጌል እውነት ወጥታ በሙት መንፈስ አምልኮ ከተያዘችበት ጊዜ አንስቶ፤ሁለቱን መላእክት ሲያበጣብጥ የኖረ አጀንዳ ነው። የ2ሺህ 81ዱ እትም ግን የሁለቱን የይገባኛል የባለቤትነት ይዞታ በመንጠቅ ገለልተኛ አካል መስሎ በመቅረብ የ3ቱ ልጆች መዝሙር በተሰኘው መጽሐፍ ምዕ1ቁ24 "*__እግዚአብሔር የላከው መላእክም ከአናንያና ከአዛርያ ከሚሳኤል ጋር ወደሚነደው የእሣት ምድጃ ወርዶ በጉድጓድ ያለውን እሳት መታው__*" ይላል። ይህ አቀራረብ የሁለቱን ድርሣናት ሀሳብ ቢቃወምም እግዚአብሔር እንዳዳናቸው ግን አይናገርም።

ይሁን እንጅ ታላቁ መጽሐፍ ትንቢተ ዳንኤል ሁሉንም ድርሣናት ውድቅ ይሆናሉ። ምክንያቱም ሦስቱም ልጆች ከእግዚአብሔር ውጭ አምላክ የለም፤ባያድነንም እንኳ እርሱን እናመልካለን ስላሉ፤ያመኑበት አምላክ አዳናቸው እንጅ መላእክትን በመማጸናቸው ዳኑ አይልም ዳን 3፥17። የአሕዛቡ ንጉሥ እንኳ የሲድራቅ የሚሳቅና አብደናጎም አምላክ ይባረክ እኔም እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና... ሲል ያዳናቸው እግዚአብሔር እንጅ መላእክት እንዳልሆኑ መስክሮአል ዳን3፥29። ከእግዚአብሔር ውጭ አዳኝ የለምና ኢሳ45፥21። ማዳንን ለፍጡር መስጠት ርኩሰት ነው። ደብተሮቹ ግን ከአሕዛቡ ንጉሥ ያነሰ መረዳት ይዘው ያዳናቸውና የሚያድነን ፍጡሩ መላክ ነው ማለታቸው ያሳዝናል ያስለቅሳልም።

መዝሙረኛው ዳዊት በምዕ33ቁ6 መላእክት እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ዙሪያ ይቆማሉ ያድኗቸውማል። ሲል መላእክትን በሚፈሩና በሚያከብሩ ሰዎች ዙሪያ ሳይሆን __እግዚአብሔርን የሚፈሩ__ ሰዎችን ነው። እግዚአብሔርን የሚፈሩና ቃሉን የሚያከብሩ ሰዎች መላእክት በአምላካቸው ትዕዛዝ መሠረት መጥተው እንደሚራዱና እንደ ሚጠብቁ ያሳያል። መላእክትን በመውደድም ሆነ በመማጸን ግን እርዳታና ደህንነት ማግኘት ፈጽሞ አይቻልም። ልዑል አምላክ መላእክትን ለእስራኤል የላከላቸው በእነርሱ ደስ ስላልተሰኘ ነበር።

መላእክት ፍጡራን ስለሆኑ ስንጠራቸው ፈጥነው የሚደር ሰብት ዓለም የላቸውም። ስንጠራቸው በሁሉም ቦታ ይገኛሉ ይሰሙናል ብለን የምናስብ ከሆነ ደግሞ፤ፈጣሪና ፍጡርን መለየት ተስኖናልና ልናስተውል ይገባል። ዮሐንስ አፈወርቅ "ወአኮ ዘፈለሰ ሰበ ተፈነወ ወልድ እመካን ወሰተ መካን፤ከመ መላእክት እስመ ይትነኖሉ አመንኖሙ ሰበ ይትፌነው"[202] ወልድ በተላከ ጊዜ እንደ መላእክት ቦታውን ለቆ የሄደ አይደለም መላእክት ሲላኩ የነበሩበትን ቦታ ለቀው ይሄዳሉ ወደ ተላ ኩበትም ሥፍራ ይደርሳሉ ስላለ መላእክት ውስን ቦታ አላቸው።

## ለፓትርያሪኩ አንድ ሚስት የፈቀደው 81ዱ ሌሎች ጳጳሳትን በመከልከሉ በብዙዎች ዘንድ ቅሬታን አስነስቶአል።

በፍትሐ ነገሥትም ሆነ በአዋልድ መጻሕፍቶች ኤጲስቆጶሳት /ጳጳስ/፣ እንዲሁም የጳጳሳት ሰብሳቢ ፓትርያሪኩ ፣ሚስት ማግባት እንደ ሌለባቸው ሽማግሌዎቻችን ወስነዋል ይላሉ። የልዑል እግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ ባይሆንም። ምንም እንኳ በሐዋርያት ዘመንና ከእነርሱም በኋላ የነበሩት አባቶቻችን እስከ 5ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ኤጲስ ቆጶሳትና ርዕሳነ ኤጲስ ቆጶሳት አንድ ሚስት ያገቡ እንደ ነበር ቤታቸውንም መምራት መቻላቸው በቤታቸው ተፈትኖ መሪ ይሆኑ እንደነበር በታሪክ ድርሣናት እናነባለን (ያልታተመ የቤ/ክ ታሪክ) /Ancient Patrologly/ ይሁን እንጅ በ5ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ ይህንን የሽማግሌዎች ውሳኔ ተቀብላ የኖረችዋ ኦርቶዶክስ "ቤተ ክርስቲያን" አዲሱ መጽሐፌ ብላ ባሳተመችው የ2ሺህ እትም 81ዱ ላይ በ1ኛ ጢሞ ምዕ 3 ቁ1-3 ለፓትርያሪኩ ጋብቻን(አንድ ሚስት) ሲፈቅድ፤ሌሎች ጳጳሳትን መከልከሉ ብዙዎችን ያሳዘነ ጉዳይ ነው። ይህም በየመድረኩ መናፍቃን /በጻድቃን ምልጃ የማያምኑ/ መጽሐፍ ቅዱስን እየቀናነሱ ቃላቶችንም እየለዋወጡ ያሳትማሉ ይባል የነበረው ፉከራ ሁሉ፤

[202] .ድርሣነ ዮሐንስ አፈወርቅ ክፍል 3 ገጽ 155 - 156



ሊቧልት ያሲቧትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል እንዲሉ ራሳቸው ለመለወጥ ዝግጅት ላይ ስለነበሩ ነበር።

መንፈስ እግዚአብሔር ያለባቸውን መጽሐፍት መቀየርና መለወጥ መጨመርና መቀነስ በሰው ዘንድ ብቻ ሳይሆን በቅዱሱ አምላክ ዘንድም የሚያስጠይቅ ነው[203]። የሐዋርያትን መልእክት በግሪኩም ሆነ በግእዙ ላይ ያልተጻፈ ቃል በመከለስ 81ዱ የተሰኘ የሀገር ቤት መጽሐፍ ቅዱስ በማሳተም ጳጳሳትን ማበጣበጥ ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች በወሲድና በአባትነት ክስ እየተመላለሱ ያሉና ጉዳዩ እንዳይወጣብን ሃይማኖታችንም እንዳይሰደብብን በማለት የመማለጃ ክፍያን በመፈጸም ኀጢአትን በመስራት ለምዕመኑ ኀጢአትን የሚያደፋፍሩ አባቶችን ጋብቻቸውን ሕጋዊ አድርገው ነጻ ሰዎች በመሆን ወደ ንስሐ የሚመለሱበት እድል ይፈጠርላቸው ነበር[204]። ለፓትርያሪካችን አንድ ሚስት መፈቀዱን አልቃወምም።ምክንያቱም ቅዱሱ የእግዚአ ብሔር ቃል"ጋብቻ ቅዱስ ነው መኝታውም ንጹህ"ይላልና ዕብ13፥5። ስለ መጨረሻው ዘመን ምልክቶችም በተናገረበት ሀሳቡ ‹‹*መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኛው ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ እምነትን ይክዳሉ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ…እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዝዛሉ እግዚአብ ሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና ከምስጋና ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም*›1ጢሞ4፥1-5 መቃወም አልችልም።ይልቁንም የሰው፣ የሥጋናየአጋንንት ትምህርት የሆነውን አለማግባት ብቃወም የተሻለ

[203] .ኤርምያስ ምዕ23፥36፤39፡40፤ምሳሌ 30፥5-6፤ዘዳ 4፥2፣ራዕ22፥18-19

[204] .አንድ ወዳጄ እኒህ ጳጳስ ከማህበረ ቅዱሳን ጋር ሆነው ወንጌል ብቻ ታስተምራለህ በሚል ክስ አንገላትውት ስለነበር፤በዚህ ብስጭት ከፍርድ ቤት ጋር የተያያዘውን ፋይልና የልጃቸውን ፎቶ፤ቢሻም የክስ ሂደቱን ቻርጅ ኮፒውን አስደግፎ በግል ጋዜጣ ለማውጣት አስቦ ስለነበር ለእኔም ሰጥቶኝ ነበር። ነገር ግን የመጽሐፌ ይዘት ግለሰብ ተኮርና ክሳሽነት እንዳይሆንብኝ ስለፈለግሁ መረጃውን አስደግፎ በዚህ መጽሐፍ ማውጣት አስፈላጊ አልመሰለኝም።

ይሆናል። ብዙ ሰዶማዊያንና ከእንስሳ ጋር የሚገናኙ በየገዳማቶች የፈሉት ይኸው የሰው ሥርዓት ጫና ስለሆነባቸው ነው። እህት መነከሳይያትም ቀላጮች የሆኑት በዚሁ ምክንያት ነው።

## *የነገሥታትን ጉልበት የፈታው 8ኛው ሺህና እንቆቅልሹ*

ሁሉም ኢትዩጵያዊ የ8ኛው ሺ.ህ ታሪክንና የብሄለ ባህታዊያንን የማስፈራሪያ ዛቻ ሳይሰማ ያደገ ይኖራል ተብሎ አይገመትም። በተለይም ወደ ኦርቶዶክስ "ቤተክርስቲያን" ቅጽረ ግቢ ጎራ ያለ ሁሉ ፀጉሩን አስረዝሞ ቢጫ/ወይባ/መጎናጸፊያ ደርቦ፤እንዲያም ሲል ሰንሰለት በወገቡ ታጥቆ ወዩልህና ወየውልሽ የሚል ተናጋሪ ሁሉ አጀንዳው ይህ ነው። በዚህ የፈጠራ ታሪክ ጉልበቱ ያልዛለ በእንቅልፉ ያልቃዥ ይገኛል ማለት እርሱ እግዚአብሔር የረዳው ብቻ ነው። ይህ አስጨናቂው የባህታዊያን ፉከራ፤ከተራው ሕዝብ አልፎ የሀገር መሪዎችን ልብ ያስጨነቀና እንቅልፍ የነሣ ነበር። ለምሳሌ፦ ንጉሥ ዐፄ ናኦድ የ8ኛው ሺ.ህን ስብከት ሰምተው መቼ ይገባል?ብለው ሲጠይቁ መስከረም ሲሏቸው የ8ኛውን ሺ.ህ መግቢያ ላለማየትና ከዘመኑም እህልና ውሃውን ላለመቅመስ ሞትን ተመኝተው ሲጸልዩ መስከረም ሳይብት ነሐሴ 7 ቀን ፀሎታቸው ተሰምቶ እንዳረፉ /እንደ ሞቱ/ ስንክሳር የተሰኘው መጽሐፍ ይተርክልናል[205]።ምንአልባት ደብተሮችም ትምህርታቸው ተቀባይነት እንዲያገኝላቸው በጥላ ወጊ ገድለዋቸው ሲሆን ይችላል የሚል አንዳንድ የታሪክ ፍንጮች አሉ በመረጃ የተደገፈ ሀሳብ ሆኑ መቅረብ ባይችልም። በ14ኛው ክፍለ ዘመን ዐፄ ዘርዓያዕቆብ መጽሐፈ ሚላድ በተሰኘው ድርሰታቸው *‹‹ወካዕበ ስማዕ ኦ ብዕሲ ክርስቲያናዊ ሀለው ኦ እለ ይብሉ እምድኅረ ሰብዐ ምዕት ዓመት ሀሎ ብዙኃ ዘመን ዘኢይትሆለቁ ዓመታት በዝዓለም ዘንተሰ እለ ይብሉ እምድኅረ ሰብዓ ምዕት ዓመት ሀሎ ብዙሃ ዘመን ዘኢይትሆለቁ ዓመታት በዝዓለም ዘንተሰ እለይብሉ ሐሳዊያን›*

[205]. ስንክሣር ዘነሐሴ ሰባት ቀን /የነሐሴ ሰባት ንባብ/ የብራና መጽሐፍ



ክርስቲያን ሰው ሆይ ! ዳግመኛ ይህንን ስማ ከሰባት ሺ.ህ ዓመታት በኋላ በቀመር የሚቆጠር ብዙ ዓመት በዚህ ዓለም አለ የሚሉ አሉ። ይህን የሚሉ ግን ውሸተኛ ናቸው ብለዋል[206]።ይህንን ማለታቸው ደግሞ ሰባተኛው ሺ.ህ አልቆ ስምንተኛው ሲጀምር ዓለም ያልፋል የሚለውን ትምህርት ለማረጋገጥ ነው[207]። ይሁን እንጅ በዚህ ስሌት መሠረት 8ኛውሺ.ህ ካለፈ ከ500 ዓመታት በላይ ሆኗል፡

*የስምንተኛው ሺህ መነሻ ሀሳቦች ምንድን ናቸው?* የመነሻ ሀሳቡ የሠራዕያነ ሕግ ቆጠራ ሲሆን፤የጥቅስ ክፍሉም ት/ሆሴዕ ምዕ 3 ቁ5 ነው።ቃሉም*‹‹ዐሠርተ-ወኃምስተ ጠፋልሀ ብሩር›› የሚል ሲሆን የትርጉም ትንታኔውም ይብል ዘንተ አመ አውፅዖሙ እግዚአብሔር ለእስራኤል እምቅኔያተ ግብፅ አመአሰሩ ወነምሱ ለሠርቀ ወርኀኤሣን አንድም /በ/ ዐሠርቱ ወኃምስቱ ጠፋልሀ ብሩር ይተረጎም አሠርቱ ወኃምስቱ ምዕት ዓመት እምድኅረ ልደተ-ክርስቶስ›*የሚል ነው። አሥራ አምስት ብር ማለቱ እግዚአብሔር እስራኤልን በግብጽ ከመገዛት በሚያዚያ ወር በ15ኛው ቀን እንደ ወጡ የሚያሳስብ ነው አንድም 15 ብር ማለት ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ 1500 ብቻ እንዳለ የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ከክርስቶስ መምጣት በፊት 5500 ሲደመር 1500 ይሆናል 7000። ይህም የስምንተኛው ሺ.ህ መግቢያ ስለሆነ የዓለም ፍጻሜ ይሆናል የሚል የፈጠራ ትርጓሜና ሐተታ ስሌት ነው። በመጽሐፈ አክሲማሮስ ገጽ 148 ዓምድ 2 ላይ ዘፈከሮ ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ /የቆጵሮሱ አጲፋንዮስ በአክሲማሪዮስ/ ላይ በጻፈው ድርሣኑ *‹‹ሰባቱን ዕለታት ሰባት ሺህ ብሎ በማስላት 7ኛው ሺህ ሲያልቅ የዓለም ፍጻሜ ይሆናል››* ብሎአል[208]። በሌላው "የቤ/ክያኒቱ" መጽሐፍ ራዕዩ ሳቤላ በተሰኘ ክፍልም ዘወለተ ሕርቃል ገጽ166-170 ላይ *‹‹7ሺ ዘመን በ9 ፀሐይ*

[206]. በንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ፡ *መጽሐፈ ሚላድ 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 110*

[207] .ስንክሣር ዘነሐሴ 29 ቀን ንባብ/ ዘነሐሴ 29/

[208] Orien 818 British musiam

*ቀመር ሲመደብ የ8 ፀሐይ አንድ ወገን ሆኖ የእያንዳንዱ ድርሻ 778 ሲሆን 9ኛው ለብቻው አንድ ወገን እየሆነ በመሠላት 776 ተደርጎ ሲቀመር የዘመን ስሌቱ 8ኛው ሺህ ይገባል ሰባተኛው ሺህም ፍጻሜን ያገኛል››*[209] ይላል፡፡ ስለዚህ ስምንተኛው ሺህ ሲገባና ሰባተኛው ሺህ ሲያልቅ የዓለም ፍጻሜ ይሆናል ይሉ ነበር፡፡ አንድ ምስኪን በሚባለው "የቤ/ክያኒቱ" መጽሐፍ ገጽ 59 ላይም *8ኛው ሺህ ማለቁን አልቆአል፤ዳሩ ግን ከእንግዲህ ወዲህ ባለው ዘመን ሁሉ የጌታ ምጽዓት ይሆናል፡፡ ፍጻሜው ግን ነገ ወይም ዛሬ ለመሆኑ አይታወቅም "* ይላል፡፡ የአሁን ዘመን "የቤተ ክርስቲያኒቱ" ምሁራን ነን ባዬች ደግሞ 8ኛው ሺህ ዘመን ላይ ዓለም አላልፍ ስትላቸውና ድሮ እንደ ሊቃውንት ይቆጠሩበት የነበረው የፈጠራ ትምህርት ከንቱ ሲሆን 7ኛው ሺህ አልቆአል፡፡ነገር ግን የ8ኛው ሺህ ፍጻሜ ነገ ወይም ዛሬ መሆኑ ስለማይታወቅ ሁል ጊዜ በመጠባበቅ መኖር አለብን ይላሉ፡፡

የጌታ ባሪያና ሐዋርያ የነበረው ጳውሎስ ስለጌታ የፍርድ ቀን ቀጠሮ የተዛባ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች እንዲሁም በዚህ የስሌት ቀመር አእምሮአቸው የተያዙትን ክርስቲያኖች ሲወቅስ እንዲህ ይላል ‹‹..የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ በአእምሮአችሁ እንዳትናወጡ እንዳ ትደነግጡም እንለምናችኋለን፡፡ ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፤አይደርስምና እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እስኪ....››2ተሰሎ2፥2-12፡፡ ስለዚህ እራስን በመንፈስ በመቀደስና እውነትንም በማመን ለመዳን በትጋት መኖር ጥሩ ነው፡፡ የጌታ መቅደስ ሰው ያልሰራው ነው፡፡ እግዚአብሔርንና ልጁን የሱስ ክርስቶስን በማወቅ መትጋት እንጅ በከንቱ የጊዜ ቆጠራ ስሌት ጊዜን በማበላሸት የምጽአትን ቀን በመጠባበቅ ማሰላሰል አስፈላጊ አይደለም፡፡ የጌታ መምጣት በዚያው

[209] Orien 818 British musiam



ትውልድ መካከልም ሆኖአል ማቴ24፥34፡፡ ከዚህ ያለፈ በከንቱ የቁጥር ስሌት አባዜ ተይዘው ወንጌልንና እውነትን ከማስተማር የወደቁ የኦርቶዶክስም ሆኑ ሌሎች ሊቃውንት ነን ባዮች በከንቱ እየደከሙ ስለሆነ ወንጌልን ቢሰብኩ የተሻለ ነው፡፡ በዚህ የጌታን መምጣት ያፋጥናሉና፡፡ ደብተሮች ድሮ ድሮ አዋቂ ምሁር ለመባል ዛሬ አንገት ያስደፋቸውን ከንቱ ቀመር ሲደርቱ ይውሉ ነበር፡፡ ዛሬ በውርደት ከተቀበረበት አንስተው በዚህ ትውልድ ላይም ሊቀልዱ ይሞክራሉ፡፡ ይህ ዘመን ግን መረጃንም ሆነ እውነትን ሳይድበሰበስ አጥርቶ መያዝ የሚወድ ትውልድ መሆኑን ግን ረስተውታል፡፡

ደብተሮቹ ከቅዱስ መጽሐፍ /66ቱ/ ጋር አቻ አድርገው ባሳተሙት አሳፋሪ የተረት መጽሐፍ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል *‹‹በዚህ ዓለም የሚኖሩ ሰዎችን እግዚአብሔር ምን ያህል ታገሳቸው ነገር ግን ይህ ዓለም ስምንት ሺህ ይኑር ብሎ ስለወሰነው ነው እንጅ ለእነርሱ ብሎ አይደለም አለኝ ››መ/ዕዝራ ሱቱኤል ምዕ6፥ቁ5፡፡* በመሠረቱ ይህ ሀረግ የእግዚአብሔርን ትዕግስት የሚያሳይ ቢመስልም የሰውን ኃጢአት እያየ የሚታገስ ሳይሆን ያስቀመጠውን የ8ኛ ሺህ ቁጥር ገደብ የሚጠብቅ መሆኑን ብቻ የሚናገር ነው፡፡ "ቤተ ክርስቲያኒቱ" መጽሐፌ ነው የምትለው የአክሲማሮስ መጽሐፍ፤ሰባተኛው ሺህ ሲያልቅ ዓለም ያልፋል ሲለን 81ዱ ደግሞ 8ኛው ሺህ እስኪያልቅ ድረስ ይህች ዓለም እንደምትቆይ ይናገራል፡፡

ገለልተኛ ነኝ የአንድ ሃይማኖት ድርጅት አጀንዳን አላስፈጽምም የሚለው የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርም በዚህ ከንቱ ተረት ልቡ የተረታ ድርጅት መሆኑን *በሚሊኒየሙ ልዩ እትም ቁጥር 3 ላይ ባሳተመው ቃሉ ይናገር መጽሔት መመልከት እንችላለን ‹‹ይህች ዓለም ከተፈጠረች 7500 ዓመት ሆኖአል* ይላል፡፡ አዳም ወደ ምድር ከመጣበት (ከገነት ከተሰደደበት) ተብሎ ሊቆጠር ይችል ይሆናል እንጅ ይህች ዓለም ከተፈጠረች ማለት ግን ደብተሮች ሲቀልዱ የኖሩበትና ለረጅም ዘመን በሀፍረት አንገታቸውን የደፉበትን

ትምህርት ማራመዱ ያለፈውን የህፍረት ታሪክ መድገም ይሆናል፡፡ የ8ኛውን ሺህ ከንቱ ትምህርት ለማራመድ መሞከር ያሳፍራልና ማኅበሩ ቢያስብበት መልካም ነው[210]፡፡ የሰማይና ምድር ተፈጥሮን ሁኔታ ሙሴ አልጻፈም፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ከሰው ልጆች ደህንነት አንጻር ብቻ በንድፍ የሚጠቁም ስለመሲሁም አመጣጥ የሚያሳይ እንጅ የፍጥረትን የምርምር ሂደት እንድንራቀቅ ከንቱና የተፈጥሮ ታሪክ ስሌት እንድናጠና አያበረታታንም ቲቶ3፥9-11፡፡ የዘፍጥረት መጽሐፍ የፍጥረትን የጊዜ ሁነት በትክክል የሚጠቁም ነው ለማለት ብዙ አያስደፍርም፡፡ አቅጣጫ ግን ያሳያል መዝ90፥4፤ 2ጴጥ3፥5-8፡፡

ታቦተ ጽዮን ኢትዮጵያ አለመግባቷ ተበሠረ

የታቦተ ጽዮን ታሪክ ከእስራኤል ምድር ከጠፋችበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባች ከአፈታሪክ አልፎ የመጻሕፍቶቻችን ማስዋቢያ ርዕስ፤የመሪዎቻችን የኩራት ንግግር[211]፤መሆኗ ይታወሳል፡፡ ከዚህም አልፎ ታላላቅ የታሪክና የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኝ የውጭ ሀገር ምሁራንን ሳይቀር ማርኮአል፡፡ ከእነዚህ መካከልም ሮበርት ኮርኑክ፣ ግራሀም ሀንኮክ በቅርቡ ዘመን ታሪካችን ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ጭብጥ ያለው የታሪክ መረጃን በማጠቃለያ ጽሁፎቻቸው ለመደምደም ባይታደሉም ማለት ነው፡፡

[210] .የኢ/መ/ቅ/ማሕበር፡ ቃሉ ይናገር መጽሔት ልዩ እትም 2000 ቁጥር 3 ርዕሰአንቀጽና ገጽ10

[211] .ሮበርት ኮርኑክ፡(Robert Cornuke:Relic Quest:2005)፡ከሲናእስከአክሱም፡1999፡ሣህሉ·ጥላሁንንግድ፡ማ/ቤት





የቃል ኪዳኑ ታቦት እንዳለ የሚነገርበት የአክሱም ማርያም ገዳም /ሰሜን ኢትዮጵያ/

ግርሀም ሀንኮክ የተሰኙት ሰው"The sign and the seal" በተሰኘው መጻሕፋቸው፤ሌዋውያን በንጉሥ ምናሴ ዘመን ከኢየሩሳሌም ወደ ግብጽ ኤለፋንታይን ደሴት በማሸሽ ለሁለት መቶ ዓመታት አቆዩአት በሂላም ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት በጣና ደሴት ለስምንት መቶ ዓመታት ተቀመጠች፤ከዚያም በዮዲት ጉዲት ዘመን ወደ ዝዋይ ሀይቅ መሀል ሸዋ አካባቢ አሸሽተው በመውሰድ ለሰባ ሁለት ዓመታት ያህል ተቀመጠች፤በመጨረሻም ሀገር ሰላም ሲሆን ወደ አክሱም በመውሰድ እስከ ዛሬ ድረስ በዛው አለች ይባላል የሚል የታሪክ ሰንሰለትን በመጽሐፋቸው ለማስነበብ ሞክረዋል[212]፡፡ በአፈታሪክ እንደሚነገረው የነገሥታቶቻችን የዕለት ውሎ የሚዘገብበት ክብረ ነገሥት መጽሐፍ በአንቀፅ 21 እንደጠቀሰው፤ንግሥተ ሳባ ንጉሥ ሰሎሞንን ለማየት ሄዳ ፀንሣ ከመጣች በሂላ፤ልጇ ቀዳማዊ ሚኒሊክ አባቱን ሊጠይቅ ሄዶ ከአባቱ ጋር በመመካከርም ታቦተ ፅዮንን ይዞ መጣ፤ለእስራኤላዊያን ግን አስመስሎ በመቅረጥ /forged/ የምስክሩን ጽላት ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶአል ይለናል[213]፡፡ በአንዳንድ መጻሕፍቶችና አፈታሪኮች ደግሞ ሰርቆ አመጣት ስለሚል ይህንኑ የስርቆት ቃል ለመሸሽ ሁለት ታቦት ነበር፣ታቦተ ሚካኤልና ማርያም /ጽዮን/ አባቱ ሰሎሞንም ታቦተ ሚካኤልን እንዲወስድ

[212] .ግራሀምሀንኮክ ታቦተጽዮንን ፍለጋ/ ትርጉም በጌታቸው ኀይሌ ገጽ 244-246፤ Graham Hancock:The sign and the seal:1997:Crown Pub.Inc.NewYork:Page191&513

[213] .ስርግው ገላው፡ክብረ ነገሥት፡1994፡የኢ/ቋ/ጥናትና ምርምር አ/አ፡ንግድ ማ/ቤት፡ገጽ12፣39



የቃል ኪዳኑ ታቦት እንዳለ የሚነገርበት የአክሱም ማርያም ገዳም /ሰሜን ኢትዮጵያ/

ቢያዝዘውም ልጁ ግን ታቦተ ሚካኤልን ትቶ ጽዮንን አመጣ ለጽዮን ማርያም ልዩ ፍቅር ነበረውና ይላሉ። በመሠረቱ ታቦተ ሚካኤልና ታቦተ ማርያም የሚባል ነገር ፈጽሞ አልነበረም አይታወቅምም። እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ፅላት የኪዳኑ ታቦት በመባል ብቻ ይጠራ ነበር። /ዘጸ24፥12፤25፥16-21/ ይህም በእስራኤል የታሪክ መዛግብት ዘንድ በግልጥ ይገኛል። ታቦተ ጽዬን የሚለው መጠሪያ የተገኘው ከንጉሥ ዳዊት ዘመን በኋላ ነው። ይህም ማለት ከሙሴ እስከ እያሱ ዘመን ከዚያም በአስራ አራቱ መሳፍንትና በንጉሥ ሳዖል ዘመን ታቦተ ጽዬን የሚል መጠሪያ ፈጽሞ የለም ነበር 2ሳሙ5፥7።

ስለዚህ ጽዬን የቦታ ስም እንጅ የኪዳኑ ታቦት መጠሪያ አይደለም። እንዲህ ያለው መጠሪያ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው። ታቦተ ጽዬን በንጉሥ ሰሎሞን ጊዜ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ መጣች ቢሉንም የ፪ሺው መጽሐፍ 81ዱ ግን፤በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመነ ንግሥና ጊዜ በእስራኤል ምድር እንደነበረች ይተርክልናል እንዲህ ሲል ‹‹ታቦቱ ጽዬንን በጫንቃችሁ መሸከም አይገባችሁም አሁንም ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እምልኩት… በየነገዳችሁ ተዘጋጁ የሌዊ ልጆች በወንድሞቻችሁ በእስራኤል ፊት እግዚአብሔር በሚመሰገን ቤት በቤተ መቅደሱ በየቦታችሁ በየሹመታችሁ ቁሙ በዓልንም አድርጉ›› *መ/ዕዝራ ሱቱኤል 1፥3-6* ይላል። ይህ የ81ዱ ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል 2ዜና ምዕ 35 ቁ 3 ።



የመጽሐፍ ቅዱሱ የኪዳን ታቦት በጉዞ ላይ (ዘጸዓም25ቁ1-22ና ኢያሱ3፡6)





የሀገር ቤቱ ታቦት ከጀርባው ሲታይ ያለው ገጽታ። ይህ ታቦት ርዝመቱ 52ሳ.ሜ ቁመቱ 65ሳ.ሜ ሲሆን ውፍረቱ ደግሞ 4ሣ.ሜ ያህል ነው። የተሰራውም ከዋንዛ እንጨት ነው። በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ እንጨቶች ከዝግባና ከጥድ ይሠራል። የወርድና የርዝመቱ ሁኔታም በልዩ ልዩ ቦታዎች ይለያያል።



የየሀገር ቤቱ ታቦት ፊት ለፊት ገጽታ፤ከዋንዛ እንጨት የተሰራ ሲሆን የታቦቱ ስም በወረቀት ተጋርዶ የተነሣ ነው። ምክንያቱም በቦታው ላሉ ሰዎች ደህንነት ሲባል ብቻ የተጋረደ ነው።

*ከነብዩ ኤርምያስ የተሰወረችው የታቦተ ጽዩን እውነታ፡-እንደ ክብረ ነገሥት ገለጣ ለቀዳማዊ ሚኒሊክ ሲባል ሰሎሞን አስመስሎ ሰርቶ ባስቀመጠሳቸው የሐሰት ታቦት፤ነብያት በመሳሳታቸው እውነተኛዋ ታቦተ ፅዩን ወደ ኢትዩጵያ መጥታ ባለችበት ኹኔታ ነብዩ ኤርምያስ ከፀሐይና ከምድር ጋር ይህንኑ የሐሰት ታቦት* /forged/ *አደራ*

ቢያዝዘውም ልጁ ግን ታቦተ ሚካኤልን ትቶ ጽዮንን አመጣ ለጽዮን ማርያም ልዩ ፍቅር ነበረውና ይላሉ። በመሠረቱ ታቦተ ሚካኤልና ታቦተ ማርያም የሚባል ነገር ፈጽሞ አልነበረም አይታወቅምም። እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ፅላት የኪዳኑ ታቦት በመባል ብቻ ይጠራ ነበር። /ዘጸ24፥12፤25፥16-21/ ይህም በእስራኤል የታሪክ መዛግብት ዘንድ በግልጥ ይገኛል። ታቦተ ጽዮን የሚለው መጠሪያ የተገኘው ከንጉሥ ዳዊት ዘመን በኋላ ነው። ይህም ማለት ከሙሴ እስከ እያሱ ዘመን ከዚያም በአስራ አራቱ መሳፍንትና በንጉሥ ሳዖል ዘመን ታቦተ ጽዮን የሚል መጠሪያ ፈጽሞ የለም ነበር 2ሳሙ5፥7።

ስለዚህ ጽዮን የቦታ ስም እንጂ የኪዳኑ ታቦት መጠሪያ አይደለም። እንዲህ ያለው መጠሪያ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው። ታቦተ ጽዮን በንጉሥ ሰሎሞን ጊዜ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ መጣች ቢሉንም የ፹፩ሺው መጽሐፍ 81ዱ ግን፤በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመነ ንግሥና ጊዜ በእስራኤል ምድር እንደነበረች ይተርክልናል እንዲህ ሲል ‹‹ታቦተ-ጽዮንን በጫንቃችሁ መሸከም አይገባችሁም አሁንም ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን አምልኩት... በየነገዳችሁ ተዘጋጁ የሌዊ ልጆች በወንድሞቻችሁ በእስራኤል ፊት እግዚአብሔር በሚመሰገን ቤት በቤተ መቅደሱ በየቦታችሁ በየሹመታችሁ ቁሙ በዓልንም አድርጉ›› *መ/ዕዝራ ሱቱኤል 1፥3-6* ይላል። ይህ የ81ዱ ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል 2ዜና ምዕ 35 ቁ 3 ።



የመጽሐፍ ቅዱሱ የኪዳን ታቦት በጉዞ ላይ (ዘጸግም25፥1-22ና ኢያሱ3፥6)





የሀገር ቤቱ ታቦት ከጀርባው ሲታይ ያለው ገጽታ። ይህ ታቦት ርዝመቱ 52ሳ.ሜ ቁመቱ 65ሳ.ሜ ሲሆን ውፍረቱ ደግሞ 4ሣ.ሜ ያህል ነው። የተሰራውም ከዋንዛ እንጨት ነው። በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ እንጨቶች ከዝግባና ከጥድ ይሠራል። የወርድና የርዝመቱ ሁኔታም በልዩ ልዩ ቦታዎች ይለያያል።



የየሀገር ቤቱ ታቦት ፊት ለፊት ገጽታ፤ከዋንዛ እንጨት የተሰራ ሲሆን የታቦቱ ስም በወረቀት ተጋርዶ የተነሣ ነው። ምክንያቱም በቦታው ላሉ ሰዎች ደህንነት ሲባል ብቻ የተጋረደ ነው።

*ከነብዩ ኤርምያስ የተሰወረችው የታቦተ ጽዮን እውነታ፦እንደ ክብረ ነገሥት ገለጣ ለቀዳማዊ ሚኒሊክ ሲባል ሰሎሞን አስመስሎ ሰርቶ ባስቀመጠላቸው የሐሰት ታቦት፤ነብያት በመሳሳታቸው እውነተኛዋ ታቦተ ፅዩን ወደ ኢትዩጵያ መጥታ ባለችበት ኹኔታ ነብዩ ኤርምያስ ከፀሐይና ከምድር ጋር ይህንኑ የሐሰት ታቦት /forged/ አደራ*

ለማስቀመጥ ብዙ እንደደከመ ተረፈ ኤርምያስ የተሰኘው መጽሐፍ ይተርክልናል። በኦርቶዶክሳዊያን ደብተሮች ዘንድ የታሪካችንን አሻራ የያዘ ነው በሚሉት ክብረ ነገሥትታቦቱ ኢትዩጵያ አለ ሲሉን 81ዱ ደግሞ ሁሉንም የቤተ መቅደስ ንብረት ኤርምያስና ባሮክ ለምድር አደራ ብለው በሰጧት ጊዜ ምድር ከእጃቸው ተቀብላ ውጣዋለች ይለናል ተ/ኤር ምዕ8 ቁ13። በሌላ ክፍሉ ደግሞ ታቦቱንና ሁሉንም የቤተ መቅደስ ዕቃ /ንዋየ ቅዱሳት/ ለፀሐይ አደራ ሰጧት ተ/ኤርምዕ8ቁ18-19 በማለት 81ዱ እራሱን በራሱ ይቃወማል።

ምንም እንኳ በቅዱስ ቃሉ ሲመዘን ሁለቱም ውሸትና የሐሰት ድርሣናት መሆናቸው ቢታወቅም። የክብረ ነገሥት ታሪክ የሚያወሳው በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን እንደመጣች ሲሆን ንጉሡ የነበረበት ዘመን አባቱ ዳዊት በ971 ዓ.ዓ. አነገሠው። በ932 ዓ.ዓ ለ40ዓ.ም ከነገሠ በሂላ ግዛቱ ለሁለት ተከፈለች። ሲሞት አካባቢ እንኳ ቀዳማዊ ሚኒሊክ ታቦቱን አመጣው ብንል /በ932ዓ.ዓ./ ኤርምያስ ለምድርም ሆነ ለፀሐይ አደራ ከሰጠበት ጊዜ ጋር ፍጹም ሩቅ ነው። ሰሎሞን ከሞተ ከ345 ዓመት ቢሂላ ይሆናል። ነብዩ ኤርምያስ የነበረበት ዘመን ደግሞ በንጉሥ ኢዮስያስ/King Josiah/ በ620ዓ.ዓ. ነው። ኢየሩሳሌም በባቢሎናዊያን የፈረሰችውና ቤተ መቅደሱ የተቃጠለውና ታቦቱ የጠፋው ደግሞ በ587 ዓ.ዓ. ነው[214]።

ንጉሥ ኢዮስያስ ሀገራዊ ተሀድሶን ያመጣበትና የቃል ኪዳኑ ታቦት ከሰው ትከሻ ወደ ቤተ መቅደሱ እንዲገባ፤የታወጀው የሕጉ መጽሐፍ በአደባባይ ተነቦ ሕዝቡ ንስሐ የገባው ከክ.ል.በፊት በ621 ዓ.ዓ ነው። ይህም ነብይ ኤርምያስ ሳይወለድ ከ9ና 10ዓመት አስቀድሞ ሲሆን፤ ንጉሥ ሰሎሞን ከሞተ ከ311 ዓመት በፊት ማለት ነው። ንጉሥ ኢዩስያስ በእግዚአብሔር ዘንድ ከወንድሙ ከምናሴ ቢሂላ የነገሠ

[214].13th year of King Josiah, in the year 627 BC, and was active in this capacity from this time on to the destruction of Jerusalem, 586 BC, under kings Josiah, Jehoahaz, Jehoiakim, Jehoiachin, and Zedekiah. ( ISBE BIBLE DICTIONARY)



ተወዳጅና እንደ አባቶቹ እንደነ ዳዊት በአምላኩ ፊት የተመሰገነ ነበር 2ነገሥት 22፥2። እንደ 81ዱ አባባል የቤተ መቅደሱ ንዋየ ቅዱሳት /ቁሳቁስ/ ለምድርና ለፀሐይ ተሰጥቶአል ቢልም፤ቅዱሱ መጽሐፍ ግን ቤተ መቅደሱ ተቃጥሎአል ይለናል በ2ኛ ነገስት 25፥9። ንዋየ ቅዱሳቱም በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር ተማርኮ በጣዖት ቤት ተቀምጦአል 2ዜና36፥7 ይለናል። በምርኮ ዘመን ጊዜ ንጉሡ በልደት በዓሉ ለመጠጫነት ለመጠቀም በመዛግብቱ ውስጥ ከንዋየ ቅዱሳቱ መካከል አንዱ የሆነውን ፅዋ ሲጠጣበት፤በራዕይ እያየ እጅ መጥታ ‹‹ማኔት ቴቄል ፋሬስ›› የሚል ጽሁፍ በመጻፏ እንደተጨነቀና ፍችውንም ዳንኤል እንደተረጎመለት መጽሐፍ ይናገራል ዳን 6። ከሰባ ዓመት በሂላም በንጉሥ ቂሮስ ዘመን ቤተ መቅደሱ እንዲሰራ የተማረኩና በጣዖት ቤት ውስጥ የነበሩ ሁሉም ንዋየ ቅዱሳት እንዲመለሱ ተወስኖ ዘሩባቤል ተረክቦታል መ/ዕዝራ1፥7-11።

ስለዚህ ተረፈ ኤርምያስ /81ዱ/ ተቀበረም አለ ፀሐይ ሰወረችው በምርኮ ባቢሎን ነበር። ቤተ-መቅደሱም በንጉሡ ወታደሮች ተቃጥሎአል። ስለዚህ የቃል ኪዳኑ ታቦት በነብዩ ኤርምያስ ዘመን ከኖረች በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን ወደ ኢትዬጵያ መጥታ ነበር ማለት ፈጽሞ አይቻልም። ምክንያቱም ነብዩ ኤርምያስ የእግዚአብሔር ትክክለኛ ነብይ አይደለም ካላልን በቀር፤አስመስለው ለሰሩት ታቦት ትንቢት አይናገርም ኤር3፥15ና 31፥31። ለምድርና ለፀሐይም የሚሰጠው አደራ አይኖርም። እንደ ክብረ ነገሥት ትረካ የተጭበረበረ ታቦት መለየት ያቃተው ነብይም ነብይ ነው ልንለው አንችልም። ምን አልባት ሌላ ኢትዮጵያዊ ነብይ ኤርምያስ ካልሆነ በቀር። "የቤተ-ክርስቲያኒቱ" የመጽሐፍት ወሳኝ አካላት የሆነው የሊቃውንት ጉባኤም ሆነ ሲኖዶሱ 81ዱ የተሰኘውን መጽሐፍ ሲያሳትም የሀገሪቱንና "የቤተ-ክርስቲያኒቱን" ታሪክ የያዘው ክቡር መጽሐፋችን የሚሉትን *ክብረ ነገሥትን* ወይም መጽሐፍ ቅዱስን ከሁለት አንዳቸውን ስህተት ነው ብለው ማስተካከያ መስጠት ነበረባቸው። መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ9፥21-23 የተሰኘው ሌላው የ81ዱ ክፍል

ደግሞ *‹‹ቤተ መቅደሳችን እንደፈረሰ አታይምን ግናይቱ እንደጠፋች ምስጋናችን እንደቀረ ዘመራ ዘውዳችን እንደወደቀ ተድላ ደስታችን እንደጠፋ የሕጋችን ማደሪያ ታቦተ ጽዮን እንደ ተማረከች...››*ሲል ታቦተ ጽዩን ተማርካ ባቢሎን ወረደች ይላል፡፡ ይህም እኛን ኢትዩጵያዊያንን የሚቃወም ከመሆኑም ባሻገር፤ለረጅም ዓመታት የኮራንበትንና የተመካንበትን ታሪክ የሚያፈራርስ ነው፡፡ ክብረ ነገሥትንም የሚቃወም ታሪክ ነው፡፡ በርግጥ ክብረ ነገሥት የተሰኘው መጽሐፍ በኢትዮጵያዊያን የታሪክ ምሁራንም ሆነ በሌሎቹ ዘንድ ተቀባይነትና ተአማኒነት የሌለው ድርሰት መሆኑ ቢታወቅም፤"በቤተክርስቲያኒቱ" ዘንድ ግን ይህን ያህል የሰፋ ልዩነት ይኖራል ተብሎ አይገመትም፡፡ 81ዱ የራሱ ክፍል ከሆነው ተረፈ ኤርምያስ ከመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ጋር ከመፋለሱም በተጨማሪ የታሪካችንን አሻራ ይዞአል ከሚሉት ክብረ ነገሥት ጋርም ፍጹም የሚቃረንን ታሪክ ይዞ ይገኛል፡፡

***ጥቅል ሀሳቡ-*** የነብዩን ቃል ፀሐይና ጨረቃ እንዳልሰሙት ምድርና የቤተ መቅደሱም በር እንዳልተቀበሉት ተደርጎ የቀረበው ሀሳብ ኢ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ ግዑዛን ፍጥረታት ለነብያት ቃል ይታዘዛሉ፡፡ ሙሴ ባህረ ኤርትራን መክፈሉ(ዘጸ14፥21-31)፤ኤልያስ ሰማይ ዝናብ እንዳይሰጥ መዝጋቱ(1ነገ17፥1)፤ኢያሱ ቀኑ እንዳይመሽ ፀሐይን መከልከሉን (ኢያሱ10፥12) መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ በኢዮስያስ ጊዜ ታቦቱን ከሸክም እንዲያወርዱትና ወደ ቤተ መቅደሱ እንዲያስገቡት ታዟል፡፡ መጽሐፈዕዝራካልዕ ምዕ1፥3-5ና 2ዜና35፥1፡፡ ይህም ወደ ሀገራችን አለመምጣቱንና የግራሃም ሀንኮክን መላምታዊ ታሪክና የክብረ ነገሥትን ልብ ወለዳዊ ድርሰት ውድቅ የሚያደርግ መረጃ ነው፡፡ ግራሀም ሀንኮክ ረጅም ርቀት ተጉዘው ይህንን ታሪክ ሲያጠኑ፤በእጃቸው የያዙትን ታላቁን መጽሐፍ ግን አላስተዋሉትም፡፡ ከዚህ የተነሣ ብዙ መላምቶችን አስቀምጠዋል፡፡ በምናሴ ዘመን ታቦቱ ወደ ግብጽ ኤለፋንታይን ደሴት ወጣ ብለዋል ይሁን እንጅ ምናሴ ለ55 ዓመት ነገሠ (2ዜና ምዕ33፥1) ልጁ አሞፅ ከምናሴ



በሂላ ነገሠ (ምዕ33፥21) የገዛ ባሪያዎቹ በቤተ መንግስት ከገደሉት በሂላ ልጁ ኢዮስያስ በ8ዓመቱ ነገሠ፤ከዚያም በ18ዓመቱ የሕጉ ቃል ሲነበብ ይህንን የተሀድሶ አጀንዳ አነሳ (ምዕ31፥1-ምዕ34፥8)፡፡ ስለዚህ የግራሀም ሀንኮክ ማለምት መጽሐፍ ቅዱስን ይቃወማልና ተራ መላምት ይሆንባቸዋል፡፡ ታቦተ ጽዩን ብለን የምንጠራው የእስራኤል ታቦት ወደ ሀገራችን ካለመግባቱም በላይ፤የሐዲስ ኪዳን አማኞች ስለሆን በአሮጌው ኪዳን ዕብ8፥5-13፣2ቆ3፥2-17 የምንደገፍበት ምንም ነገር የለም፡፡ የምንኮራበት የፈጠራ ታሪካችንም በዚሁ በ81ዱ መጽሐፍ ውድቅ ስለሆነልን፤ወደ አዲሱ የመንፈስና የእውነት ኪዳን ዘወር እንል ዘንድ ጥሪዬን በጌታ ፍቅር አስተላልፋሁ፡፡

## *<u>የቆጡን አወርድ ብላ ... ማኅበረ ቅዱሳንና ቁርዓን</u>*

ገና በፊት ድሮድሮ ሁለቱን ብቻ ነው የምናውቀው ከሁለቱ ውጭ በሀገራችን ምንም አናውቅም፡፡ የሚሉ መፈክሮች "በየቤተክርስቲያኑ" ቅጥር ግቢ በምንሰማበት ጊዜ በመስቀልና በጨረቃ ኮከብ ማህተሞች የስምምነት ፊርማዎች የፖሊስ ጣቢያዎችንና የቀበሌ ጽ/ቤቶችን መዝገብ ሲያጣብቡ በየመነኮሳቱ እጅ ጨረቃና መስቀል በአንድ ላይ ተጣምረው ሲታተሙ[215]፤ይህ ነገር ልክ አይደለም ያሉ ብዙ ነበሩ፡፡ ጨረቃዎቹ መጻሕፉ በሚያዘው መሠረት እንደመጽሐፉ ሥርዓት[216] በጅማ፣በድሬዳዋና፣ በመተከል ትንሽ ትንሽ ፈጽመዋል፡፡ ይህ ታሪክ ዛሬ በየአደባባዩ በወረቀት፣በብጥስጣሽ ጨርቅና በትሸርት "*<u>አንድ ሃይማኖት፤አንዲት ጥምቀት፤አስር ጊዜ ከመሰቃለቅ አንድ ጊዜ መጠመቅ</u>*" የሚባሉ መፈክሮች ሳይነገቡ ማለት ነው፡፡ እንደ ክርስትና ሀሳብ ይህም አካሄድ መልካምና ትክክል አይደለም:: ምክንያቱም የክርስትና መሠረቱ ፍቅር ስለሆነ በፍቅር እንጅ የቀረርቶና የሽለላ

---

[215] .አባኪዳነ ማርያም ገ/ሕይወት፡ሃይማኖት አይለያየንም፡1968፡ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት

[216].ሱረቱል አል አሳዕ8፡12-13፣ሱረቱል ገጽ550-553፣እምነገክር7.966፣ሳሂህ ሙስሊም3ገጽ 963-960፣ሚስካት27.454፣ክርስቲያኖች ከነቁማቸው እንዲቀበሩ የታዘዘው በሳሂህ ሙስሊ ገጽ

ሄደት የለውምና። በሰይፍና በጦር የሚስፋፋው ክርስትና ሳይሆን ሌላ ነው። እንዲህ መሰሉን ሃይማኖት ለማወቅ የሚፈልግ የ6ኛው ክፍለ ዘመንን ታሪክ ማጥናት ይበቃዋል። ክርስቶስ ክርስትናን የመሠረተው በፍጹም ፍቅር ነው። ስለ ሃይማኖት ሰውን መግደል ግን የተለመደ ነው።ስለእምነት መሞትንና ጸንቶ መኖርን ግን ከጌታና ከአባቶቻችን ሕይወት ተምረናል። የትኛውም ሃይማኖት ደግሞ ከማንም ሃይማኖት አይበልጥም አያንስምም። ስለዚህ ስለሃይማኖት መከራከርና ማበላለጥ ተገቢ አይደለም። *እምነት ግን እግዚአብሔርን ብቻ ማመን* ስለሆነ (ኤር17፥5-9፤ምሳ22፥14)፣በአንዱ በልዑል እግዚ አብሔርና በላከው በልጁም ማመን ንጽጽር የለውም ዮሐ17፥3።

*ማኅበረ ቅዱሳን/ማቅ/ ከእንቅልፉ እንደነቃ የጻፈው መጽሔት* ከበፊት ሕትመቶቹ የተሻለ ይዘትና የጽሁፍ አቀራረብ የታሪክ ጥንክሩም ጥሩ የሚባል ነው። ምክንያቱም አባ ዘጋስጫ ኩንታል ሙሉ በልተው ኩንታል ሙሉ ተጸዳዱ ይሉን ስለነበር፤ ከዚህ አንፃር ሊበረታታ የሚገባው ነው። መጽሔቱ «*ሐመረ-ተዋህዶ ልዩ እትም ይባላል። የውስጡ ሰፊ ዘገባም ቁርዓንን መተቸት ነው።ይሁን እንጅ የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንዲሉ አበው የነሙሐመድን መጽሐፍ ሊቃወሙ በጻፉት ጥንክር ላይ የቤታቸውን ገመና* የኦርቶዶክስን ጉድ ባደባባይ ገልጠዋል[217]። ቁርዓንና ድርሣናቻችን አንድ *መሆናቸውን ያላስተዋሉት* ማቆች ኦርቶዶክስን ባደባባይ አዋርደዋታል። በርግጥ እሆን ብለው ላይሆን ይችላል። *ያለእውቀት ይመስላል*። ስለየሰስ ልደትና የሕጻንነት ጊዜ ቁርዓን በሱራህ፫፥፵፱ ከጭቃ ወፍ ስለመፍጠሩ ይተርካል። እነርሱም ይህ ትክክል አይደለም ብለው ቁርዓንን ይተቻሉ ነገር ግን "በቤተክርስቲያኒቱ" ውስጥ የሚገኘው ሌላው ቁርዓን እንዲህ ይላል "*..መንፈስ ርኩስም መልሶ እግዚአብሔር ሰማይን ምድርን በፈጠረ ጊዜ በምሥራቅ በኩል ገነትን በተከለ ጊዜ፤ በአምሳላችን በአርአያችን ሰውን እንፍጠር አለ፤ ሰውንም በእጁ ከመሬት*

[217] .ሐመረ ተዋህዶ ልዩ መጽሐፍ/መጽሔት/ : ማህበረ-ቅዱሳን ሚያዚያ 1999 ገጽ 14 - 38



*አንስቶ ፈጠረው ፈጥሮም መላእክትን በእጄ ለፈጠርኩት ሰገዱ አላቸው፤ ያንጊዜ ሚካኤል ተነስቶ እንደትዕዛዙ ሰገደ እኔ ግን የውነት ፈራጅ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ አልኩ፡በትዕቢቴም አምላክን ልገዳደር አሰቤ።በተፈጠርኩ ጊዜ ሰማይ ተዘጋብኝ ፈጣሪዮ ከእርሱ ዘንድ አባረረኝ፡በድንጋይ ላይ እንዲወርድ ዝናም፡ ከማዕረጌ ከአውርዶ ጣለኝ ኩንደኞቼም በታች ሆንኩ፡ ወደምድርም ጣለኝ በሰማይ ዳርቻ አስቀመጠኝ ክብሬም ይህ ነው..."*[218] በተጨማሪም ዲያቢሎስ ለአዳም አልሰግድም በማለቱ ከማዕርጉ እንደ ሻረው የቁርዓንን ሀሳብ በሱራህ ፪፥፴፬ ፲፯፥፷፩ እና ፯፥፲፩-፲፫ የተጻፈውን ተችተዋል። 81ዱ ይህንኑ የቁርዓን ሀሳብ ሳይለወጥ እንዳለ በ3ኛመቃብያን "*...ለሚዋረዱልኝ ለአዳም አልሰግድም በማለቱ እግዚአብሐር ስለአባታቸው ስለአዳም ከማዕርጌ አዋርዶኛልና" ይላል (3ኛመቃ1፥15፤4፥10፤2መቃ9፥3)*። በየሱስ የውልደት ጊዜ የዘንባባው ዛፍ *ታሪክም* ቁርዓን በሱራህ፲፱፡፳፪ ሲተርክ "ቤ/ክኒቱ" *ነገረ ማርያም* በተሰኘው *መጽሐፏ* ዘንባባ የሚለውን ዛፍ "*ያም*" በሚል የእጽዋት ዓይነት ተክታ *ያንኑ* ቁርዓን አቅርባዋለች።

ስለዚህ አሻግሮ የሰውን ሃይማኖት ከመቃወም የቤትን ገመና ጥራጊና ጉድፍ ማስወገዱ የተሻለ ሳይሆን አይቀርም። ጌታችንም ያስተማረው ይህንን ነው "*...ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴት ትለዋለህ? እነሆ በዓይንህ ምሰሶ አለ አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያ በሂላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ* " ማቴ7፥3-5 ብሎአል። ማቅና አባቶቹ ብዙ ጊዜ የሌሎችን ሃይማኖት ሲተቹ ይስተዋላሉ። የደረቀ ዋንዛ ተሸክመው እየሄዱ የቆመ ዛፍ ቅቤ እየቀቡ በሚያመልኩትም ይስቃሉ? መቼም ከእነርሱ የደረቀ እንጨት የነዚያ በሕይወት ያለው ዛፍ የተሻለ መሆኑን ማንም ሊፈርድ ይችላል። ሁለቱም ጣዖት አምላኪያን ቢሆኑም ሕይወት ያለው ከደረቀው ይሻላል። የራስን ጉድፍ ምሰሶና ግመል ተሸክሞ በሰው መሳቁ አንድ ቀን ሁሉም ወደ አደባባይ ሲወጣ ያሸማቅቃል አንገት ያስደፋልና እንደቃሉ ለመኖር ራስን ማስለመድ ከሰው ጉድፍ የራስን ማየት ነውና መልካም ነው።

[218] . ገድለ ጊዮርጊስ በግእዝና በአማርኛ፡ 1985፡ተስፋ ገብረሥላሴ ማ/ቤት ምዕራፍ፯ ገጽ 19-20

## *<u>የገዳማቶቻችንን ሀሜት /ግብረ ሰዶማዊነት/ ይበረታታልን ?</u>*

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ታላላቅ ከሚባሉ የተፈጥሮ ክሳራዎች መካከል 1ኛው የባቢሎን ውድቀት (የቋንቋ መደባለቅ)፤2ኛው ደግሞ ግብረ ሰዶማዊነት ነው። ሁለቱም ቅጣቶች ከሰው ልጅ አልፈው በእንስሳትና በመኖሪያው ምድር ላይ ክሳራን አምጥተዋል (ዘፍ11፥1 ዘፍ13፥11፤ዘፍ19፥11) የግብረ ሰዶማዊነትን ከየት መጣ ታሪክ የማያውቅ የዋህ ሰው፤81ዱን አንብቦ ይህንን ፀረ ፍጥረትና ፀረ ፈጣሪ የሆነ ድርጊት ቀላል አድርጎ ቢመለከተው መፍረድ አይቻልም። ምክንያቱም አባቶቼ የሚላቸው ደብተሮችና የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያሳተመው አዲሱ 81ዱ መጽሐፍ፤ይህንን ድርጊት አቅልሎና ለውጦ አንደኛ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ስላሳተሙለት መቃወም የሚችልበትን ጉልበት አፍዝዘውበታል።

ሰዶም ከዮርዳኖስ ማዶ ከዞሀር ምሥራቃዊ ክፍል የምትገኝ ከተማ ስትሆን በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ አስቀያሚ የሆነን ኀጢአት የሚተገበሩ መኖሪያ ነበረች ዘፍ13ና19። በዚያች ምድር የአብርሐም የአጎት ልጅ ሎጥ ነፍሱ ተማራለች፤ሁለቱን ልጆቹን ለርኩሰት አቅርቦአል፤ሚስቱን በጨው ሀውልትነት አጥቶል የክፋት ምድር ነች። እግዚአብሔርም የቁጣው መቅሰፍት የነደደበት እሣት ከሰማይ ያዘነበበት ነው። ሰዶማዊነት ዛሬም ቢሆን በልዑል ፊት ርህራሄ የሌለው ቅጣት ያለበት ኀጢአት ነው። ምክንያቱም የተፈጥሮን ኪዳን የሚቃወም ነውና። አንድ ጓደኛዮ የተፈጥሮ ሳይንስና ማኅበራዊ ግንኙነት ጥናቱን በኤች አይቪና ተዛማጅ ሁነቶች ላይ 2ኛ ዲግሪውን ሲሰራ፤ያገኘው ጥናት እንደሚያመለክተው በአዲስ አበባና በአቅራቢያው በሚገኙ ገዳማውያን ላይ የግብረ ሰዶማዊያን ብዛት በመቶ ሲሰላ ከፍተኛ ነው[219]። ይህ እንግዲህ የዚሁ መጽሐፍ/81/ማበረታቻ ውጤት ነው ቢባል ማጋነን

[219] በማህበራዊ ግንኙነቶች ዙሪያ ምስጢራዊ ጥናት ስለሆነ መረጃውን ይፋ ማድረግ ስለማይቻልና የአንዳንድ የዋህ ምዕመናን አእምሮ ለመጠበቅ መረጃውን ይፋ ከማድረግ ተቆጥቢያለሁ።



አይሆንም። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ስም የምትጠራ ቤተ ክርስቲያን የፍጥረትና የፈጣሪን ሕግ የሚቃወም ድርጊትን አምርራ በመቃወም ፋንታ ማለዘቧ እንዳለ ሆኖ፤በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን መለኮታዊ ቃል መለወጥ ከመደገፍ አይተናነስም። ይህንን ኀጢአት በግልጥ የሚቃወመውንም ክፍል መሠረዝ፣ ወይም መለወጥ ወይም በአሻሚ ቃላት መተካት ደጋፊ አስመስሏታል።

"ቤተ ክርስቲያኒቱ" ሃይማኖቱን ጠበቅሁ ስትል የጥንቱን መጽሐፍ በመደለዝና በመፋቅ በደካማ ቃልና ሀረግ ቀይራ ለርኩሰት ሀሳብ ማበረታቻ ዳርጋዋለች። በ1915ና/33ዓ.ም. የታተመው የድሮው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን በ1ኛጢሞ1፥8-11 ላይ ‹‹...ወንዶች ለባሕሪያቸው የሚገባውን ሴቶችን ማድረግ ትተው በፍትወት ተቃጠሉ..››ይላል። በ2ሺ. 81ዱ እትም ግን "ለኀጢአተኞችና ለከዳተኞች ኀጢአትን ለሚያዘወትሩና ከእውነት ለወጡ ርኩሳን ..ለሴሰኞችና ለአመንዝራዎች..." እያለ በመቀጠል ስለ አሪት ትዕዛዝ ብቻ ትንታኔን በመስጠት ሀሳቡን ይቋጫል። ግብረ ሰዶማዊነትን የሚቃወመውን ሀሳብም አውጥተውታል ሠርዘውታልም። በተጨማሪም ይህንኑ አቋም የሚያጠናክር ሆኖ ያገኘሁት በመጽሐፈ ኩፋሌ 16፥24 ላይ የሚገኘው ሀሳብ እንዲህ ይላል "...ሁለቱም በአንድ አልጋ በአንድነት ተኙ ያዕቆብም በአባቱ አባት በአብርሃም አጠገብ ተኛ ሰባት ጊዜም <u>ሳመው</u> ሩህሩህ <u>ልቡናውም</u> በእርሱ <u>ደስ</u> አለው" ይላል። አልጋ ላይ ሲስመው ልቡን ደስ አለው ማለት ምን ማለት ይሆን? በተጨማሪም በሮሜ1:27 የተገለጠውን መልእክት በማፍዘዝ <u>ሴቶቸን መገናኘት ትተው</u> የሚለው ኀይለ ቃል ተሰርዟል። በአጠቃላይ እይታ "ቤተ ክርስቲያኒቱ" ይህንን ድርጊት የምታበረታታ ሆና መቅረቧ በእጅጉ ያሳዝናል። ግብረ ሰዶማዊነትና ቀላጭነት የከፋ ኀጢአት ነው። ይህንንም የሚቃወም ትምህርት በግልጥ ሊሰጥ ይገባል። መጻሕፍቶችንም ማረምና እንዲህ መሰል ፀረ ክርስትና ፀረ ፍጥረት አበረታች እትሞችንም ማስተካከያ መስጠት የሁሉም ክርስቲያን ግዴታም ኃላፊነትም ነው። ስለሆነም አፓክሪፓ

መጻሕፍቶችን ከቅዱሱ የልዑል ቃል እንዳይቀላቀል ለይቶ ማሳየቱ ተገቢ መሆኑ አንደኛው ሥራ ሲሆን፤ቅዱሱን መጽሐፍ መሠረዝ መልእክቶቹን መቆራረጥና መለወጥን አምርረን መቃወም ደግሞ ሌላኛው የሁላችንም ክርስቲያኖች ሥራና ግዴታ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ "ቤተ ክርስቲያንም" ወደ ጥንት መሠረቷ እንድትመለስ ማገዙ ከዚህ መሰል የክህደት አረንቋ እንድትወጣ ይረዳታል። በሮም ካቶሊክ ፍቅር ከወደቀችበት ከንቱ የርኩሰት ትምህርትም እራሷን ልትለይ ይገባታል። ቅዱስና ፍጹም የአምላክ እስትንፋስ በሆነው በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እንደጥንት አስተምህሮዋ ዛሬም በዚህ ዘመን ልትመራበት ይገባታል። በግብረ ሰዶማዊያን ኀጢአት የተያዛችሁ ደግሞ እንደ ሌሎች ሱሶች በየሱስ ስም የሚወገድ ርኩስ መንፈስ ስለሆነ፤እግዚአብሔርንና የላከውን ልጁን በብቸና አዳኝነት በሚያምኑ ቅዱሳን ጸሎት እገዛ ስለምትፈወሱ ክርስቶስ የሱስን መማጸን አማራጭ የሌለው ፍቱንም ፈውስ ነውና ከዚህ ርኩሰትና ኀጢአት ልትለዩ እንደሚገባ እና እንደሚቻልም እመኑ ጸልዩም።

### *እግዚአብሔር አዳምን ከጥንት ሲፈጥረው ኃጢአተኛ አድርጎ ነው*

ለብዙዎቻችን ይህንን ንዑስ ርዕስ ስናነብ ሳያስደነግጠን አይቀርም። ምክንያቱም በልዑል አምላክ ላይ ይህንን ያህል የድፍረት ንግግር ይጽፋሉ ብለን አናስብ ይሆናል። ይሁን እንጅ ሰይጣን ዋና ዓላማውን ለዘመናት ሲያስፈጽምበት በኖረው አውድማው ላይ፤ ከዚህም በላይ ተብሎአል። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው ስንል፤ አዳም አስቀድሞ እንደሚሳሳት እያወቀ ለምን ፈጠረው? ይላሉ። በርግጥ ጥያቄያቸው ተገቢ ቢሆንም፤የሰውን ልጅ በራሱ መልክና ምሳሌ ስለፈጠረው ከሌሎች ፍጥረታት የተለየና የከበረ ፍጡር ነው። ብዙ ሰዎች ለራሳቸው ያላቸው አመለካከት ፈጽሞ የተበላሸ የሚሆነውም በፈጣሪ አምሳል መፈጠራቸውን ባለማወቅ ነው። ሰው በልዑል ምሳሌና መልክ የተፈጠረ ልዩ ፍጡር ነው። የፈጣሪ መልክና ምሳሌ አሁን ከምንኖረው በላይ ቢሆንም፤አሁን ያለንበትን



የከፋ ውድቀትና የታናሽነት ሂደትን፤ እኛም ሆን የፈጠረን አምላክ የማንወደው ነው። ለዚህ ነው ልጁን ልኮ ርስታችንን ያስመለሰልን ዮሐ3፥16። የእግዚአብሔር መልክ ደግሞ ክርስቶስ ነው 2ቆሮ4፥4፣ ፊል2፥6 በዳግመኛ መወለድ ከመገኛችን እግዚአብሔር ተመልሰን የምንገባውም በዚሁ መንገድ ብቻ ነው።

ሰው በተፈጥሮው ኀጢአተኛ አልነበረም መ/መክብብ 7፥29። ይሁን እንጅ ይህንን ያላስተዋሉና ከሰው ልጅ የጥንት ጠላት ጋር የጠበቀ ዝምድና ያላቸው ደብተሮቹ፤ በሃይማኖት ካባ ውስጥ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲቃወምና ከልዑል ሀሳብ ጋር እንዲለያይ፤የኖረ አጀንዳቸውን በመ/ዕዝራ ሱቱኤል2፥30ና6፡1 ላይ ገልጦአል «*ጥንቱን ኀጢአት በአዳም ልቡና ተሰርቶ ነበርና...*» በሁለተኛው ክፍልም «*...ይህን ዓለም በፈጠረው ጊዜ አዳምንም በፈጠረው ጊዜ ቁርጥ ፍርድ ገሃነምን አስቀድሞ ገና አዘጋጀ*» ይላል። ገሃነም እሳት ገና ከጥንቱ ለሰው እንደ ተዘጋጀ የሚናገረው መጽሐፍ፤የልዑልን ባህሪይ ጨካኝ፤ለሰው መልካም የማያስብ፤ከማድረጉም በላይ የጌታችንን ትምህርት ይቃወማል። ጌታችን በወንጌል«...ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘለዓለም እሣት ከእኔ ሂዱ..» (ማቴ25፥41) ስለሚል ለሰው ልጅ እንዳልተፈጠረ መረዳት ይቻላል።

### ***<u>ለ10 ብር ሲል ሐሰትን በሐሰት ላይ የደራረበው መልአክ</u>***

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ "ቤ/ክያን" ውስጥ የመታሰቢያ ዕለት ተሰይሞ ለት ወር በገባ በየ13ኛው ቀን የሚከበርለትና የሚዘከርለት መልአክ ሩፋኤል ይባላል። ይህ መልአክ በሁሉም የአፖክሪፓ መጻሕፍትና ድርሣናት ውስጥ ስሙ የተገለጠ ቢሆንም፤በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ፈጽሞ አይታወቅም። በአፖክሪፓም ሆነ በድርሣናቱ ውስጥ የተገለጠባቸው ማንነቶች ቅዱስ መላእክ መሆኑን እጅግ አጠራጣሪ ገለጻዎች ናቸው። እንደ መጽሐፈ ጦቢት ገለጣ ከሆነ ሩፋኤል የመላእክት አለቃ ነው። ባህርይውን ሲገልጥ ደግሞ ስንኳን በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም መላክ፤አንድ ዓለማዊ ሥጋዊ ፍጡር ከሞራል አንጻር እንኳ ሊፈጽመው የማይችል ገጽ ባህርይን ተላብሶ

ቀርቦአል፡፡ ለምሣሌ፡- በመጽሐፈ ጦቢት ምዕ6ቁ7ና16 ላይ የመተት አሰራርን ለሰዎች ሲያስተምር እናያለን፡፡ በምዕ12ቁ9 ደግሞ ምጽዋት ከሞት /ከገሃነም እሣት/ እንደሚያድን ከኀጢአትም ነጻ እንደ ሚያወጣ ይናገራል፡፡ በምዕ12ቁ20 ደግሞ የሰዎችን ጉዳይ የዕለት ውሎ እየተከተለ ታሪክ ሲዘግብ የሚውል ጋዜጠኛ ሆኖ ይህው መልአክ በስፋት ተተርኮለት እናነባለን፡፡

በኦርቶዶክስ የድርሣናት መጽሐፍ ውስጥ ድርሣነሩፋኤል በሚበላው ክፍል የልምድ አዋላጅ፣ለሴቶች የማህጸንና የወሊድን ጉዳይ የሚከታተል ሆኖም ተዘግቦአል፡፡ በሌላ ክፍል ደግሞ የሰዎችን ዓመታዊ የጸሎት ስብስብ ወደ ፈጣሪ የሚያደርስ ነው ተብሎአል፡፡ በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕ19ቁ1 ደግሞ ከሚካኤል ጋር ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ ዕውቀት ላይ ጥያቄ ያለው መልአክ ሆኖ በመቅረብ፤ መንፈስ ቅዱስን ሲያማ እናነባለን፡፡ ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሙ የማይታወቀው ይህ ሩፋኤል የተሰኘ መልአክ፤በተጠቀሰባቸው የአፖክሪፓና የድርሣናት ክፍል ውስጥ ሁሉ ለሰዎች ጥንቆላን፣ ሐሰትን፣ሀሜተኝነትን የሚያስተምር ነው፡፡ ስለዚህ ባህርይውንና ሥራዎቹን በመንተራስ የመልአኩን ማንነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከዚህ በመነሣትም ደብተሮቹ ሩፋኤል በማለት የሚጠሩት የቅዱሳን መላእክት ወገን ሳይሆን የአጋንንት አለቃ ለመሆኑ ጥርጥር አይኖረንም፡፡ ምን አልባት ይህ መልአክ የቅዱሳን ወገን ነው ከተባለ እንኳ በስሙ የተጠቀሱት ባህርያትና ግብሮቹ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ስለማያስችለው ማስተካከያ ተደርጎበት ደብተሮቹ ስሙን ያጠፉት መልአክ ነው ተብሎ "በቤተ ክርስቲያኒቱ" አመራር በኩል የማስተካከያ መግለጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በተለምዶ 81ዱ በተሰኘው መጽሐፈ ጦቢያ ውስጥ ሩፋኤል ከሦስት ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ የዋሸበትን ምስጢር በስፋት ያስነብበናል፡፡ ለ10ብር ወይም ለአንድ ድርሀም ሲል ሐሰት በሐሰት ላይ ሲደራርብም፡- 1ኛው የወንድምህ የታላቁ አናንያ ወንድም አዛርያ ነኝ /5፥10-12/፤2ኛው ስለሜዶን ራጊስ ስለገባዔል ሲጠየቅ በዚያ ነበርኩ 3ኛጊዜ ከወዴት መጣችሁ ሲባሉ ሩፋኤል ፈጠን ብሎ በተካነው የሐሰት ልምዱ ከንፍታሌም ልጆች ወገን ወደነነዌ የተማረክን



ምርኮኞች ነን ሲል የውሸት ቋቱን ሲያፈስ እንመለከታለን፡፡(መጽሐፈ ጦቢት ምዕ5ቁ10-12) ይህ ሁሉ ሐሰት ደግሞ በገባዔል ዘንድ ጦቢያ ያስቀመጠውን ገንዘብ ተቀብሎ የውሎ አበሉን ክፍያ ለማግኘት ነው (ምዕ4፥20ና 5፥14)፡፡ ከዚህ በላይ እንደሚከፈለው ቢነገረው ኖሮ ወይም ቢዋዋሉ ሩፋኤል ተብሎ የተገለጠው አካል ፈጣሪውንም ሊክድ ነፍስም ሊያጠፋ እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም እንደ መጽሐፉ ገለጣ ከሆነ ማለቴ ነው፡፡

ስለዚህ የተጠቀሰው መልአክ በርግጥ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆነ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ሥፍራ የሌለው በሰማይ ሠራዊትም መካከል የተዋረደ መሆኑ ግልጥ ነውና፤በየ13ቀኑ በስሙ ዋንዛ ጠርባችሁ ደፋ ቀና የምትሉ ወንድም አባቶቼ ቀኑ ሳይጨልም ድንገትም ሳትወሰዱ ብታስቡበት መልካም ነው፡፡ ከሞት የተነሣውን የትንሣኤ ጀግና (1ቆሮ15) ፍቅሩን እስከ ሞት በመስቀል በመግለጥ መውደዱን ያሳየውን እውነተኛ አፍቃሪ የሱስ ክርስቶስንም (1ጴጥ2፥24) ብትከተሉ ዛሬ ይቅር ሊላችሁና ከኀጢአትም በደሙ ሊያነጻችሁ የታመነ መሐሪና ቸር አምላክ ነው፡፡ የሊቀ መልአኩን ስም በማጥፋት ክፉ ባህሪ የሳሉብን ደብተሮች ከሆኑ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሙ ባይታወቅም መልአክ ከሆነ ይህንን የጻፉ ደብተሮች አጋንንዊ አስተምህሯቸውን በስህተትና በይቅርታ እንደ ተሳሳቱ ለሕዝቡ በይፋ ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል፡፡ እግዚአብሔር ያከበራቸውን ቅዱሳን መላእክት ሊያከብሩ የተዋረደውን ወዳጃቸውን ዲያቢሎስን ደግሞ ሊክዱ ከተስማሙና ከልባቸው ከተመለሱ ምሕረት ያገኛሉና "ቤተ ክርስቲያኗን" ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል፡፡

## የቁርዓንና የ81ዱ ዝምድና፤እንዲሁም የመንፈስ አንድነታቸው

‹‹…ከዚያ ለአዳም ስገዱ አለን ወዲያውም ሰገዱ አብሊስ/ዲያቢሎስ/ ሲቀር ከሰጋጆቹ አልሆነም፤አልላህም/አላህ/ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ? አለው አብሊስም እኔ ከርሱ የበለጥኩ ነኝ ከእሳት ፈጠርከኝ ፤እርሱን ግን ከጭቃ ፈጠርከው አለ፡፡ አልላህም ከእርሷ ከጀነት /ገነት/ ውረድ በርሷ ውስጥ ልትኮራ አይገባህምና ውጣም

አንተ ከወራዶች ነህና አለው›› (ቁርዓን አልአዕራፍ ሱራህ 7፥11-13) የኦርቶዶክሱ 81ዱ ደግሞ‹‹…ለሚዋረድልኝ ለአዳም አልሰግድም በማለቴ፤እግዚአብሔር ስለአባታቸው ስለአዳም ሲል ከማዕርጌ አዋረደኛልና…››3ኛመቃብያን 1፥15-16፡፡ እንዲሁም ቁርዓን በሱራህ 2፥14፤17፥15-16 ከመቃብያን 4፥8-10 ጋር አንድ ነው፡፡ ቁርዓንም ይበለው የኦርቶዶክስ አዲሱ 81ዱ፤ዲያቢሎስ የተዋረደው ግን አዳም ከመፈጠሩ በፊት ነው ዘፍ1፥2፤ኢዮ26፥13፡፡ የታልሙድ ታሪክም ይህንን ያስረዳል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳንም በሐመር መጽሔቱ ‹‹በክርስትና ትምህርት ሰይጣን የወደቀው ለአዳም አልሰግድም በማለቱ አይደለም ከአዳም መፈጠር በፊት ነው››[220]ብሏል ይህ አባባል" በርግጥም ትክክልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ነው፡፡

በአብዛኛው የውስጥ ሀሳቡ ከቁርዓን ጋር የሚመሳሰለው ሌላው "የቤ/ክያናችን" ቁርዓን ደግሞ ድርሣነ ሚካኤል ነው፡፡ "አንዱ አለቃ ግን ከሠራዊቱ ጋር ወደቀ ዲያቢሎስ ለአዳም መስገድን እንቢ ስላለ ወደቀ" ይላል ዘጥር ሚካኤል ድርሣን [221]፡፡ በመሠረቱ ዲያቢሎስ የመላእክት አለቃ አልነበረም፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ዲያቢሎስ ከመላእክት ወገን እንዳልነበረ ነገር ግን ኪሩብ እንደሆነ ያስረዳል ሕዝ28፥11-15፡፡ መጋረጃ የሚጋርድ ልዩ ፍጡር እንጅ የመላእክት አለቃ አልነበረም ሕዝ10፡፡ እንዲያውም በነበረው የከበረ ሥፍራ በመታበዩ ከማዕርጉ እንደ ወረደ እናነባለን ሕዝ28፥17፡፡ ቁርዓን አል አዕራፍ ሱራህ3፥49 የአልመሲህ ኢሳ/የሱስ/ የልጅነት ጊዜን ሲተርክ ‹‹…በምልክትና በተአምር መጣሁባችሁ እኔ ለእናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ እፈጥራለሁ በርሱም እተነፍስበታለሁ በአልላህም (አላህ) ፈቃድ ወፍ ይሆናል›› ይላል፡፡ በኦርቶዶክስ መጽሐፍ ደግሞ "ተአምር ዘገብረ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሣህሉ ወምሕረቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለም ዓለም አሜን! ወአሐተ ዕለተ እንዘ ይትዋነይ እግዚእ ኢየሱስ ምስለ

[220] .ሐመረ ተዋህዶ ልዩ መጽሔት ማኅበረ ቅዱሳን ሚያዚያ 1999 አዲስ አበባ ገጽ 30

[221] . ድርሣነ ሚካኤል፡ ግእዝና አማርኛ 1981 ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት አዲስ አበባ ገጽ153



ሕጻናት ገብረ ፅቡረ በማይ ወገብረ እምውስቴቱ ብዙኀተ ከመአርአያ አዕዋፍ ንዑሳን ወዐቢያን ወነፍሐን ለኩሎን ሠረረ በሥጋ ወነፍስ" [222] ከዕለታት በአንደኛው ቀን ጌታ ኢየሱስ ከሕፃናት ጋር ሲጫወት ጭቃ አደረገና ከውስጡ በታናናሽና በታላላቅ አዕዋፍ አምሳል ሥዕል ሠራ ከዚያም እፍ አለባቸውና በረው በረው ሄዱ" ይላል፡፡ በዚህ ተውኔት ውስጥ ከእርሱ ጋር ይጫወቱ የነበሩ ሕጻናት እንደርሱ ለማድረግ ቀኑን ሙሉ እፍ ሲሉ በመዋላቸው የጉሮሮ በሽተኞች ሆኑ ይላል፡፡ በመቀጠልም ሕፃናት ብሎ የጀመረው አንቀጽ ሕፃናትን ይረሳና ሊቅ ሆይ! እኛም እንዲበሩልን ምን እናድርግ አሉት፤እርሱም በድንግል ማርያም ልጅ ስም ብረሩ በሏቸው አለ" ይላል፡፡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሙታንን ስም ማንሳት ስለሚወዱ እንጅ ለሕጻናት እንዲህ ይላል ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው፡፡ አንድ ሕፃንም ከጌታችን እግር ሥር ወደቀና "እድሜየን ሁሉ እስከለተ ሞቴ እገዛልሃለሁ አገልጋይ ህም ልሁን ይህንን ስልጣን ስጠኝ አለው" ይላል ሕፃኑ??? ሕፃናት ምንም ድንቅ ነገር ቢያዩ ስጠን ብለው ያለቅሱ ይሆናል እንጅ፤ሊቀ ሆይ! ብሎ እግሩ ሥር ወደቀ ማለት ተረቱን ያኀላባቸዋል፡፡

ስለዚህ አጠቃላይ ሀሳቡን ስንገመግመው "ተአምረ የሱስ" የተሰኘው የኦርቶዶክስ መጽሐፍ ትንሹ ቁርዓን ነው ልንለው ድፍረት እናገኛ ለን፡፡ በቁርዓን ማህዱስ ክፍልም "መላእክት ወርደው ሚስቶችን አግብተው አዛሄልና አዛዝሄል /ሂሩትና ማሩት/ የሚባሉ ረጃጅም ልጆችን ወለዱ" የሚለውን ሀሳብ በሀገር ቤቱ መኩሪያ ድርሰት መ/ሄኖክ ም2፥1-16 ላይ የማህዱስን ግልባጭ እናገኛለን፡፡ በአጠቃላይ እይታ ይህ አካሄድ በየመድረኩ አንድ ነን፤ሁለቱን ሃይማኖቶች ብቻ ነው የምናውቀው፤ ይባል የነበረውን ሀሳብ በግልጥ ያሳየ ነው፡፡ የ2ቱንም የመንፈስ አንድነትና ወዳጅነትንም ይህ መረጃ በትክክል ያጠናክርልናል፡፡ 81ዱ የተሰኘው የኦርቶዶክስ መጽሐፍ የቁርዓንን ሀሳብ የሚጋራው ተጨማሪዎቹ/15/ብቻ አይደለም፡፡ የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍምበመደለዝናበመለወጥ የነሙሐመድን ወዳጅነት አሳይቷል

[222] . ተአምረ ኢየሱስ በግእዝና በአማርኛ 1990፡ ገጽ 21



**የአቋም መግለጫውን ለማሳየት**

1..የጴንጤ አገልእምነት..ተባብረንለማጥ ፋት በውሳኔ አሳልፈናል።
2. ቤት ያከራዩ ወይም ያስጠጉ ክርስቲያ ኖች ወይም እስላሞች በአስቸኳይ እንዲ ያስለቅቁ ጴንጤ የሆኑም እንዲመለሱ
3. ይህ የ2ቱም ሃይማኖት ዐር ጴንጤ...
4...ቢሞቱ በየትኛውም ቦታ እንዳይቀበሩ
5.ማንኛውም የርካሽ እምነት ተከታይ /ጴንጤ/እድር ቅሬ መመስረት አይችልም
6.የ2ቱም ሃይማኖት ተከታዮች ጴንጤን . አጥብቀን እንቃወማለን።

ፏብቷ ከተማ ኦርቶዶክስና እስላም የወንጌል አማኞችን በጋራ ለማጥፋት የአቋም መግለጫ

በ*ዘፍ22፡2* ላይ‹‹*...አብርሐምም እነሆ አለሁ አለ የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞርያ ሂድ*›› የሚለውን ሀሳብ‹‹*...ይስሐቅን ይዘህ ወደ ከፍተኛው ተራራ ሂድ*›› በማለት ይተርካል። እስራኤልና ፍልስጥኤም ለዘመናት ሲጋደሉ የኖሩበትን የኔነት ድርሻ የሞርያን ተራራ ከአይሁዶች እጅ አሻራውን በማጥፋት ሞርያን በአንድ ከፍተኛ ተራራ ተክቶ የጥንቱን ስምም ሰርዞ አቅርቦታል።

በሐዲስ ኪዳንም እንዲሁ በ*ሉቃ1፡32-33* ‹‹ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱ ታላቅ ይሆናል›› የሚለውን በመሰረዝ‹‹..*እርሱ ታላቅ ነው*›› ብሎ እንደ ጎረቤቶቹ ሙሐመዳዊያን የሱስን በአንድ ወቅት የነበረ ታላቅ ሰው አድርጎ ጽፏል። በ*ሉቃስ 1፡48* ማርያም ‹‹...የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና››ያለችውን፤የኦርቶዶክስ ደብተሮች 2በ81ዱ‹‹..የባርያውን ትህትና ተመልክቶአልና›› ይላል። ውርደት የሚለውን ትህትና በሚል ሲለውጠው፤የባርያውን የሚለው ቃል የወንድ ጾታን ገላጭ ነው። 81ዱን ያሳተሙልን "የቤ/ክያኒቱ" የሊቃውንት ጉባኤናሲኖዶስ፤ጾታን መለየት ተስኖታል።ስለዚህ የነገረ መለኮትን ምስጢር ይጠነቅቃል ብሎ ማሰቡ ለኦርቶዶክባዊያን አፋፍ ላይ ቆሞ መጫወት ይሆናልና ቢታሰብበት መልካም ነው እላለሁ።



# *ክፍል አምስት*

## *መጽሐፍ ቅዱስን የተቃወመው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር*

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከተመሠረተበት ከ1917ዓ.ም አንስቶ በዋና መ/ቤቱ ርእዮና አላማ መሠረት የሚተዳደር መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጅ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሥራ ሂደት ስንገመግም በተቃራኒ መንገድ እየሄደ መሆኑን በየዕለት እንቅስቃሴ ውጤቶቹ ማየት እንችላለን። ይህ ማኅበር ርእዮን በግልጥ በማስቀመጥ በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ ቅዱሳን ጉሮሮ በሚያገኘው ገንዘብ የሚተዳደር አትራፊ ያልሆነ አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ነው። ማኅበሩ እንደሌሎች ሀገራት ሁሉ በኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ቢሮው ከልዩ ልዩ ቤተ እምነቶች በተውጣጡ አባላት ሲመሠረት፤ የሁሉንም ቤተ እምነት አስተምህሮና ዶግም /Dogma/በማይቃወምና በማይደግፍ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱስን የትርጉም ሥራ ሊመራ ነበር ። የትርጉም ሥራውንም ለእናት ቋንቋው ታማኝ በሆነ፤ለትርጉም ቅባሎት በተመቹ ቋንቋዎች፤ማህበረተሰቡ ሊያገኘው በሚችል የዋጋ ምጣኔ፤እያስተረጎመና እየተረጎመ የሚያደርስ ሊሆን ተመሠረተ።

*<u>የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ርእይ ምንድን ነው</u>*? የማኅበሩ ርእይ ግልጥ ቀላልና የሚተገበር በሦስት ነጥቦችም የተቀመጠ ነው። አንባቢ ይመዝነው ዘንድ በዓለም አቀፍ የመግባቢያ ቋንቋው እንግሊዝኛ ያገኘሁትን ጽሑፍ እንዳለ አቀርበዋለሁ።

THE PURPOSE OF BIBLE SOCIETY

1. In a language which can be easily understood and is faithful to the original texts.
2. Without sectarian doctrinal note or comment.
3. At a price which people can afford and in a formal people will appreciate. (***sorce:www.biblesocity.org***)

፩. በቀላሉ ለመግባባት በሚቻልበት ማንኛውም ቋንቋ ለእናት ቋንቋው /ቅጅ/ ታማኝ መሆን ፦

፬. የማንኛውም ወገን የእምነት አጀንዳ/አስተያየት/ ያልስፈረበት :-

፫. ተመጣጣኝ በሆነ የሽያጭ ዋጋ ሕዝቡን /ተጠቃሚውን/ በሚያበረታታ የዋጋ አቀራረብ ማድረስ የሚሉ ናቸው።

፭. ለእናት ቋንቋው(ብሉዩን ለዕብራይስጥን፤ሐዲስ ኪዳኑን ለግሪክ) ታማኝ መሆን የሚለውን ዓላማው ያደረገው የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤የኦርቶዶክስ "ቤተ ክርስቲያን" ለአዲሱ ትርጉሟ ለብሉይ ኪዳን ሰባ ሊቃናትን፤ለሐዲስ ኪዳን ግእዙን ነው የምጠቀም ስላለች፤ዓላማውን በመሳት አሳትሞአል። ይሁን እንጅ "ቤ/ክኒቱ" በጥንት ታሪኳ ስንኳንስ እናት ቋንቋውን ግሪክና ዕብራይስጥ፤ዓረብኛ እንኳ ትጠቀም እንደነበር የታሪክ ድርሣናቿ ያሳያሉ። <u>ለምሳሌ</u> **«ሰላም ለከ ለያመ ሃይማኖት ስርዋ፤ትዛዛተ ኦሪት ወወንጌል እንተ ዲቤከ ተከእዋ፤ሰላማ ዝከርከ ከመ በኅቤነ ነዋ፤በከናፍሪከ ምዑዛት እመዓዛ ከርቤ ወዐልዋ፤ <u>እምነ ዓረቢ ለግእዝ</u> መጻሕፍት ተዐልዋ»**[223] አባሰላማ የተሰኙ መተርጉም በሞቱ ጊዜ የተደረሰላቸው መልክዕ ነው። *ትርጉም* "የሃይማኖት ዛፍ ሥር ለሆንከው ላንተ ሰላምታ ይገባል፤የወንጌልና ኦሪት ትዛዛት በአንተ ላይ ፈሰዋል፤ሰላማ ሆይ! መታሰቢያህ በኛ ዘንድ ይገኛል፤ ከርቤና ዐልቃ ከሚባሉ ሽቱዎች የበለጠ መዓዛ ባላቸው ከንፈሮችህ ኃይል፤ <u>መጻሕፍትን ከዓረብኛ ወደ ግእዝ ተርጉመሃል</u>" ይላል።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚረዱ ረጅዎቹ፤ከላይ የተገለጠውን ዓላማ በማሳየት የኀትመት ገንዘብ ቢሰበስብም፤ርእዩንና አላማውን ትቶ ትልቅ መንፈሳዊ ኀላፊነቱንም ከግምት ሳያስገባ አሳማኝ ሁነት በሌላት በአንድ የሃይማኖት ድርጅት እሳቤ በመጠላለፍ የደብተሮችን ድርሳን በመሰብሰብ ለሁሉ በሆነውና የሆነውን ገንዘብ በተለይም ቅዱሳን የአምላካቸው ቃል መግዛት ለማይችሉት እንዲደርስላቸው አስበው ለሕትመት የሰጡትን ገንዘብ ኀላፊነቱን በመተውና የጋራ የሆኑትን 66ቱን መጻሕፍት ሳይቀር በደብተሮች አሳብ በርዞና ሰርዞ በማሳተም ተባባሪነቱን አሳይቶአል።

[223] .መጽሐፈ. ስንክሳር፡በግዕዝና አማርኛ፡ከመስከረም-ነሐሴ፡ት/ማ/ቤት፡ ዘነሐሴ 20 ምንባብ



፬. የትኛውንም የሃይማኖት ድርጅት አቋምና አጀንዳ ሳይቀበል ቅዱስ መጽሐፍን ብቻ የሚያሳትም መሆኑን በዓላማው ቢገልጥም የአንድ ሃይማኖት ድርጅት አጀንዳ አስፈጻሚ ሆኖ ተገኝቶአል።በሐዲስም ሆነ በብሉይ ኪዳን ላይ ከዕብራይስጥ፣ከግሪክና ግእዝ የማይገኙ ቃላትና ሀረጋትን እየቆራረጡና እየጨማመሩ ለድርጅታዊ ደካማ አስተሳሰብ በክለው ሲሰጡት ሳይቃወም አሳትሞአል። ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ ይደርስ ዘንድ ከችግራቸው ሳይቀር እየሰጡ የሚገኙ የቅዱሳንን ገንዘብ ከሀገር ቤት እስከ አሜሪካ ምድር የሚሰበስበው ማኅበሩ ለኑፋቄና ለፀረ ክርስትና አስተምህሮ ማሳተሚያ ማድረጉ እጅግ አሳዛኝ ነው።በዚህ ድርጊትም ጠያቂናከልካይ ያለው አይመስልም?[224]

፫. ማኅበረሰቡን ባማከለ መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ የእግዚአብሔርን ቃል ለማቅረብ በገባው ዓለም አቀፍ ቃል መሠረት በኢትዮጵያ ምድር ቅርንጫፉን ቢከፍትም፤ከዓላማው በተቃረነ መልኩ እያከናወነ ይገኛል። የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በየትኛውም ዓለም ተቀባይነትና ዕውቅና የሌላቸውን ሀገር በቀል የጥንቆላና የፈጠራ ልብ ወለድ ድርሰቶችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እኩል በመቀበልና በማጽደቅ ትውልዱን በሚገድልና ከክርስትና ይልቅ እስልምናን የሚደግፉ መጻሕፍትን አሳትሞአል።(በገጽ24 ና66 ይመልከቱ) የሥርጭት ይዘቱን በሚመለከትም ከማኅበረሰቡ ኑሮ ጋር የማይጣጣም ከመሆኑም ባሻገር አንድ የብሉይና የሐዲስ ኪዳንን ክፍል ያካተተ መጽሐፍ ቅዱስ ከ20-40 ብር በሚሸጥባት ሀገር ከሁለት መቶ ሃምሳ ብር /ከ250/ በላይ በሆነ የኢትዮጵያ ብር መቸብቸቡ ማኅበሩ ርእዩን ትቶ ወደንግድ ተሰማራ እንዴ ያሰኛል።

ስለዚህ እንደ ዓላማና ርእይ ያስቀመጣቸውን አቋሞች እንዲያነሣና በሌላ እንዲተካ ሊጠየቅ ይገባዋል። በዚህ አሰራሩም የክርስትናን መርህ ቅዱስ መጽሐፍን ይጠብቅልኛል ብሎ ማሰቡ ለክርስቲያኖች ሁሉ ጥያቄ ውስጥ የገባ ጉዳይ መሆኑን ሊያጤኑት የሚገባ ይመስለኛል እላለሁ።

[224]. የ1980ዓ.ም 81ዱ መጽሐፍ መቅድም 7ኛ አንቀፅ 10ኛ መስመርና የ2ሺዕትም አንቀፅ 10



*የተለያዩ የሕትመት ይዘት ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አይነቶች ዋጋቸው ልዩ ልዩ ነው:: ነገር ግን ለኦርቶዶክስ በታተመው ጥራዝ ልክ የሆ ነው ግን መጽሐፉ 81ድሳይ ሆን 81ድ የሚል የሐሰት ቅስቀሳ ማሕበሩም ሆነኦርቶ ዶክስ፤ለንግድ ሲሉ በሀሰት ሕዝቡን ከማታለላቸውም በላይ ዋጋው ተመጣጣኝ አይደለም::*

በማኅበሩ የመተዳደሪ ደንብ አንቀጽ አንድ ሐምሌ 2 1968 ዓ.ም. ተሻሽሎ በቀረበው ደንብ ለ<u>ተ.ቁ</u> <u>፩</u> ላይ "*መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ወይም በከፊል አስተያየት ሳይታከልበት ሰዎች በሚገባቸው ቋንቋና ሊገዙ በሚችሉበት መጠነኛ ዋጋ አዘጋጅቶ ማቅረብ* " ይላል:: /The Constitution of the Bible Society of Ethiopia Article I; N<u>o</u>**1.** <u>The Objective of the Society shall be</u>:- To produce the Holy Scripturess,in whole or Inpart without Comment & To make them Available to People in language they can Understand & At aprice they Can Afford to Buy./ Jan.1,1977 Addis Abeba.[225] በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተመለከትኩት ነገር ቢኖር ማኅበሩ ከምሥረታው ጀምሮ የተጭበረበረና የተምታታ አሠራርን የሚከተል ምን አልባትም ከገንዘብ አንጻር ትኩረቱን ያደረገ ይመስለኛል:: ምክንያቱም እንደ ውጫሌ ውል በአማርኛው ያካተተው አንቀጽ /Article/ በእንግሊዝኛው ከሠፈረው ጋር ሰፊ ልዩነት ይታይበታል::

***<u>የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርና ሌሎች ፀረክርስትና ሥራዎች</u>***

ማኅበሩ ከኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ ውጭም ሌሎች መጻሕፍትን ሲያሳትም እንዲሁ ለመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪኖች ግድ የለሽና ኀላፊነት የማይሰማው አካሄድ እንደተጠቀመ ከበቂ መረጃዎች ጋር

[225].የኢትዮጵያ መ/ቅዱስ ማሕበር የመተዳደሪያ ደንብ:1968:ንግድ ማ/ቤት:ገጽ4 ና Page 15



ማየት ይቻላል:: ከነዚህ መካከልም:- ቀላል አማርኛ የሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ አንዱ ነው:: የዚህን መጽሐፍ የትርጉም ሥራ ዋና ዓላማ የምደግፍና ሊበረታታም የሚገባው እንደሆነ ላሰምርበት እወዳለሁ:: ነገር ግን ማኅበሩ ከቆመለት የክርስትና እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪን ጥበቃ አንጻር፤ሥራውን በግዴለሽነት እያከናወነ መሆኑን ግን በህትመት ውጤቱ መረዳት የቻልኩትን ጥቂት ሀሳቦች ቀንጭቤ በማቅረብ ለአንባቢ ማሳየት እወዳለሁ:-

- በ1ኛ ቆሮ ምዕ1ቁ18 « የመስቀሉ ነገር ለሚጠፉት ...» ይላል

የመስቀሉ ቃል የሚለው ሀሳብ ተለውጦ *ነገር* በሚል ቃል ተተክቶአል:: ይህም የመጽሐፍ ቅዱስን አንኳር ነጥብ የሚያዛባ ሲሆን ***ቃል*** የሚለው ሀሳብ የወልድን የባህርይ ምንነት ትርጉም የያዘ ነው:: በእናት ቋንቋው/Ὁ <u>λόγος</u> γὰρ ὁ τοῦ ***<u>σταυροῦ</u>*** τοῖς μὲν ἀπολλυμένοις μωρία ἐστίν, τοῖς δὲ σῳζομένοις ἡμῖν δύναμις θεοῦ ἐστιν./

***<u>የተሠመረበት</u> ቃል የመስቀሉ ቃል*** የሚል ነው:: ዓውዳዊ ትርጉሙም ከቁጥር18 እስከ ቁጥር 24 የሚገኝ ሲሆን ቁ.23ና24 «... ለአሕዛብ ሞኝነት ነው ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም የእግዚአብሔር ኀይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው በማለት የመስቀሉ ቃልን ማንነት በግልጽ ያሳያል:: ይሁን እንጅ ለኦርቶዶክስ በታተመው 81ዱና ቀላል አማርኛ ትርጉም ላይ እንደ እስራኤላዊያን ደህንነት በተከናወነበት ቁሳቁስ ላይ የሰው አእምሮ እንዲያርፍ በማድረግ (***2ኛነገ ምዕ18ቁ3-6***) የጣዖት አምልኮን ልማድ ማኅበሩ በማበረታታት ላይ መሆኑ አሳዛኝ ሁኔት ነው (ቆላ1÷19-20)::

- በኤፌሶን ምዕ1÷17ና1ኛጴጥ ምዕ1÷3 ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ

አምላክና አባት በሚለው ሀረግ ላይ *አምላክ* የሚል ቃል በማጉላት /በመቁረጥ/ሲያሳትም ማኅበሩ ደንታ አልነበረውም:: በእናት ቋንቋው /*<u>ἵνα ὁ θεὸς τοῦ κυρίου ἡμῶν Ἰησοῦ Χριστοῦ, ὁ πατὴρ</u>* τῆς δόξης, δώῃ ὑμῖν πνεῦμα σοφίας καὶ ἀποκαλύψεως ἐν ἐπιγνώσει αὐτοῦ ይላል:: የጴጥሮስ መልእክትም /Εὐλογητὸς ὁ θεὸς καὶ *<u>πατὴρ τοῦ</u>*

<u>*κυρίου ἡμῶν Ἰησοῦ Χριστοῦ,*</u> ὁ κατὰ τὸ πολὺ αὐτοῦ ἔλεος ἀναγεννήσας ἡμᾶς εἰς ἐλπίδα ζῶσαν δι' ἀναστάσεως Ἰησοῦ Χριστοῦ ἐκ νεκρῶν, **ይላል::**

በዮሐንስ ወንጌል ከትንሣኤ በኋላ"...ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ..." ማለቱ ስህተት እንደነበር በማሳየት የክርስቶስን ንግግር የሚያርመ ደፋር መናፍቃንን የሚያበረታታው ማኅበሩ፤ ለኦርቶዶክስ ደብተሮችም የዚህን ምዕራፍ ትርጉም እንዲያበላሹት ፈቅዶ በተመሳሳይ መንገድ አትሞአል:: ለክርስትና የቆመ ነው? ወይስ??? ለሌላ የሚያሰኙ ክንውኖችን የሚፈጽመው ይህ ማኅበር ባለማወቅ ወይስ እሆን ብሎ ይሆን? ፍርዱን ለአንባቢ እተዋለሁ::

***<u>ፀረ ክርስትና አርማዎች</u>:-*** መንፈስን የማይለየው የማኅበሩ የበላይ አመራር ከኑሮና ከገንዘብ ማግኛ አንጻር እንጅ ፤ ለትውልድም ሆነ ለልዑል ቃል አስቦ እንደሚሠራ ማመን አስቸጋሪ ያደርገዋል:: ምክንያቱም በጥቃቅን በራሪ ጽሁፎችና በአንዳንድ የመጽሐፍ የውጭ ገጾች፤እንዲሁም በብሮሸሮች ፀረ ክርስትና አርማዎችን በልዩ ልዩ ጊዜያት ሲያሳትም ሀይ ያለው አልነበረም:: ሁሉም ምስሎች ማለት ይቻላል የኦርቶዶክስ ደብተሮች የጥንቆላ ጠልሰም ናቸው::

በጥንቆላ እና በመጽሐፍ ገለጣ እንዲሁም በኮከብ ቆጠራ ሥራ የተሰማሩ የማውቃቸው ደብተሮች፤አርማውን እንዲያነጻጽሩት እና ለምን እንደ ሚጠቀሙበት አሳይቻቸው የጥቂቶቹን ምስልና የሚያከናውኑበትን ዓላማ ገልጸውልኛል:: ማኅበሩ የሚጠቀምባቸው አብዛኖቹ ጠልሰሞች በድግምት ሥራ ውስጥ ለከፍተኛ የሟርት አሰራር እንደሚጠቅሙ አረጋግጠውልኛል:: ብዙ ተመሳሳይ ጠልሰሞችንም ሰጥተውኛል::

በሌሎች ሀገራት የማይታዩ የመስቀል ሥራዎች /አርት/ በሀገራችን በብዛት ተስፋፍቶአል:: ለምሳሌ የአክሱም ዘመን፣የላሊበላ ዘመን፣ የፋሲል ዘመን መስቀሎች፣የመሳፍንት ዘመን መስቀሎች ይሏቸዋል:: የጥበብ ሥራውን ባልቃወምም የውስጥ ዓላማውና መንፈሱ ግን



**አጋንንታዊ ስለሆነ ልንቃወመው ይገባል የሚል እምነት አለኝ:: የጥንት ጠላታችን እባብ የተባለው ዘንዶ ዲያቢሎስ፤በመስቀሉ ይረገጣል እንጅ በመስቀሉ ተውቦ ጎንበስ ቀና እያልን አምልኮንና ክብርን ልንሰጠው አይገባም:: እባብና ዘንዶ በመስቀሉ ሥራ ተዋርደውበታል እንጅ አይዋቡበትም:: በማኅበሩና በኦርቶዶክስ "ቤተ ክርስቲያን" ደብተሮች ግን እያከናወኑ ያሉት ከዚህ በተቃረነ መልኩ ነው:: ለአንባቢ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ሁለቱን ብቻ ምስሎች ከደብተሮቹ ጠልሰም ጋር በማነጻጸር ለማሳየት እሞክራለሁ:-**







***<u>፩ቱእባቦች የሰለጠኑበት</u>*** ***<u>፪ቱእባቦች የሰለጠኑበት</u>***

**አንባቢ ሌሎች ምስሎችን ለማነጻጸር ቢፈልግ፤በማዕከላዊ ዶክመንቴሽን ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን 1996 እትምን በመስቀል መለያ ቁጥር G-V-27፤30፤38 ኡራኪዳነ ምሕረትና መ.ቁ G-V-416፤415 ይጋንዳ ተ/ኀይማኖት እንዲሁም በመስቀል ቁጥር G-V-304 መሐል ዘጌ ጊዮርጊስ ምስሎችን በመመልከት በመስቀል ስም የሚፈጸመውን አጋንንታዊ አምልኮ በጥቂቱ መመልከት ይችላል[226] ይህ ክርስቲያናዊ ማኅበር ክርስትናን ለማስፋፋት ቁልፍ መንገድ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ለማሳተም ለማሰራጨትና ሰዎችም ለማንበብ የሚችሉ**

---

[226] .የቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን አማራ ክልል:ማዕከላዊ ዶክመንቴሽን ቅርስጥናትና ጥበቃ:1996

የአምላክ ቃል በአንድ ሃይማኖት ተቋምና አቋም /Denominational Ideology/ ሲዛባና እንደ ተራ ገድላ ገድል ወይም ድርሣናት ሀሳቡ ሲለወጥና ተቆርጦ ሲቀጠል መቃወም ካለመፈለጉም በላይ ድጋፉን እንዴት ሊሰጥ እንደቻለ ለሁሉም ክርስቲያን በቂ የሆነ ምላሽ መስጠት እንዳለበት ግን አምናለሁ:: እኔ በግሌ የማኅበሩን አመራር ጠይቄ በቂ ምላሽ አላገኘሁምና::

## *ክፍል ስድስት*

### *መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ እናጥናው?*

መጽሐፍ ቅዱስ/Bibel/የብዙ መጻሕፍት ስብስብና ከሌሎች ጽሑፎች የተለየ እንደ ማለት ነው:: ባይብል የሚለው ቃልም ቢቢልያ/Biblia/ ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሆኖ ብዙ ጽሁፎችን ወይም መጻሕፍትን ያካተተ ማለት ነው[227]:: ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎችና ከ1600 ዓመት በላይ በሆነ የዘመን ልዩነት ውስጥ የተጻፈው ይህ መለኮታዊ ጽሁፍ ለሰዎች የተጻፈ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለልዑል አምላክ ማንነት በጥልቀት እንድናውቅ ባይረዳም ይጠቁማል:: ስለሰው ባህርይና አኗኗር ማንነትና ከየት መጣነት፤እንዲሁም በዚህ ዓለም እንዴት መመላለስ እንዳለብን ግን በስፋት ያስተምራል:: ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ብለን መጽሐፋችንን ስንገልጥ ስለ እግዚአብሔር ከየት መጣነት ሳይናገር ስለፍጥረት ጅማሬ ያሳያል:: ከዚያም ሰማያዊያን ፍጡራን በሰው ዓለም ውስጥ ገብተው ስለፈጸሙት ሁነት ጠቁሞ፤ስለሰው ልጅ ውርደት የትንሣኤ ምስጢርና ኑባሬ እያተተ ይሄዳል:: መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች ልዩ ልዩ የሆነ የነፍስ ዕውቀት ያላቸው ቢሆኑም፤አንዳቸውም ከዚህ ቋት አላካፈሉንም:: የመጽሐፉ ባለቤት የሆነው መንፈስ ቅዱስ የራሱን ሀሳብ ብቻ በወደደውና በሰዎች የመግባቢያ ባህል ቋንቋና ዘዮ አጽፎልናል 1ኛ ጴጥሮስ 1፥21::

[227] Rev.William Evans/Dr/:The Great Doctrines of The Bible;1939:Moody press,Chicago.



ከፀሐፊዎቹ ውስጥ የጥቂቶቹን ማንነት ብንጠቅስ የጦር ጄነራሎች (ኢያሱ)፤ነገሥታት (ዳዊት ሰሎሞን)፤ምሁራን (ጳውሎስ ሉቃስ)፤ ዋርካ ለቃሚ ወይም እረኞች (አሞጽ)፤ምንም ያልተማሩ አሣ አስጋሪዎች (ዮሐንስ ጴጥሮስ) ወዘተ... የነበሩ ናቸው:: ወደ ኋለኛው ዘመን ሄደው የፍጥረት ጅማሬን ጽፈዋል (ሙሴ፤ዳዊት፤ኢዮብ)፤ወደ ፊተኛው ዘመን ሂደው ደግሞ ፍጻሜ ዓለምንና የሰውን መደምደሚያ ተናግረዋል (ዳንኤል፤ጳውሎስ፤ዮሐንስ) እነዚህ ቅዱሳን በራሳቸው ማንነት ሁለቱንም ጽንፎች የማሳየት አቅምም ሆነ ችሎታ የሌላቸው ሲሆን፤የመንፈስ ቅዱስ መጠቀሚያ ለመሆን ግን እራሳቸውን የሰጡ ነበሩ:: መጽሐፍ ቅዱስ ሳይንሳዊ ሀቅን የያዘ መጽሐፍ ነው ነገር ግን የሳይንስ መጽሐፍ አይደለም:: የፍልስፍናና የከዋክብትን ልዩነትና አንድነት እንዲሁም የሥነ ተፈጥሮ ሁነቶችን የሚያሳይ ነው:: ነገር ግን የፍልስፍናም ሆነ የከዋክብት ጥናት መጻሕፍት አይደለም:: የግጥም መድብልና የሳይኮሎጅ፤የጂኦሎጅና ሶሾሎጅ እንዲሁም ያስትሮሎጂ ሁነቶችን የያዘ መጽሐፍት ነው:: ነገር ግን የግጥም መድብል ወይም የሳይኮሎጅና ሶሾሎጅ መጽሐፍ አይደለም:: ዘመን የማይሽራቸውን ፍጹም እውነቶች ብቻ የያዘ መለኮታዊ ጽሁፍ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ /ቅዱስ/ የተባለበት ዋና ነጥብም የማይለወጠውን የፈጣሪ ቃል የያዘና፤ ፈጣሪ እግዚአብሔርም የማይለወጠውን ቃሉን በመጽሐፍ እንዲጻፍ ስላዘዘ ነው:: የንጉሥ ቃል ነውና አይለዋወጥም (መክ8፥4)ብቸኛ ቅዱስ ነውና አይቀየርም (ኢዩብ6፥10) ዘለዓለማዊ እውነት ነውና ሐሰት የለበትም ታማኝ ቃል ነው (ቲቶ1፥9)የእርቅና የማስታረቅ ቃል ነው (2ቆሮ5፥20) የፀጋ ቃል ነው (ሐዋ14፥3፤ዕብ1፥1-2):: የሰው ልጅ መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ቢያነብና መመሪያው ቢያደርግ ከሃይማኖትና ከፖለቲካ ከንቱ ቀንበር ይላቀቃል አርነትም ይወጣል:: ምክንያቱም ሁሉም ፀረ መጽሐፍ ቅዱስና ፀረ እግዚአብሔር አካሄዶችን የያዙ ቀንበሮች ናቸውና [228]::

### ሃይማኖተኞች መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ለምን ይፈራሉ?

[228] ጌታችን የሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከት ዘመኑ ፖለቲከኞችንም ሆነ የሃይማኖት ሰዎች ጋር ብዙ ቀረቤታ ታአለነበረውም:: ምክንያቱም ሁለቱም ይፈሩት ነበርና:: ክፉ አስተሳሰባቸውን የተቃወመ ሲሆን በሁለቱም ድርጅቶች ውስጥ ያለውን ክፋት ሳይተባበር ነው የፈጸመው::

ድምፄን ይሰማሉ የሚለውን ቃል ለመረዳት የአይሁድን የበግ እርቢ ዘዮ የማያውቅ ሰው እንዴት ድምፅ ይሰማሉ? ይላል።ከዚህም በላይ የመልእክቱን ክብደትና ጥንካሬም ሳይረዳው ያልፋል ምሳሊያዊ አባባሎችን በጥልቅ በመመርመር ዋና ሀሳባቸውን አግኝቶ መረዳት የመልእክቱን አንኳር ነጥብ በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል። ለምሳሌ:-

*1ኛ.<u>ሙሉ መጽሐፉ አንድ ወጥ መሆኑን በሚገባ መረዳት</u>* :- ብሉይም ሆነ ሐዲስ ኪዳን ዓላማውና ግቡ አንድ ስለሆነ ደራሲው መንፈስ ቅዱስ ሕያው አምላክ ነውና ያለ ዘመን ርቀት ሀሳቡን በሰዎች ዘመን ስሌት ሳይለያይ ያስተላለፈበት ነው። ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎችና ከ1600 ዓመት በላይ በሆነ የዓመታት ልዩነት ቢጻፍም ወጥና አንድን ጥቅል ሀሳብ የያዘ ቅዱስ ነው (ዮሐ5፥39)።

*2ኛ. <u>ትንቢታዊ የሆነ ኀይለ ቃልን እንደያዘ በመረዳት</u>*:- ከሰዎች ድርሰት የሚለይበትና የሰውን አእምሮና የእውቀት ደርዝ የሚገዳደርበት የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ባህርይው፤ ዘመን ተሻጋሪ ትንቢታዊ ቃል በመያዙ ነው። ለዚህ ነው በኢሳይያስ ምዕ44፥7 "እንደኔ ያለ ማን ነው?... የሚመጣውንም ነገር ሳይደርስ ይንገረኝ" ሲል የሰውን የአቅም ውሱንነት ይገዳደራል። እግዚአብሔር የተናገረውን መጭ ዘመን ያለምንም ጉድለት የሚከናወን መሆኑን ሲናገርም በዘዳ18፥21 "ነብዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገር ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም ያ! ነገር እግዚአብሔር ያልተ ናገረው ነው" ሲል ልዑል የተናገረው ሁሉ የሚፈጸም መሆኑን ይጠቁማል። ዳዊት በ1000 ዓመተ ዓለም ስለክርስቶስ የተናገረው ትንቢት ግልጥናየአንድን ግለሰብ ታሪክ የሚያሳይ ነበር መዝ22፥16-18 በዚያን ዘመን ወንጀለኛ ሰው በስቅላት ስለመቀጣት ፈጽሞ የማይታሰብበት ጊዜ ነበር። ወንጀለኛ በስቅላት መቀጣት የተጀመረው በ250 ዓ.ዓ. ቢሂላ በሮማውያን ሕግ ነው። ኢሳ ምዕ 53 የሚተርከው የክርስቶስ ስቅላትና የመከራ ሂደት ከ700 ዓመታት በፊት ነበር። ስለውልደቱና የውልደት ቦታው ደግሞ ሚክያስ በምዕ5፥2 ሲናገር ከክ/ል/በፊት በ701 ዓ.ዓ በፊት ነበር። ይህ ሁሉ ታሪክ የተፈጸመው ግን ከ30 ዓ.ዓ ቢሂላ ነው ማቴ2፥1ና ሉቃ2፥4-7።



*3ኛ. <u>የሚጣረስ አለመሆኑን በመረዳት</u>* :-ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ የሚጋጭ ይመስላቸዋል። በርግጥ አንዱን ታሪክ በተለያየ የትኩረት አቅጣጫ ሆነው ጸሐፊዎች ሲጽፉት ትኩረት የሰጡትን ክፍል ብቻ በአትኩሮት ስለጻፉ ትኩረት ላልሰጡት ክፍል ደግሞ በቀላል አገላለጽ ሲያልፉት ይመስላል። <u>ለምሳሌ</u> በ4ቱም ወንጌላት የክርስቶስ ትንሣኤ የተዘገበ ሲሆን ሌላኛው ትኩረቱ ከተነሣ በሂላ ስላዩት ሰዎች ነው። ሌላኛው ደግሞ ስለተነሣበት ጊዜ ሌላው ስለድንጋዩ መንከባለልና ስለዘበኞች መደናገጥ ትኩረት ይሰጣል። በዚህ ሂደት ውስጥ ልዩነት አለ ማለት ሳይሆን የትኩረት አቅጣጫ መለያየት ነው። ይህ ደግሞ ሁሉንም ሁነቶች ለማወቅ ይረዳል። አንዱ የጻፈውን ሌላኛው እንዳለ ቢጽፍ ኖሮ ዛሬ ስድሳ ስድስት የሚባል የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ባላስፈለገንም ነበር።

*4ኛ. <u>የሰውን ሕይወት የሚለውጥ እንደሆነ ተረድቶ ማጥናት</u>*:- መጽሐፉን በምናነብበት ጊዜ ካለንበት የሃይማኖት ወይም የባህልና ልማድ አመለካከቶች ወጥተን፤ገለልተኛ በሆነ ሕሊና ማንበብ ተገቢ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት ቃል እንጅ የሃይማኖት መመሪያ አይደለም።የየትኛውንም ሃይማኖት ሀሳብ አይደግፍም ስለየትኛውም ሃይማኖት ሀሳብ አይናገርም። የሰው ሕይወት በሰዎች መካከል ትገኛለች ለሚያምንባት ብቻ መገናኝት ይሆንላታል ዮሐ1:10። መጽሐፍ ቅዱስ ስለሕይወት የሚተርክ ሲሆን ከሕይወት ጋር ሰዎች ይገናኙ ዘንድ ብቻ ያትታል። ሙት የሆነው የሰው ማንነት ሕይወትን ያገኝ ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። የሰው ብርሃን የሆነችው ሕይወት በዓለም ያለችና የነበረች እንዲሁም ዓለም በእርሷ የሆነ ነው። ይህንን ሙሉ ጽንሰ ሀሳብ የተረዳ የመጽሐፍ ቅዱስን ማዕከል በቀላሉ መረዳ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ሕይወት የሚለውጥ ሙት የሆነውን ማንነት በትንሣኤ የሚያስነሳ ሲሆን፤ደካማ ሥጋዊና ምድራዊ አስተሳሰብን ማለትም ዘረኝነትን፤ ጎጠኝነትን፤ጥላቻንና ገዳይነትን ከውስጠኛው የጥልቅ ክፍሉ ያጠፋል። ስለዚህ ለለውጥ እራስን አዘጋጅቶ የሚነበብ መጽሐፍ እንጅ ለሃይማኖት መረጃ ለማግኘት ለባህልና ለወግ ማጠናከሪያ ጥቅስ ለማውጣት የሚነበብ አይደለም የለውምም።

***5ኛ.ከእግዚአብሔር የመጣ የመገለጥ ቃል መሆኑን በመረዳት፡-*** መገለጥ ማለት ከጨለማው የሰው ዓለም አምልጦ መውጣት ነው። በጴጥሮስ ሕይወት የሆነውን የመገለጥ ኀይል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይገልጠዋል "ትዳሩን ልጆቹንና ከተራራው ሥር የነበሩ ጓደኞቹን በመርሳት በፊት የሚያውቀውን የሱስ በመለኮታዊ ነጸብራቅ በተመለከተው ጊዜ ለኤልያስ ቤትን ለመስራት ጠየቀ ላንተ ለሙሴና ለኤልያስ ሦስት ጎጆዎችን እንስራ ለኛ በዚህ መሆን መልካም ነው ማቴ17፥6-8 ነበር ያለው። ስለዚህ ዛሬም ቃሉን ስናነብ መገለጡን በመናፈቅና የመንፈስ ቅዱስን አብርሆት /ሬማ/ በመጠበቅ እንጅ ፊደላዊ የሆነ የአእምሮ እውቀትን ለማዳበር አይሁን። ሰው እግዚአብሔርን በቃሉ መገለጥ ካገኘው ራሱንና ማንነቱን ያለውንም ሳይቀር ይተዋል። በቃሉ መገለጥም ልዑል ይታወቃል 1ሳሙ3፥21። ሰው እግዚአብሔርን ባወቀ ጊዜ በራሱ ላይ ያለውን የጨለማ ዓለም ያቆማል ያስወግደዋል ኢዮብ 28፥3ና ኤፌ5፥14፤ሰው በጨለማው ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በመገለጥ ከተረዳው፤የቃሉ ባለቤት እንድንኖርለት በፈለገው ልክና መጠን የመኖርን አቅም እናገኛለን። የራሳችን ማንነትም በልዑል ልጅ ማንነት ይተካና እንደ ፈቃዳችን ከመኖር በመለየት እንደ ፈቃዱ መኖርን እንጀምራለን። የክርስትናም መሠረታዊ ሂደት ይህ ነውና።

## ***<u>የቀኖናዊ መጻሕፍት መለያ መርሆዎች</u>***

ቀኖና/Canon mean standard or approved/ማለት ልኬታ፤ዋና መርህ ፤ማረጋገጫ ማለት ነው።ካኖን/Canonization/ማለት በክርስቶስ አካል (ቤተ-ክርስቲያን) ውስጥ አገልጋይ ሆነው በእግዚአብሔርና በሰው የተመረጡ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡና እራሳቸውንም የሰጡ ሰዎች፤ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጡበት ዝርዝር ማለት ነው። ይህ ቀኖናዊ መስፈርት ሐሰተኛ መጻሕፍትና ሐሰተኛ ሰዎች በእውነተኛ ሰዎች ስም የጻፉትን የሚለይ ነው። ለቀኖናዊ ውሳኔ ሀሳቦች እንደ መንደርደሪያ /መነሻ/ ሀሳብ የተጠቀሙበት መሥፈርቶች፡-

ሀ. ክርስቶስንና ክርስትናን በሚከተሉና በሚያውቁ ሰዎች መካከል ጥቂቶች የሚቀበሉት ወይም የተቀበሉት ከሆነ ፡-



ለ.በክርስቲያኖች ስብስብ ወይም ጉባኤ የተገኘ ወይም የቆየ መጽሐፍ ከሆነ፤ወደ ቀኖናዊ መስፈርቶች ሥር በመምጣት ይፈተሽ ነበር። የመፈተሻ መስፈርቶች ሆነው በጥንት ጊዜ በነበሩ ዋና የቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች ዘንድ የተቀመጡት ደግሞ 5ቱ መርሆዎች፡-

1. <u>ሥልጣን ያለው ሆኖ መታየቱ ወይም መለኮታዊና አምላካዊ ሥልጣንን የያዘ</u>፡- ይህ መርህ አንድን መጽሐፍ መለኮታዊ መመሪያን ለሰዎች የሰጠ አምላካዊ መርህንም የያዘ መሆኑ የሚፈተሽበት መለኪያ ነው፤ፀሐፊው "*እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ* የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ ወዘተ... የሚሉ ሀሳቦችን መያዙ የሚረጋገጥበት ነው። ምድራዊ ፣ ሥጋዊና አጋንንታዊ ሀሳቦች ነጥረውና ተለይተው የሚታዩበት ከሆነ ሥልጣን ያለው መለኮታዊ መጽሐፍ መሆኑ ከሌሎች ይለያል።

2. <u>ትንቢታዊ ሀሳብን የያዘ ከሆነ</u>፡- የነጠሩ ቀኖናዊ መጻሕፍቶች በዚህ ዋና መርህ ያለፉ ናቸው። ምክንያቱም የመጽያትን ጊዜም ሆነ ወቅታዊ የሕይወት መመሪያዎችን ማካተትና አለማካተቱ የሚፈተሽበት ነው። የድርሰቱ ባለቤት እግዚአብሔር ሆኖ ፀሐፊዎቹ እንደ እርሱ ፈቃድ የፃፉት ከሆነ (ዘፃ24፥4፣2ጴጥ1፥20-20)። ምክንያቱም ሁሉም መጻሕፍት ትንቢታዊ መልእክቶችን ይዘዋልና። የጳውሎስ መልእክቶች ጊዜያዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ የሚያፅናኑ ወቅታዊ መልእክት እንደያዙ ይታወቃሉ። ነገር ግን ሐዋርያዊ መልእክት በመሆናቸው ትንቢታዊ መልእክቶችንም አካተዋል። ለምሳሌ እነዚህን ክፍሎች ማየቱ ሀሳቡን ያረጋግጠዋል (ዕብ1፥1፣ገላ1፥1)።

3. እውነታነትን ብቻ የያዘ /Authenticity/፡- ይህ የቀኖና መለኪያ ወይም መርህ ብዙ የፍልስፍናና የሃይማኖት እንዲሁም የኑፋቄ መጻሕፍትን የሚለይ መመዘኛ ነው። እግዚአብሔር አምላክ እንጅ ሰው አይደለም (ሆሴ11፥9)። ስለዚህ ጥንት የተናገረውን አይረሳም ደግሞም አይዋሽም። በዚህ መርህ ብዙ መጻሕፍቶች ሲፈተሹ እስትንፋሰ መለኮት መሆንና አለመሆናቸው ይታወቃል። ተጨማሪ /አፖክሪፓ/መጻሕፍቶች በታሪክ፤በመለኮታዊ አጠቃላይ መርህ፤

በፍጥረት ሕግና እሳቤ በአምላካዊ የማይለወጥ ባህርያት ወዘተ... ሲፈተሹ ከቀኖናት ጎድለው የተገኙት በዚህ ሚዛን ነው:: ተጨማሪ /አፖክሪፓ/ መጻሕፍት ከሌሎች መለኮታዊ መጻሕፍት ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸውም የሚፋለሱ ናቸው:: አጠራጣሪነታቸውና የሐሰት ታሪክን ፣ዶክትሪንና የዘመን ስሌትን እንዲሁም አጠቃላይ የክርስትናን ሀሳብ የሚያፋልስ ትምህርትንም ይዘዋል::

4. <u>ሕይወት/ሕያውነት/ያለው ቃል መሆኑና የመተላለፍ አቅም ያለው /The life transforming ability or dynamic of writing/</u>:- የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ሥልጣን ያለው ነው ዕብ4፥12:: ስለዚህ ሕያውና ቀጣይነት የማይታይበት፣አጠራጣሪና የሐሰት ሀሳብን የያዘ ከሆነ መለኮታዊ የቀኖና መጽሐፍት ሊሆን አይችልም:: ጳውሎስ ሐዋርያዊ በሆነው የመጋቢነት ሥልጣኑ በመጠቀም ጢሞጢዎስን ሲያስጠነቅቀው እንዲህ ይላል " ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ እራስህንና የሚሰሙህን ታድናለህ" (2ጢሞ3፥16-17፤1ጴጥ1፥23፤2፥2፤2ተሰሎ2፥2)በሁኔታዎችናበወቅታዊ የሃይማኖት ጥበቃና ማስፋፊያ ሲባል መጽሐፍ ቅዱስ አይሻሻልም አይለወጥም:: ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ትምህርት እንደተሰጠን ማስተላለፍ ተገቢ ነው:: ተጠንቀቅ የሚለው መመሪያም ለዚህ የሚሆን ነው:: ብዙ ሃይማኖተኞች በነፍስ ዕውቀቶቻቸው /The Latent of soul/ በመንቀሳቀስ የኔ የሚሉትንና እራሳቸው የመሠረቱትን ሃይማኖት ለመታደግ የእግዚአብሔርን ትምህርት ይለውጣሉ::

ይሁን እንጅ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ መሰሉን አካሄድ እንዳ ንጠቀም ያስጠነቅቀናል::"ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታ ገሱበት ዘመን ይመጣል፤ነገር ግን ጆሯቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ እውነትንም ከመስማት ጆሮዎቻቸውን ይመልሳሉ" 2ጢሞ4፥3:: መጽሐፍ ቅዱስን የምናነበው ለየሃይማኖቶቻችን ድጋፍ ልንፈልግ ሊሆን አይገባም ቃሉ የሚለውን ተቀብለን ለማመን ብቻ ነው:: በዚህ የመለያ መስፈርት መሠረት መጻሕፍቱ ቅዱስና ቅዱስ አለመሆናቸውን የጥንት አባቶቻችን ከቀኖና መጻሕፍት ላይ እንዳይደመሩ ከልክለዋል:: ተጨማሪዎቹ መጻሕፍትም ቀጣይነትና



ተሻጋሪ የሥልጣን ቃልነታቸው ደካማ ስለሆነ ቀኖናዊ አለመ ሆናቸውን በየጊዚያቱ አውጀዋል መመሪያዎችንም ሰጥተዋል::

5. <u>ፀሐፊው በጊዜው በአማኞች ተቀባይ የሆነ ወይም</u> እግዚአብሔር <u>በሥልጣኑ ኀይል አገልጋይነቱን ያረጋገጠለት፤እንዲሁም ጌታ የሱስና ሐዋርያቱ የጠቀሱለት ሊሆን ይገባል</u>:- በእግዚአብሔር መንግስት ሥራ ውስጥ በሰዎች ዘንድ የቅድሚያ ቅባሎቶች የሉም:: ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ሥልጣንና ኃይሉን በፈቃዱ ለጨለማው ገዥ ያስረከበበት የፍጥረት ታሪክ በመሆኑ ነው:: የሰው ብቻ ሀሳብና አመለካከት የብርሃንን መገለጥ ስለሚጠላ ሁልጊዜም መቃወሙ አይቀርም:: ነገር ግን በአሸናፊዋ የልዑል መንግስት ውስጥ እስካለና ጸንቶ እስከተገኘ ድረስ ማሸነፋም ሆነ ተቀባይነት ማግኘቱ አይቀሬ ነው:: ሙሴና አሮን በአገልግሎ ታቸው ላይ ጥቂት ሰዎች በተቃውሞ በተነሱባቸው ጊዜ ልዑል በሥልጣኑ በመገለጥ ቅባሎትን አምጥቶላቸዋል (ዘኁልቁ 16):: በተጨማሪም የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ቀኖናዊነት የምናረጋ ግጠው በመጽሐፍቱ ባለቤቶች በአይሁዳዊ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነትን ሲያገኙ ነው:: እንዲሁም በሐዲስ ኪዳን ዘመን ጅማሬ ክርስቶስም ሆነ የበኩር አገልጋዮቹ (ሐዋርያት) የሚጠቅሷቸውና የጠቀሷቸው ተፈጻሚነታቸውም በግልጽ የታዩ ሊሆን ይገባል::

<u>ለምሳሌ</u> ፩. <u>*ጌታችን የጠቀሳቸው*</u>:- ማቴ4፥7 (ዘዳ6፥16)፣ማቴ4፥10 (ዘዳ6፥13) ፣ማቴ15፥7 (ኢሳ29፥13) ፣ማቴ21፥16 (መዝ8፥2)፣ማቴ21፥42 (መዝ117፥22) ፣ሉቃ11፥30 (ዮናስ3፥1)፣ሉቃ11፥31 (1ነገ10፥1)

፪. <u>*ደቀ-መዛሙርቱ የጠቀሷቸው*</u>:- ማቴ1፥23 (ኢሳ7፥14)፣ማቴ2፥5 (ኢሳ23፥1እና ሚክ5፥2)፣ ማቴ2፥18(ኤር31፥15)፣ ማቴ4፥6 (መዝ90፥11) ፣ዕብ3፥15 (ዘኁል 14፥22) በጥቂቱ ጠቋሚ መረጃዎቻችን ናቸው::

- ------------------: ከዐዒ ይኩኑ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል 2ኛ መጽሐፍ በ28ኛው ዘመን ንግሥና:ተስፋ ማተሚያ ቤት
- ——————: የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐዒልብነ ድንግል - ዐዒቴዎድሮስ: 1949:ት/ማ/ቤት
- ——————: ዐዒ ዩሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት!1982!ኩራዝ አሳታሚ
- --------------------: ከዐዒ ቴዎድሮስ -ዐዒ ኃይለ ሥላሴ:1952:አዲስ አበባ
- ቻርሊስ ሲራይሪ:የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ:አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት (Chareles Serayera)
- ያሬድ ግርማ ኀይሉ:የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ሲነፃፀር: 1999:አሚይጵሪንተርስ ማተሚያ ቤት
- ጸሐፊ ትዕዛዝ ገ/ሥላሴ:ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ሚኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ: 1959:አ/አ
- ፓውል ኤንዝ(ዶ/ር)(Docter Poul Aenze):ታሪክዊ ሥነ መለኮት አመጣጥና ትንተናው:1993: አርቲስቲክ ማ/ቤት
- ጴርጋሞን:መንፈሳዊ መጽሔት 1994 ዓ.ም.
- Abbaye De Maredsous&Metzger,Bruce mannonrs:A concordance to the Apocrypha/Deuterocanonical Books:1983:William.B.EPub.
- A.G.Hebert;The Authority of the Old Testament;Faber& faber LTD 24:London
- A.Harnack Geschichte Der Altkirchlichen Literatur, Dieveberlie ferung T.v.1886 T.II T.I 1893
- -----:Der Altkirchlichen Literatur,Dieveberlieferung:1893:T.v.T.II,T.I
- Amplified Bible: Zondervan P.H:1987:Michigan 49530,U.S.A
- Bruce M.metzger,AnIntroduction to the Apocrypha,195, NY.
- Beatitude+JUSTINIAN(Patriar):The Chritian Orthodox Confession of Faith, 1952,Bucuresti.
- C.f Moses Hadas: Aristeas to Philocrates:1951:N.Y & London.
- Chr. Wordsworth, D.D., Bishop of Lincoln, vol. II,1887,New York: James Pott & Co.
- Connolly; The use of didache in the didascalia,J.T.S 24/1924
- Cornill: Introcuction to the Canonical Books of the Old Testament: 1907,London.
- Cowley.R.W. The Biblical Canon of the Ethiopian Orthodox Church Today:1974:Ostkirchliche.
- David Noel Freedman:The Anchor Bible Dictionary:1992: Doubleday, NewYork Vol. I





- Donald Guthrie: Chart of Old Testament Biblical canons: Canonical pseudepigrapha in New Testament criticism last up date 21,April 2008.
- E.Vlleadorff: Exploration & Study of Abyssinina:1945:Asmara.
- Fr. Tadros Yacoub Malaty:Revised bySamy Anis DrNoraElAgamy : Introcuction to the Coptic Orthodox Church: ISBN977-500508n6
- Graham Hancock:The sign and the seal:1992:Crown Pub.Inc.NY.
- Havpert,R.S.:The Transcription Theory of the Septuagint:1934:JBI
- Heeren,A.Vander,The Septuagint Version in The Catholic Encyclopedia,vol.XIII.
- J.Bienner:Geschichte Der Novellen Jnstiniaus:page 167
- Jellicoe: S.The septuagint and modern study,oxford,1968.
- : S.Studes in the septuagint:origins,Recnsions,and Inter pretations,1974,New Your.
- Josef T. Milik (with Matthew Black). *The Books of Enoch: Aramaic ,Fragments of Qumran Cave 4* :1976,Oxford,Clarendon.
- ------------ :Turning Points in Ethiopian History:1966:RSE 21
- Johannes Kirchhofer: *(Quellensammlung zur Geschichte des Neutes tamentlichen Kanons bis auf Hieronymus* (Zürich: Meyer and Zeller, 1844/, *A Select Nicene and PostNicene Fathers of the Christian Church*, vol. 4,1892,New York. (English translation is based upon the version published)
- Lancelot C.L.Brenton, The Septuagint with the Apocrypha: Greek&English,1998,Hndrickson
- -------------: The Septuagint Version Greed &English :1970,London.
- Lewis,J.J.:The Table Section in the Letter of Aristeas:1966.
- Littman,E.,The legend of the Queen of Sheba in the tradition of Axum:1904:Leiden.
- Mansi:Sacropum Conciliorum nova et Amplissima Colletio, Asutria 1960-61.
- Meccham,H.G.:The Letter of Aristeas:1935:Manchester.
- Melvink.K.H.Peters:Septuagint in The Anchor Bible Dictionary (doubleday 1992)vol I
- ----------------: Septuagint in The Anchor Bible Dictionary (doubleday 1992)vol 5

- Murad Kamel/Dr/: Deutrocanonical Books Introduction to The Coptic O/C Arabic Vers.webSite.
- Muhammad (Dr):**Qur'an**: Taqi_ud_din Al_Hilai and Muhsin Khan: 1417 A.H
- PAULN BENWARE: The Essential Bible Survey of The Old Testament:1993: Moody Publishers,Chicago
- Pfeiffet,R.H.:History of New Testament Times with an Introductio to the Apocrpha:1949:New York.
- Philip schaff:Creeds Christendom,Grand Rapids;BokerBookHouse 1977,vol.III,page 489
- Sawirus Ibn-Mukafta: History of the Patriarchs of the Egyptian Church:vol. II Pt. II
- Sergew Hable Sellassie(Prof.):Ancient and Medievl Ethiopian History:1972:United printer Addis Abeba.
- SIDNEY JELLICOE:The Septuagint and Modern Study,1968: Oxford University.press
- Sperber Alexander:Septuaginta Probleme:1929:Stutgart.
- Siegfried Meurer,ed.:The Apocrypha in Ecumenical Perspective :1991:NewYork.
- R.H.Charles,D.Litt.,D.D.The Apocrypha and Pseudeplgrapha of the Old Testament:Vol.II 1973,Oxfored at the Cla.Pre.
- R.J.H.Shutt: Latter of Aristeas:3rd Cent – 1st Centur A.D New Translation and Introduction.
- Robert J.Sargent: Canonization the Apocrypha :
- St.Luke and the Letter of Aristeas:JBL 80(1961)Thackeray H.ST.J. The Septuagint and Jewish Worship:1923:2ND Ed.London.
- Swete H.B:The latter of Aristeas,In An Introcuction to the Old Teastament in Greek,1902,Cambridge.
- Ullendorff,E.,Ethiopia&The Bible,London,1968,Oxford Univ.pres.
- Wilbur O'Donovan; Biblical Christianity in Africa Perspective, 2006,SriLank
- Willian Evans,(Rev.,Ph.d.,D.D.);The Great Doctrines of the Bible; 1939, Moody Press, Chicago.
- Williams: The text & Canon of the New Testament, 1960, london.


የማውጫ እርምት:- ክፍል 2 ቁ 4 የእርምት ገጽ 34

ቁ 5 የእርምት ገጽ 37

ክፍል 3 ቁ 1 የእርምት ገጽ 80

ቁ 4 የእርምት ገጽ 91

ክፍል 4 ቁ 1 የእርምት ገጽ 91

ቁ 2 የእርምት ገጽ 93

ክፍል 5 ቁ 1 የእርምት ገጽ 132

ክፍል 6 ቁ 1 የእርምት ገጽ 141

## የውስጥ ገጾች ሩት ኖታቸው በሕትመት ምክንያት የተዛቡ ማጣቀሻዎች የማስተካከያ እርምት

የገጽ 20 ማጣቀሻ ቁጥር 52 .ράλλη-ηοτλή: Σύντα:γμα των Θειων κυὶ Ιερων καὺονων T.B page 109

የገጽ 22 ማጣቀሻ ቁጥር 63 .Παύλου Σουηδίας Η ἒν Καρθαγένη Σῦνοδος τοῦ 419 "Aksum Thyateira" A Festschrift for Archb....

የገጽ 23 ማጣቀሻ ቁጥር 65 .ράλλὴ ποτλῆ Σῦνταγμα των θείων κυὶ Ι'ερών κανὸνων Τ.Δ Page 78 – 80

የገጽ 24 ማጣቀሻ ቁጥር 68.Στ Σάκκου ΉΛθ εορταδτικὴ ἑπιδτολὴ τοῦ Μ'Αθαναδὶου 1973 – 1974 page 9 *Quellensammlung zur Geschichte des Neutestamentlichen Kanons bis auf Hieronymus* (Zürich: Meyer and Zeller, 1844), pp. 7-9. *A Select Library of the Nicene and Post-Nicene Fathers of the Christian Church*, vol. 4 (New York: 1892), pp. 550-5.

## የገጽ 30 ማጣቀሻ ቁጥር 75

[1] .ράλλὴ ποτλῆ Σῦνταγμα των θείων κυὶ Ι'ερών κανὸνων Τ.Δ Page 365 – 367

የገጽ 60 ማጣቀሻ ቁጥር131 .In Hebrew: יְהוּדִית Yehuwdiyth {yeh-ho-deeth'} mean: ...